# የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ።

## መቅድም ።

### (ሀ) ከልማዳዊ ፡ ወደ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ስለመሸጋገር ፡—

ከ፲፭፻፲፪ ፡ እስከ ፡ ፲፭፻፲፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ ፖርቱ ጋሉ ፡ አልቫሬዝና ፡ ከ፲፯፻፷፩ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፷፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአገር ፡ ጐብኝነት ፡ መጥቶ ፡ ከነበረው ፡ የስኮትላንዱ ፡ ብሩስ ፡ ካቆዩልን ፡ ታሪክ ፡ በቀር ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ሌሎች ፡ አገር ፡ ጐብኝዎችም ፡ እጅግ ፡ ዝነኛ ፡ የሆነችው ፡ የንግሥተ ፡ ሣባ ፤ የአክሱም ፡ ነገሥ ታትና ፡ ያስደናቂው ፡ ባለታሪክ ፡ የካህኑ ፡ ዮሐንስ ፡ አገር ፡ የሆነችውን ፡ ከአፍሪቃ ፡ አሕጉር ፡ በንጉሦች ፡ የምትመራውን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ አፍሪካዊት ፡ ኢትዮ ጵያን ፡ በምስጢር ፡ ተሸፍኖ ፡ ይኖር ፡ የነበረውን ፡ ታሪኳን ፡ ገልጸውልናል [1] ። እነዚህ ፡ ባለታሪኮች ፡ ስለ ፡ ባሕሎቿዋ ፤ ስለፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ ልማዶቿዋ ፤ ከብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ ስለ ፡ ነበሩት ፡ ሕጎችዋ [2] ፡ ከሞላ ፡ ጐደለም ፡ ቢሆን ፡ በሚገባ ፡ አስተካክለው ፡ ጽፈውልናል ። ዘመኑ ፡ እጅግ ፡ በመራቁ ፡ የተነሣ ፡ ምልክታቸው ፡ ጭምር ፡ የጠፋውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ እናት ፡ በሆነችው ፡ አክሱም ፡ በምት ገኘው ፡ በጽዮን ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የነበሩትን ፡ የፍርድ ፡ መስጫ ፡ የችሎት ፡ አደባባዮች ፡ በጽሑፋችን ፡ ሳናነሳቸው ፡ ብናልፍም ፡ እንኳ ፡ ለምለም ፡ በነበረው ፡ በንጉሥ ፡ ፋሲለደስ ፡ ከተማ ፡ በጐንደር ፡ ይገኝ ፡ የነበረውን ፡ የቅር

---

[1] አ ፡ ኤም ፡ ዦንስ ፡ እና ፡ ኤ ፡ ሞንሮዩ ፡ የጻፉትን ፡ (ሂስትዋር ፡ ዳቢሲኒ) የሐበሻ ፡ ታሪክ ፡ የሚባለ ውን ፡ መጽሐፍ ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፴፭ እ ፡ ኤ ፡ አ) አ ፡ ዜርቮስ ፡ የጻፈውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፴፮ እ ፡ ኤ ፡ አ) አ ፡ ጂንጉልድ ፡ ዱፕሬይ ፡ የጻፈውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከጠ ላት ፡ ወረራ ፡ እንስታ ፡ ነፃ ፡ እስከ ፡ ወጣችበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የሚለውን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ የተጻፈውን ፡ አንደኛውን ፡ ቮሲዩም ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፶፭ እ ፡ ኤ ፡ አ) በተለይ ፡ ተመልከት ፤ በአዲሱም ፡ ዘመን ፡ ሆነ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የታወቀው ፡ የአገሪቱ ፡ መጠሪያ ፡ ስም ፡ ኢትዮ ጵያ ፡ ነው ፤ አቢሲኒያ ፡ (ሐበሻ) እየተባለች ፡ ትጠራበት ፡ የነበረው ፡ ቀርቷል ።

[2] በየጊዜው ፡ እየበረከቱ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከበዛው ፡ ከዘመናዊ ፡ ድርሰቶች ፡ መካከል ፡ ደግሞ ፡ ሐ ፡ ኖርደ ርን ፡ የጻፈውን ፡ በሐበሻ ፡ የመጨረሻው ፡ የአፍሪካ ፡ አምፒር ፡ የሚለውን ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፴፭ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ዣን ፡ ዱስም ፡ የጻፈውን ፡ በምኒልክ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ መካከል ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፵፯ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ማዳም ፡ ክሪስቲን ፡ ሳንድፎርድ ፡ የጻፈችውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አገዛዝ ፡ ሥር ፡ የሚለውን ፡ (ለን ደን ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ጂ ፡ ባክስተን ፡ የጻፈውን ፡ ትራቨልስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ (ለንደን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፶ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) እንደገና ፡ የታተመውን ፡ (ኤስ ፡ እና ፡ ኤር ፡ ፓንክረስት ፡ የጻፉትን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እና ፡ ኤርትራ) ፡ ኤሌክስ ፡ ብራክ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የታተመውን ፤ ኤ ፡ ሊትማን ፡ የጻፈውን ፡ አቢሲኒያን ፡ (ሐምበርግ ፡ ፲፱፻፴፭ እ ፡ ኤ ፡ አ) የታተመውን ፤ ኤም ፡ ካሚል የጻፈውን ፡ የንጉሦች ፡ ምድር ፡ (ኢንስ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ላንድ ፡ ኤም ፡ አውፍ ፡ ብሩች) ፡ ስቱትጋርት ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የታተመውን ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ዘርዝረን ፡ የጠቀስናቸውን ፡ ለጽሑፋችን ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ መጥቀስ ፡ በቂያችን ፡ መሆኑን ፡ በመገመት ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ የፖሊቲካ ፡ ጠባይ ፡ የተመሠረቱትን ፡ ወይም ፡ ፍሬቢስ ፡ ሐሜት ፡ የተሞላባቸውን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ የሆኑ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርሰቶችን ፡ ዋጋቢስነት ፡ በመገመት ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አስቀርተን ፡ ት ተናቸዋል ።

ንጫፎቹ ፡ ከንፍ ፡ ግርማ ፡ ጠቃሚነቱን ፡ በግልጽ ፡ የሚመሰክርለትን ፡ በድሮ ፡ ዘመን ፡ ነገሥታቱ ፡ እሥሩ ፡ እያስቻሉ ፡ ፍርድ ፡ የሚሰጡበትን ፡ ታላቁን ፡ የፍርድ ፡ ዛፍ ፡ ሳናስ ታውሰው ፡ አንቀርም ። ባለታሪኮች ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለትክክለኛ ፡ ፍርድ ፤ ስለ ፡ እውነተኛ ፡ ዳኝነት ፡ ያላትን ፡ ጽኑ ፡ ፍቅር ፡ ጽፈዋል ፤ እንዲሁም ፡ ጠበቃ ፡ እውነትን ፡ አብራርቶ ፡ ለመግለጽ ፡ ርቱዕ ፡ አንደበት ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ ይሰጠው ፡ የነበረውም ፡ ክብር ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ከፍተኛ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሲያስታውሱን ፡ በክርክር ፡ አቀራረ ቡም ፡ ረገድ ፡ እጅግ ፡ ዘዴኛና ፡ የአነጋገሩም ፡ ጣዕም ፡ ተወዳዳሪ ፡ እንደሌለው ፡ የሚገ መት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ በጠቅላላው ፡ አኗኗሩም ፡ በየዕለቱ ፡ ፍትሕን ፡ የማግኘትና ፡ የማስ ገኘትን ፡ ተግባር ፡ እንደ ፡ ፍጹም ፡ ሞያው ፡ የሚቈጥረው ፡ በመሆኑ ፡ በድንገት ፡ ተመ ርጦ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ በሚያይ ፡ ፈራጅ ፡ ፊትም ፡ ሆነ ፡ በደንብ ፡ በተቋቋመ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የችሎት ፡ አደባባይም፡ ጥንታዊውንና፡ የተከበረውን ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት[3] ፡ ጠንቅቀው ፡ የሚያውቁና ፡ የሞትን ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ቅጣትን ፡ ፍርድ ፡ ከመወሰና ቸው ፡ በፊት ፡ የነገሥታት ፡ ፍርድ ፡ መስጫ ፡ የሆነው ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት፡ የሚፈርዱ፡ ዳኞች፡ ባሉበት፡ ፍርድ፡ ቤትም፡ በሚያቀርበው፡ ክርክርና፡ በሚያ ስገኘው ፡ ፍርድ፡ የጥንቱን፡ የዳኝነት ፡ ወዳድነት ፡ የሚገልጽ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዱናል ።

አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ከተጀመረው ፡ ከአዲሱ ፡ ዘመን ፡ መግቢያ ፡ ዋዜማ ፡ ጀምሮ ፡ በተለይም ፡ የአዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ዘመናዊ ፡ የሥልጣኔ ፡ አስተዳደር ፡ ከተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ ማለት ፡ የዛሬው ፡ መሪዋ ፡ የሆኑት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የአገሪቱን ፡ አስተዳዳሪነት ፡ አደራ ፡ ተረክበው ፡ ዘውድ ፡ በተቀዳጁበት ፡ ቀን ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታወጀው ፡ የመጀመሪያው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጽሑፍ ፡ የተዘጋጀና ፡ ተጠናቆ ፡ በመጠቃለል ፡ የተደራጀ ፡ ሕግና ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ደንብ ፡ አልነበራትም ። የመሠረታዊ ፡ ሕጎችዋ ፡ ዋና ፡ ምንጭ፡ የነበረው ፡ ለጥንታዊው ፡ የግዛት ፡ ክፍሎች ፡ ዋና ፡ ለክርስቲያን ፡ ሕዝቡዋ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፤ በሐረርጌና ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ለሚኖረው ፡ በእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ለሚያምነው ፡ ሕዝቡዋ ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፤ እንደ ፡ አገሩ ፡ አነጋገር ፡ ትርጓሜ ፡ ደግሞ ፡ የጥንት ፡ ዘመን ፡ አረማውያን ፡ ፍጹም ፡ አፍሪካዊ ፡ ተብሎ ፡ ለሚጠራው ፡ ሕዝ ቡዋ[4] ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ነበራት ።

---

[3] ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ከጥንታዊው ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ላቪ ፡ ገዮዲሲ የር ፡) ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ መጽሔት ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፵፭–፩፻፵፮ ፡ በጥቅምት ፡ ፲፰ ፡ እና ፡ ፱ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በታተመውና ፡ እንዲሁም ፡ ረቩዊ ፡ ኢንቴርናሲዮናል ፡ ደክሪሚናሎዢ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ፖሊስ ፡ ቴክኒክ ፡ በተባ ለው ፡ መጽሔት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ዠኔቭ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በቍጥር ፡ ፪፻፶ ፡ በተለይም ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፶፪ ፡ እስከ ፡ ፪፻፷ ፡ ከፕሮ ፌሰር ፡ ዣን ፡ ግራቨን ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልከት ።

[4] በኢጣልያን ፡ የወራሪነት ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ በነበረችበት ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያና ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ፡ ተከፋፍለው ፡ በሚገኙት ፡ ክፍለ ፡ ሀገሮች ፡ አውራጃዎችና ፡ ወረዳዎች ፡ በሚኖረው ፡ በባሕል ፡ በልማድ ፡ በሃይማኖት ፡ ብዙ ፡ ልዩነት ፡ ባለው ፡ ሕዝብ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የአስተዳደርና ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ባሕላዊ ፡ ልማዱን ፡ በመግለጽ ፡ የተጻፉ ፡ ቍጥራቸው ፡ የበረከተ ፡ ድርሰቶች ፡ አሉ ፤ ከነዚህም ፡ መካከል ፡ በተለይ ፡ የምንጠ ቅሳቸው ፡ ካፖ ፡ ማስዛ ፡ የጻፈውን ፡ (አስመራ ፡ ፲፱፻፳፱) የታተመውን ፤ ፑታስዚ ፡ የጻፈውን ፡ (አስመራ ፡ ፲፱፻፳፱) የታተመውን ፤ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የጻፈውን ፡ (ፍሎራንስ ፡ ፲፱፻፴፯ እ ፡ ኤ ፡ አ) የታተመውን ፤ ኮስታንስ ፡ የጻፈ ውን ፡ (ሮም ፡ ፲፱፻፵ እ ፡ ኤ ፡ አ) የታተመውን ፡ ማስዙኪ ፡ የጻፈውን ፡ (ሮም ፡ ፲፱፻፵፬ እ ፡ ኤ ፡ አ) የታተ መውን ፡ ሚኒኒ ፡ የጻፈውን ፡ (ሮም ፡ ፲፱፻፵፭ እ ፡ ኤ ፡ አ) የታተመውን ፡ ሲሆን ፤ ከዚህም ፡ በቀር የኢጣሊያን ፡ አፍሪካ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለኢጣልያን ፡ አፍሪካ ፡ ሕዝብ ፡ ልማዶች ፡ ባሕሎችና ፡ ሃይማኖቶች ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በሁለት ፡ ቮሊዩም ፡ (ሮም ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ያተማቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ የጠቀስናቸው ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ስላለው ፡ ጉዳይ ፡ እንነዚህን ፡ ድርሰቶች ፡ ሁሉ ፡ በአጭሩ ፡ ለማስታወስ ፡ ብቻ ፡ ለጽሑፋችን ፡ ምንጭ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሆኑን ፡ ነው ።

## ፩ ፤ የነገሥታት ፡ ፍርድ ፡ መጽሐፍ ፡ ወይም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ።

ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የተባለው ፡ ሕግ ፡ በፍርድና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፤ በአስተዳደር ፡ አመራር ፡ ረገድ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ የያዘ ፡ ታሪካዊ ፡ ዓምድ ፡ ነው[5] ፤ እርሱም ፡ የሃይማኖትንና ፡ የብሔራዊን ፡ አስተዳደር ፡ በአንድነት ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ የላቀውን ፡ የክብር ፡ ደረጃ ፡ ይዞ ፡ እንዲኖር ፡ ያደረገው ፡ ይህች፡ አገር ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የእስክንድርያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የጥንት ፡ ሃይማኖት ፡ እምነት ፡ ተቀብላ ፡ የምትኖር ፡ ስለሆነች ፡ ነው ። የመጀመሪያው ፡ ፓትርያርኩዋ ፡ ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ አባ ፡ ሰላማ ፤ (የሰላም ፡ አባት) ፡ ብለው ፡ የሚጠሩትን ፡ የኒቅያውን ፡ ጉባኤ ፡ እምነት ፡ ደጋፊ ፡ የሆነው ፡ ቅዱስ ፡ አትናትዮስ ፡ በ፫፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የእስክንድርያን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ መንበር ፡ ወርሶ ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቆየ ፡ የፓትርያርክነት ፡ ማዕርግ ፡ ቀብቶ ፡ ሾመው ፤ ቀጥሎም ፡ በ፲፫ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ተቃራኒዎች ፡ ዙሪያዋን ፡ ከበዋት ፡ እጅግ ፡ የደከመችውንና ፡ በጠላት ፡ አደጋ ፡ ከባድ ፡ ሥጋት ፡ ላይ ፡ ትገኝ ፡ የነበረችውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማጠንከርና ፡ ለማበርታት ፡ ጠንካራ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ሥርዓት ፡ ማቋቋም ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ ፓትርያርክ ፡ ቄርሎስ ፡ ሣልሰኛ ፡ (፲፪፻፳፯ ፡ እስከ ፡ ፲፪፻፴፭) አንድ ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ በግልጽ ፡ አነጋገር ፡ የሃይማኖታዊና ፡ የብሔራዊ ፡ አስተዳደርን ፡ አቀላቅሎ ፡ የያዘ ፡ ደንብ ፡ በጽሑፍ ፡ ተለቅሞ ፡ እንዲዘጋጅና ፡ መምሪያ ፡ እንዲሆን ፡ አደረገ ። እነዚህም ፡ ቄርሎሳዊ ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩት ፡ ሕግጋቶች ፡ ከብሉይ ፡ ኪዳንና ፡ ከአዲስ ፡ ኪዳን ፡ ተውጣጥተው ፡ የተጠራቀሙ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ምንጮች ፡ ናቸው ። በውሳጣቸውም ፡ የብዙ ፡ ሐዋርያት ፡ መልእክቶች ፡ እንዲሁም ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔዎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሪዎችና ፡ አበው ፡ ያቆዩዋቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ተለቅመውና ፡ ተጠቃለው ፡ ይገኙበታል ። የዚሁም ፡ መጽሐፍ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍሉ ፡ የተመደበው ፡ የሃይማኖትንና ፡ የጸሎት ፡ ድርሰት ፡ ሥርዓትን ፡ በሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ (ከምዕራፍ ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፳፪) ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍሉ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ አንቲካ ፡ ዕቃዎችና ፡ ስለመንግሥት ፡ ሃብቶች ፡ አጠባበቅ ፡ ደንብ ፡ ነው ። (ከምዕራፍ ፡ ፳፫እስከ ፡ ፶፪) ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ የሚመለከተው ፡ ክፍሉ ፡ የሥራው ፡ ዝግጅት ፡ ሊከናወን ፡ የቻለው ፡ በ፫፻፳፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ መሪነት ፡ የተሰበሰበው ፡ የኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጣቸውን ፡ ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎችና ፡ ብይኖች ፡ ሰብስቦ ፡ በማጠቃለል ፡ በጽሑፍ ፡ ስለሠፈሩ ፡ ነው ። ፍትሐ ፡ ነገሥትም ፡ ተሠራ ፡ ተብሎ ፡ የሚታመነው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቆስጠንጢኖስና ፡ በሠለስቱ ፡ ምዕት ፡ ወይም ፡ ፫፻፲፰ ፡ ሊቃውንት ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አበው ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩት ፡ ብፁዓን ፡ ጉባኤ ፡ አድርገው ፡ በወሰኑት ፡

---

[5] ይህ ፡ የሕጎች ፡ ዓምድ ፡ የሆነ ፡ መጽሐፍ ፡ ኢኛሲዮ ፡ ጉይዲ ፡ በተባለ ፡ ሰው ፡ ተተርጉሞና ፡ ተብራርቶ ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ወይም ፡ የነገሥታት ፡ ሕግጋት ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ስለ ፡ ሐበሻ ፡ መንፈሳዊና ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ መግለጫ ፡ (ሮም ፡ በ፲፰፻፺፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፭፻፶፩ ፡ ገጽ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ታትሟል ፤ እንዲሁም ፡ የነገሥታት ፡ ሕግ ፡ ማብራሪያ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ኤል ፡ ዶ ፡ ካስትሮ ፡ (ሉቨርን ፡ ፲፱፻፳፩ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) አሳትሞአል ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ክፍሉ ፡ ጉይዲ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠውን ፡ ትርጉም ፡ በመደገፍ ፡ ኤር ፡ ዶ ፡ ሮሲኒ ፡ ካኔቫሪ ፡ የተባለ ፡ ጠበቃ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ወይም ፡ የንጉሦች ፡ መጽሐፍ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ የሐበሻ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጎች ፡ መጽሐፍ ፡ ተብሎ ፡ (ሚላን ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፫፻፲፰ ገጾች ፡ ተጽፏል ። የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘጋጅ ፡ በተቋቋመበት ፡ ጊዜ ፡ ለሥራችን ፡ ማከናወኛ ፡ ይሆኑን ፡ ዘንድ ፡ እንደመሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ መነሻ፡ ሆነው ፡ እንዲረዱን ፡ በማድረግ ፡ የተገለገልንባቸው ፡ እነዚሁኑ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስናቸውን ፡ ድርሰቶች ፡ ነው ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ከዘረዘርናቸውም ፡ በቀር ፡ ከነዚህ ፡ ብፊት ፡ የተጻፉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መጻሕፍት ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ እንደነዳርኑልድ ፡ (፲፰፻፵፩ እ ፡ ኤ ፡ አ) እና ፡ እንደነ ፡ ባከማን ፡ ያሉ ፡ ደራሲዎች ፡ ኮርፑስ ፡ ዡሪስ ፡ አቢሲኒዩም ፡ (፲፰፻፹፩ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) የተጻፉ ፡ ይገኛሉ ።

መሠረት ፡ መሆኑ ፡ ይታመናል ፤ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክም ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅ ፡ ናቸው ፡ የሚባሉት ፡ እነዚሁ ፡ ሊቃውንት ፡ መሆናቸው ፡ ይነገራል ። እነዚህ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ተብሎ ፡ ከሚጠራው ፡ ከብሉይ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ፡ መንፈስ ፡ ጋር ፡ ተቀላቅለው ፡ በአምስት ፡ ክፍል ፡ የተመደቡትን ፡ የሙሴን ፡ መጻሕፍት ፡ መንፈስ ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ በመከተል ፡ የተዘጋጁት ፡ የብይን ፡ ጽሑፎች ፡ አብዛኛውን ፡ የገዥስቲኒያኖስን ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ መሠረትም ፡ ተከትለው ፡ የተጻፉ ፡ በመሆናቸው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥት ፡ ሕግ ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ያቋቋሙ ፡ ናቸው ።

ይህም ፡ ጽሑፍ ፡ ለብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍርድና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ መተዳደሪያ ፡ መሪ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ኖሯል ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ሕግ ፡ የያዘው ፡ የሙሴን ፡ ሕግጋት ፡ ወይም ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ምንጭና ፡ የክርስቲያንነትን ፡ ጠባይ ፡ በመሆኑና ፡ ከሩቅ ፡ ዘመናትም ፡ ጀምሮ ፡ ከሮማኖ - ቢዛንቲን ፡ ባሕል ፡ ጋር ፡ የተዛመደና ፡ ከኤሮፓ ፡ አሕጉር ፡ የሕግ ፡ ባሕል ፡ ጋር ፡ የተቀራረበ ፡ ሆኖ ፡ መታየቱ ፡ ሊያስደንቀን ፡ አይገባም ።

ይህም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ በግዕዝ ፡ ማለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጥበባዊ ፡ ቋንቋ ፡ በሆነው ፡ ተተርጉሟል[6] ። እንደሚባለውም ፡ [ይህን ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ የፈጸመው ፡ ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የተባለው ፡ (፲፬፻፲፰-፲፬፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም) የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የነበረው ፡ ነው ። እርሱም ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድን ፡ ወዳጅ ፡ ስለነበረ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ አስተርጉሞ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ሲያደርግ ፡ የፍትሕ ፡ አፍቃሪነቱን ፡ የሚመሰክርለት ፡ የወለደው ፡ ልጁ ፡ ባሪያውን ፡ ቢገድል ፡ የገደለ ፡ ይሙት ፡ በሚለው ፡ በሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ተመርቶ ፡ በመስፍኑ ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ እንዲፈጸምበት ፡ እስከማድረግ ፡ ደርሷል ።

ይህም ፡ ንጉሥ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱን ፡ ሕግ ፡ ራሱ ፡ በጥልቅ ፡ አጥንቶ ፡ ያውቅ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ፤ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ መጽሐፉ ፡ የመንፈሳዊና ፡ የሥጋዊ ፡ አስተዳደር ፡ መምሪያ ፡ ዋነኛ ፡ ምንጭ ፡ ሆኖ ፡ በመኖሩ ፡ በመጽሐፉም ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ቃላት ፡ ሁሉ ፡ በፍጹም ፡ የማይደፈሩ ፡ የማይሻሩና ፡ የማይለወጡ ፡ ሆነው ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ሲከበሩ ፡ ኑረዋል ፤ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ የሆኑ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሊቃውንቶችም ፡ ሰፊ ፡ ማብራሪያ ፡ እየሰጡና ፡ እያስተማሩ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ በማስተላለፍ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ተከብሮ ፡ እንዲቆይ ፡ አድርገውታል ፤ በታሪክ ፡ ጥንታዊነትን ፡ የያዘ ፡ በመሆኑ ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ የሕጎች ፡ ምንጭ ፡ የሆነው ፡ ታላቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ለተመደበበት ፡ ጉዳይ ፡ "በቂነት ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ ቢገመትም" ፡ የእስክንድርያ ፡ ኮፕት ፡ ክርስቲያንነት ፡ የሥልጣኔ ፡ አርምጃ ፡ መስታዮት ፡ በመሆኑ ፡ "ታላቅ ፡ ክብር" ፡ ያስገኘለት ፡ ከመሆ

---

[6] ዜርሾስ ፡ የተባለው ፡ ደራሲ ፡ በጻፈው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጠቀስነው ፡ ድርሰቱ ፡ ላይ ፡ (በገጽ ፡ ፪፻፳፱) እንደገለጸው ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲፯ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ያስተረጎመችው ፡ የድረሰቶችና ፡ የመጻሕፍት ፡ ፍቅር ፡ ያደረባት ፡ የቀዳማዊ ፡ ኢያሱ ፡ እናት ፡ ነች ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ መኖሩን ፡ ገልጾልናል ፤ ይህም ፡ የኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ ሊቃውንቶች ፡ ድንጋጌ ፡ መጽሐፍ ፡ የመጀመሪያው ፡ ጽሑፍ ፡ ከዓለም ፡ ላይ ፡ ጠፍቶ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ በ፲፫ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ አቡነ ፡ ይስሐቅ ፡ እብን ፡ አልሐሰል ፡ በተባለ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ዐረብኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጉሞ ፡ ተገኘ ። በሲያንስ ፡ ክሪቲክ ፡ ላይ ፡ እንደሚነገረው ፡ የቁርሎሳዊው ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ራሱ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ኢትዮጵያውያን ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሳወጁት ፡ መሠረታዊ ፡ የጽሑፍ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ ሆኖ ፡ የረዳቸውና ፡ ለሕግ ፡ ጽሑፋቸው ፡ መሠረት ፡ መነሻ ፡ ያደረጉት ፡ ይህንኑ ፡ ወደ ፡ ዐረብኛ ፡ ተተርጉሞ ፡ ምንም ፡ ሳይጉድለው ፡ እንደነበረ ፡ የተገኘውን ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ነው ፡ የተባለውም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ የመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ። በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ከተተረጐሙት ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ትክክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ በቀር ፡ ዋናው ፡ የማይገኝ ፡ መሆኑ ፡ ይታመናል ። በዚህ ፡ አሁን ፡ በያዝነው ፡ ዘመን ፡ ኦፊሲዬል ፡ በሆነው ፡ በዐማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መጽሐፍ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል ።

ኑም ፡ ይልቅ ፡ "ለደራሲው" ፤ ለተመሠረተበት ፡ ክፍለ ፡ ዘመንና ፡ ለአፍሪካዊው ፡ ምሥራቅ ፡ ከፍተኛ ፡ እድገት ፡ መድኅን ፡ ሆኖታል ፤ አገልግሎቱ ፡ የተመደበለትንም ፡ ሕዝብ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያደረገው ፡ ወደ ፡ ክብር ፡ ደረጃ ፡ አድርሶታል ፤ (ምንም ፡ እንኳ ፡ ሊታለፍ ፡ የማይቻል ፡ ጉድለት ፡ መድረሱ ፡ ባይቀር) ፡ የኮፕት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የእምነት ፡ መንፈስ ፡ ጥንታዊ ፡ ምንጩን ፡ እንዳይለቅና ፡ መሠረቱን ፡ እንዳይረሳ ፡ የሚያደርገው ፡ ነዋሪ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖታል ። የግእዝኛ ፡ ትርጉሙ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መመሥረቻ ፡ አቅዋምና ፡ ራስ ፡ ሆኖ ፡ ፍጹምና ፡ የታመነ ፤ ሌላ ፡ አምሳያና ፡ ማወዳደሪያ ፡ ያልተገኘለት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ የጽሑፍ ፡ ሕጎች ፡ ምንጭ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ አድርጎታል ።

የሐበሻን ፡ ሕዝብ ፡ የመተባበርና ፡ የአንድነት ፡ መንፈስ ፡ ያጠነከረ ፡ በዚህ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ በሆነው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ከ፲፫ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እስካለንበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡[7] ከርሱ ፡ ተከታትለው ፡ ለታወጁት ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ በመሆን ፡ የሕዝቡን ፡ የዳኝነትና ፡ የትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ አፍቃሪነት ፡ እያጠነከረ ፡ የሄደው ፡ ይህ ፡ ታላቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ተያይዞ ፡ በመጣው ፡ በነገሥታቱ ፡ ገዥነት ፡ ሕዝቡ ፡ ካለው ፡ ጽኑዕ ፡ እምነት ፡ ጋር ፡ የንጉሦች ፡ የፍርድ ፡ መጽሐፍም ፡ ለእምነቱ ፡ መሠረት ፡ በመሆን ፡ በሲሚንቶ ፡ ላይ ፡ እንደተገነባ ፡ ነዋሪ ፡ ሕንፃ ፡ ሐውልት ፡ ሆኖ ፡ ዘወትር ፡ አደጋ ፡ ተለይቶት ፡ ለማያውቀው ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ የሕይወት ፡ መድኅን ፡ ሆኖታል ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ።

የዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍሉ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ማለት ፡ የሥጋዊን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ የሚመለከት ፡ ሲሆን ፡ አስቀድሞ ፡ የቤተ ፡ ሰብን ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ የማኅበራዊን ፡ የኑሮ ፡ አቅዋም ፡ (ከዚህም ፡ ውስጥ ፡ በስሕተት ፡ እየተተረጐመ ፡ ስለ ፡ ባሪያ ፡ ሽያጭ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ከንቱ ፡ ሐሜት ፡ ያደረሰውን ፡ የአገልጋዮችን ፡ አስተዳደር ፡ ሥርዓት ፡) ስለ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የውል ፡ ሥርዓቶች ፡ ስለ ፡ ማኅበሮች ፡ አቋቋምና ፡ ስለ ፡ ውርስ ፡ አወራረስ ፡ ስለ ፡ ሌላውም ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ መሳሰለ ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ብሔራዊ ፡ ሥርዓተ ፡ ሕግ ፡ የሚናገር ፡ ድንጋጌ ፡ ያለበት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀጥሎም ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ስለ ፡ ዳኞችም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ምስክሮች ፡ የእምነት ፡ ክደት ፡ ቃል ፡ አሰጣጥ ፡ (ምዕራፍ ፡ ፴፱ና ፡ ፵፫) ፡ ይናገራል ፤ በመጨረሻም ውም ፡ ስለ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ከምዕራፍ ፡ ፵፮ ፡ እስከ ፡ ፶) ፡ የሚናገር ፡ ሆኖ ፡ ምዕራፍ ፡ (፶፩) ፡ ስለ ፡ ነገሥታት ፡ የሚለው ፡ ክፍል ፡ ከሌላው ፡ ጉዳይ ፡ መካከል ፡ በይበልጥ ፡ የሚመለከተው ፡ እስረኞችን ፡ ስለሚገጥማቸው ፡ የፍርድ ፡ ዕድል ፡ ሸሽተው ፡ ያመለጡ ፡ ስደተኞችን ፡ ስለ ፡ መቀበል ፡ (ለማስጠጋት) ፡ በአገራቸው ፡ ላይ ፡ የከሐደ

---

[7] የአምብሯዚየን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ወመዘክር ፡ ዓቃቤ ፡ መጻሕፍት ፡ የሆነው ፡ የሞንሴኘር ፡ ጋልቢያቲ ፡ ሐሳብ ፡ ሮሲ ፡ ካኔቫሪ ፡ ለጻፈው ፡ ድርሰት ፡ በሰጠው ፡ መቅድሙ ፡ ላይ ፡ ይህንኑ ፡ የሚደግፍ ፡ ነው ። ስለ ሆነም ዝንጋስና ፡ ሞንሮዬ ፡ በጻፉት ፡ ታሪክ ፡ በገጽ ፡ ፺፰ ፡ እና ፡ ፖሌቲ ፡ ረግዋ ፡ የአበሾች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ሕግ ፡ ለሚለው ፡ መጽሐፍ ፡ መቅድም ፡ (በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፻፹፩ ፡ ገጽ ፡ በጻፈው ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ እሳብ ፡ የማይደግፍ ፡ መሆኑን ፡ ገልጾታል ። በራሳችን ፡ አስተያየት ፡ በወሰድነው ፡ ተቃራኒ ፡ ሁኔታ ፡ ግን ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ በኢትዮጵያ ፡ በቆየንበት ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮን ፡ አባሎች ፡ በመሆን ፡ አብረውን ፡ በመሥራት ፡ ከረዱን ፡ ከዛሬዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሊቃውንቶች ፡ ጋር ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ እሳብ ፡ ለእሳብ ፡ በመለዋወጥና ፡ ሰፊ ፡ ጥናት ፡ በማድረግ ፡ በግልጽ ፡ እንደተረዳነው ፡ ሁሉ ፡ ከላይ ፡ የተገለጸው ፡ ግምት ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑንና ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መጽሐፍም ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጽሳት ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ የኖረ ፡ የተከታዮቹ ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ምንጭና ፡ ግዙፍ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ የኖረ ፡ መሆኑን ፡ ልናረጋግጥ ፡ ችለናል ። ስለሆነም ፡ ከቀድሞው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ እማካይ ፡ ክፍል ፡ እጅግ ፡ የራቁ ፡ ሆነው ፡ ሙሉ ፡ መቆጣጠር ፡ ሊደረግላቸው ፡ አስቸጋሪ ፡ የነበሩ ፡ ክፍለ ፡ ሀገሮች ፡ ብቻ ፡ የተለየ ፡ ባሕልና ፡ ልማዳዊ ፡ ደንብ ፡ እየቀላቀሉ ፡ መሠረታዊውን ፡ ሕግ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ተቀብለው ፡ ያልሠሩበት ፡ ነገዶች ፡ ይገኙ ፡ እንደነበረ ፡ የታመነ ፡ ሲሆን ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ልዩነት ፡ ቢኖርም ፡ ቅሉ ፡ በግልጽ ፡ ግዙፍ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አፈጻጸምና ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ ቢባል ፡ ስሕተት ፡ አይሆንም ።

ትን ፡ ተግባር ፡ የፈጸሙ ፡ ሰዎች ፡ ስለሚቀጡበት ፡ ደንብ ፡ ነው ። ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ምዕራፍ ፡ (፵፩) ፡ እንስሳት ፡ ወይም ፡ አደገኛ ፡ ሕንፃዎች ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሀብታቸው ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለውን ፡ አደጋ ፡ ስለመካስ ፡ የጠፉ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለመመለስና ፡ ስለማጭበርበር ፡ ወንጀል ፡ የሚናገር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ሕጉ ፡ በ(፵፯) ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ በመናፍቃን ፡ ሃይማኖትን ፡ በሚያዋርዱና ፡ በሚያረክሱ ፡ ተሳዳቢዎች ፡ በጠንቋዮችና ፡ በጋኔን ፡ ጐታቾች ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ የማስካድ ፡ ሙከራ ፡ በሚፈጽሙ ፡ ጥፋተኞች ፡ በምትሐተኞች ፡ የአምልኮ ፡ ባዕድ ፡ እምነት ፡ በሚፈጽሙ ፡ ጣዖት ፡ አምላኪዎችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አምልኮትን ፡ በሚፈጽሙ ፡ ወንጀለኞች ፡ ላይ ፡ የሚወስነውን ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡ በምዕራፍ ፡ (፵፯) ያመለክታል ።

የሰው ፡ መግደልንና ፡ የአመንዝራነትን ፡ ወንጀል ፡ ቅጣት ፡ (ም ፡ ፵፰) ይወስናል ። ስርቆትንና ፡ ውንብድናን ፡ (ም ፡ ፵፱) ። በመጨረሻውም ፡ (ምዕራፍ ፡ ፶) ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስለሆኑ ፡ ስለሌሎች ፡ በደሎች ፡ የሚናገረው ፡ በመደዳው ፡ በተቀላቀለ ፡ ጠቅላላ ፡ አጻጻፍ ፡ ስለ ፡ ስካር ፡ ስለ ፡ አራጣ ፡ በንጉሡ ፡ ማኅተም ፡ ያላገባብ ፡ አጭበርብሮ ፡ በመጠቀም ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ ቅጣት ፡ ተናግሮ ፤ አመጸኛ ፡ የሆነ ፡ ልጅ ፡ የሚደርስበትን ፡ ቅጣት ፡ ንጹሑን ፡ ሰው ፡ በሐሰት ፡ ስለ ፡ መወንጀል ፡ በሐሰት ፡ ስለመመስከር ፡ በስሕተት ፡ ወይም ፡ አውቆ ፡ ቤትን ፡ በማቃጠል ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የቃጠሎ ፡ አደጋን ፡ በማድረስ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ የሚገባውን ፡ ቅጣት ፡ ይወስናል ። እንዲሁም ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ (ርስት) በኃይል ፡ ስለ ፡ መቀማትና ፡ እጅ ፡ ስለማድረግ ፡ የሕዝብ ፡ ስብሰባዎችን ፡ ስለማወክና ፡ ጉባኤዎችን ፡ ስለማደፍረስ ፡ በሚሠሩ ፡ ጥፋቶች ፡ ላይ ፡ የሚደርሰውን ፡ ቅጣት ፡ ያመለክታል ፤ በገዳማት ፡ ውስጥ ፡ ሸሽቶ ፡ የመማጠን ፡ መብት ፡ ያለመደፈርንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሌሎችንም ፡ በመዘርዘር ፡ ይወስናል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ እንግዲህ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ጥንታዊ ፡ አኗኗር ፡ በሕግ ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ ከአያሌ ፡ ክፍለ ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ በዘልማድም ፡ በሃይማኖት ፡ በባሕላዊ ፡ ሥርዓት ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ድርጅት ፡ በሕዝባዊ ፡ እምነት ፡ በሰዎችና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ይሠራ ፡ የነበረው ፡ ወንጀል ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ሐሳብ ፡ የመነጨውና ፡ በጠቅላላው ፡ ከክርስቲያናዊ ፡ እምነት ፡ ባሕርይ ፡ በመፈጠር ፡ የተገኘ ፡ ጥበብ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ስለ ፡ ንጉሦችና ፡ ስለ ፡ ሹማምንቶቻቸው ፡ አላፊነትና ፡ ተግባር ፡ ሲናገር ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ በመጥቀስ ፡ "...ያሉትም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፈራጆች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሾሙ ናቸው ፡ ስለዚህ ፡ ባለሥልጣንን ፡ የሚቃወም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥርዓት ፡ ይቃወማል ፤ የሚቃወሙትም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ ይቀበላሉ ። ገዥዎችና ፡ ፈራጆች ፡ ለክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ለሚያደርጉ ፡ የሚያስፈሩ ፡ አይደሉምና ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ ባለሥልጣንን ፡ (ፈራጅን) እንዳትፈራ ፡ ትወዳለህን? መልካምን ፡ አድርግ ። ...ለመልካም ፡ ነገር ፡ ላንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነውና ። በከንቱ ፡ ግን ፡ ሰይፍን ፡ አልታጠቀምና ፡ ክፉ ፡ ብታደርግ ፡ ፍራ ። ክፉ ፡ አድራጊውን ፡ የሚበቀል ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነውና ። ስለዚህ ፡ ፈራጅን ፡ መፍራት ፡ ያለብን ፡ ስለ ፡ ቍጣው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሕሊና ፡ ደግሞ ፡ መገዛት ፡ ግድ ፡ ነው ። ... እንዲሁም ፡ ንጉሥ ፡ እውነተኛና ፡ ትክክለኛ ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ፡ ለዚህም ፡ ተቀዳሚ ፡ ምሳሌ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቦቹ ፡ መካከል ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድን ፡ ማደል ፡ አለበት ፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ በሌሎችም ፡ እንዲሁ ፡ ለወለደው ፡ ልጁም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ለዘመዶቹ ፡ ወይም ፡ ለባለሙዋሉ ፡ ለግል ፡ ወዳጅም ፡ ለባዕድም ፡ ለእንግዳም ፡ ቢሆን ፡ አድላዊ ፡ እንዳይሆን ፡ ስለ ፡ ፈራጆች ፡ ተጽፏልና ፡ የተከበረ ፡ ንጉሥ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድን ፡ ይወድ ፡ ዘንድ ፡ አድላዊ ፡

ግን ፡ ክፉ ፡ ነገርንና ፡ አድልዎን ፡ ይከተላልና ፡ ለነፍሱ ፡ ጥፋት ። ጠቢቡ ፡ ሰሎሞንም፡ መሥዋዕት ፡ ከማቅረብ ፡ ፍርዱንም ፡ ከመሠዋት ፡ ይልቅ ፡ ሕግን ፡ አክብሮ ፡ መጠበቅና ፡ የተበዳይን ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ማቅለል ፡ ይሻላል ፡ ሲል ፡ ተናግሯልና ።" በጽሑፎች ፡ ላይ ፡ የሚገልጽ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ መንፈስ ፡ መንጭቶ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አጻጻፍ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የተገኘው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስም ፡ ለቅዱስ ፡ ሌዊ ፡ (ስን ፡ ሉዊ) ፡ እና ፡ ለቦሱዌ ፡ የእምነታቸው ፡ ጽኑ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ እንደኖረ ፡ የሚያስገምተን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ የተሠራ ፡ ሆኖ ፡ ሰማያዊ ፡ መለኮታዊ ፡ ሕግን ፡ ለማስከበር ፡ (የመንፈስ ፡ ወይም ፡ የውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ሕግ) ፡ ከሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ውጭአዊ ፡ ሆኖ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ሕግ ፡ ከሚባለው ፡ ጋር ፡ በመቀላቀል ፡ ተዋሕዶ ፡ ሳይለያይ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ በመጠራት ፡ የትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ምንጭ ፡ ከሆነ ፡ መለኮታዊ ፡ ሥልጣን ፡ የመነጨ ፡ መሆኑ ፡ ለመንፈሳችን ፡ ይሰማናል [8] ።

ይህም ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ ጥንታዊነቱን ፡ ሳይተው ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ኦሪታዊውን ፡ ሕግ ፡ ሳይለቁ ፡ በሚኖሩ ፡ በዘላኖችና ፡ በጠረኛ ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ የሚሠራበት ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ በንጉሥ ፡ በካህኑ ፡ በፈራጁ ፡ አግጣጫ ፡ የባሪያው ፡ ባለቤት ፡ (ጌታ) ወታደሩና ፡ ምርኮኛው ፡ አማኒውና ፡ መናፍቁ ፡ ይጠቀሳሉ ፤ ሴሰኛዋ ፡ ሴትና ፡ አንጥረኛው ፡ እንደ ፡ አቃጣሪና ፡ እንደ ፡ ምትሐተኛ ፡ ጠንቋይ ፡ ተቆጥረው ፡ ይዋረዳሉ ፤ ኮከብ ፡ ቆጣሪውና ፡ መንፈሳዊ ፡ የሆነው ፡ ቅዱስ ፡ ጠሩን ፡ የያዘው ፡ አዳኙና ፡ አራሹ ፡ ገበሬ ፡ ተቀላቅለው ፡ ይገኛሉ ። ስለሆነም ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ይሠራ ፡ የነበረበት ፡ የጊዜ ፡ ርቀት ፡ ሲታሰብ ፡ በዚህ ፡ ጥንታዊ ፡ በሆነው ፡ ዘመን ፡ እስከዚህ ፡ ደረጃ ፡ ደርሶ ፡ በተስተካከለና ፡ በተቃና ፡ ሁኔታ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ መቻሉ ፡ ሲገመት ፡ ደግሞ ፡ አድናቆትን ፡ ሳያተርፍልን ፡ አልቀረም ። እጅግ ፡ ጠባብና ፡ ርኅራኄ ፡ ያልነበረው ፡ ዓይን ፡ ለዓይን ፡ ጥርስ ፡ ለጥርስ ፡ ማለት ፡ ቋንቋ ፡ የመቀጣጠሪ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ቋንቋው ፡ ይቆረጥ ፡ ዓይን ፡ ያፈሰሰ ፡ ዓይኑ ፡ ይፍሰስ ፡ የሚባለው ፡ የቅጣት ፡ ደንብ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የቀረ ፡ መሆኑን ፡ ሳናስበው ፡ በግዙፉ ፡ ወንጀል ፡ መጠን ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነውን ፡ ቅጣት ፡ ይወስን ፡ የነበረው ፡ ደንብ ፡ መሻሻሉ ፡ የሕጉን ፡ መሻሻል ፡ ያስታውሰናል ።

---

[8] ኩበሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ፡ ተውጣጥተው ፡ የተጠቀሱትን ፡ በምዕራፍ ፡ ቁጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ቃላት ፡ ማስታወስ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ ስለታየን ፡ ሳናነሳቸው ፡ አናልፍም ። ከነዚህም ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ እንደሚገልጹት ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ የተፈጠረው ፡ ከነፍስና ፡ ከሥጋ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ሁለት ፡ ሕጎች ፡ ሊሰጡት ፡ ይገባል ፤ ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ሥጋዊ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የሚመራበትን ፡ ግዙፍ ፡ ነገሮችና ፡ ሀብቶች ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ሲያጠፉ ፡ አካላዊ ፡ የሆነ ፡ ግዙፍ ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰንበትን ፡ ደንብ ፡ መደንገግ ፤ ውስጣዊ ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ማለት ፡ «በነፍስ» ግዙፍ ፡ ባልሆነ ፡ በማይዳሰስ ፡ ውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ረገድ ፡ (የንጽሕና ፡ ሕግ) ሆኖ ፡ መንፈሳዊው ፡ ረቂቅ ፡ ነገር ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ደንብ ፡ የሚደነግግ ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ ቢሆኑ ፡ የማይነጣጠሉ ፡ ባንድነት ፡ የተዋሐዱ ፡ ናቸው፤ ምክንያቱም፡ የሁለተኛይቱ ፡ የመጀመሪያይቱን ፡ ለማደስ ፡ እንጂ ፡ ለማፍረስ ፡ አልመጣችምና ፡ (ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደተናገረው ፡ ሕግን ፡ ማለት ፡ ኦሪትን ፡ ለማደስ ፡ (ለማሟላት) እንጂ ፡ ለማፍረስ ፡ አልመጣሁም) ብሏልና ። መንፈሳዊ ፡ ፍርድና ፡ ቅጣት ፡ ከሥጋዊ ፡ ፍርድና ፡ ቅጣት ፡ ጋር ፡ ተባብሮ ፡ ሳይነጣጠል ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ በመኖር ፡ የሚሠራ ፡ መሆኑን ፡ መርሳት ፡ አይገባንም ፡ የምዕራፉ ፡ መጨረሻ ፡ ክፍል ፡ እነዚህ ፡ ቅጣቶችና ፡ የንሥሐ ፡ መግባት ፡ ግዴታዎች ፡ የትኞቹ ፡ እንደሆኑ ፡ ይገልጻል ። በ፫ ፡ አህጉር ፡ በመካከለኛው ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ይደረግ ፡ እንደነበረው ፡ ዐይነት ፡ የሕጉን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ። ሃይማኖታቸውን ፡ የካዱ ፡ መናፍቃን ፡ እምነት ፡ የሌላቸው ፡ በመንፈሳዊ ፡ ቅጣት ፡ ምክንያት ፡ ከማኅበረ ፡ ክርስቲያን ፡ የተወገዱ ፡ ለምሳሌ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዮች ፡ አመንዝራዎችና ፡ ጽንስን ፡ ያስወረዱ ፡ ሴቶች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመግባት ፡ የተከለከሉ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚሠሩት ፡ በሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ቅርጽ ፡ በክብ ፡ ሆነው ፡ ወይም ፡ በስምንት ፡ ማዕዘን ፡ በተከበበ ፡ አሠራር ፡ ስለሆነ ፡ በሦስት ፡ ክፍል ፡ ከተከፈለው ፡ አንዱ ፡ የቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ስፍራ ፡ እየተባለ ፡ በሚጠራው ፡ ውስጥ ፡ ታቦት ፡ ወይም ፡ የጽላተ ፡ ሙሴ ፡ ማኖሪያ ፡ ስለሆነ ፡ እነዚህ ፡ የተቀጡ ፡ ሰዎች ፡ የመንፈሳዊ ፡ ርክሰት ፡ ቅጣት ፡ ደርሶባቸዋልና ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ እንዳይደርሱ ፡ ይከለከላሉ ።

የሕጉ ፡ አመሠራረት ፡ ማለት ፡ የአሠራሩ ፡ ዘዴ ፡ የመነጨው ፡ በሚዳሰሰው ፡ (በኮንክሬት)
ፍች ፡ በመጀመር ፡ ሲሆን ፡ የመሻሻል ፡ እርምጃውን ፡ ያደረገው ፡ ቀስ ፡ በቀስና ፡ በጊዜ ፡
ብዛት ፡ ስለሆነ ፡ ወደማይዳሰሰው ፡ (አብስትሬ) መንፈስ ፡ ሲሸጋገር ፡ በዘመኑ ፡ ረጅም ፡
እርምጃ ፡ በየጊዜው ፡ ያጋጠመውንና ፡ የሚገጥመውንም ፡ አሻሽሎ ፡ በመግለጽና ፡ በመወ
ሰን ፡ በተለይም ፡ በአላፊነትና ፡ በአጥፊነት ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ የተወሳሰበ ፡ ግንኙነት ፡
ፍች ፡ በመስጠት ፡ የወንጀልን ፡ ግብረ ፡ አበርነትንና ፡ በወንጀል ፡ አድራጊው ፡ ላይ ፡ የሚ
ወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ከጥፋቱ ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሚሆንበትን ፡ ዘዴ ፡ በየዘመኑ ፡ አጥንቶ ፡
እንደነገሩ ፡ አመጣጥ ፡ ለማስተካከል ፡ መቻሉ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ነው ።
ለዛሬው ፡ ዘመን ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ እንኳ ፡ እጅግ ፡ አሳሳቢ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየውን ፡
የተደራረቡ ፡ ነገሮችን ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታና ፡ በጸብ ፡ የሚነሱ ፡ ሽብሮችን ፡ ጉዳይ ፡ ሕጉ ፡
እጅግ ፡ ረቂቅ ፡ በሆነ ፡ ስሜትና ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ባለው ፡ ዓይነት ፡ አስተካክሎና ፡
አጣርቶ ፡ በሕግ ፡ አዘገጃጀት ፡ ጥበባዊ ፡ ዘዴ ፡ ደንግጓቸው ፡ ይገኛል ። ጥፋት ፡ የግል ፡
መሆኑም ፡ ጭምር ፡ በሚገባ ፡ ተገልጿል ። ልጆቻቸው ፡ በፈጸሙት ፡ ወንጀል ፡ አባቶች ፡
አላፊ ፡ ሆነው ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸምባቸው ፡ እንዲሁም ፡ ልጆች ፡ በአባቶቻ
ቸው ፡ ምትክ ፡ እንዳይቀጡ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተወስኗል ። ቅጣትን ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ስለ
መፈጸም ፡ የሚለውም ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ ተገልጾ ፡ ይገኝበታል ፤ በሕጉ ፡
ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በተነገረ ፡ ወንጀል ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡
የሆነ ፡ ቅጣት ፡ አትወስኑ ፤ ወንጀልን ፡ በአድራጎት ፡ በፈጸመ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚወሰነው ፡
ቅጣት ፡ በንግግር ፡ ወይም ፡ በሐሳብ ፡ በፈጸመው ፡ ጥፋተኛ ፡ ላይ ፡ ከሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡
ጋር ፡ እኩል ፡ መሆን ፡ አይገባውም ። ላንዳንዶቹ ፡ አጥፊዎች ፡ ተግሣጽ ፡ ብቻ ፡ የሚበቃ
ቸው ፡ ሲሆን ፡ ለሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በፈጸሙት ፡ ጥፋት ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ ከቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ እንዲወገዱ ፡ የማባረር ፡ ቅጣት ፡ ይወሰንባቸው ። የሙሴ ፡ ሕግ ፡ አጥፊ ፡ በሆ
ኑት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ቅጣት ፡ እንዲወሰን ፡ አያዝዝምና ፡ የሚሉ ፡ ቃላት ፡ ይነበ
ባሉ ፤ እንዲሁም ፡ አውቆ ፡ ባጠፋ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፡ ቅጣትና ፡ ሳያውቅ ፡
ተሳስቶ ፡ ባጠፋው ፡ ላይ ፡ ከሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ።
ላንዳንዶቹ ፡ ወንጀለኞች ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ሲገባቸው ፡ ለሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ የግርፋት ፡
ቅጣት ፡ ይበቃቸዋል ፡ እንዲሁም ፡ ላንዳንዶቹ ፡ ከሀብታቸው ፡ ላይ ፡ መቀጮ ፡ እንዲከ
ፍሉ ፡ ሲወሰን ፡ ሌሎቹን ፡ ደግሞ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ለማድረስ ፡ በሞከሩት ፡ ወይም ፡ በመሰ
ሎቻቸው ፡ ላይ ፡ ካደረሱት ፡ ጉዳት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ዓይንን ፡ በዓይን ፡ እጅን ፡
በእጅ ፡ የሚለው ፡ ቅጣት ፡ ይወስንባቸው ። ስለዚህ ፡ በያንዳንዱ ፡ አጥፊ ፡ ላይ ፡ ሊወሰን ፡
የሚገባውን ፡ የቅጣት ፡ መጠን ፡ ለይታችሁ ፡ እወቁ ፤ ይህም ፡ ሲሆን ፡ ፈራጆች ፡ በሆና
ችሁት ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ አድላዊነት ፡ አይኖርምና ፡ እንደፈረድክ ፡ ይፈረድብሃል ፡
ተብሏልና ።

የታሪክን ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ ባለማወቅና ፡ የጊዜውን ፡ ረጅም ፡ ርቀት ፡ ባለማስተ
ዋል ፡ የቅጣቱ ፡ ከባድነትም ፡ ሆነ ፡ የሕጉ ፡ አመሠራረት ፡ መንፈስ ፡ ከኤሮፓዊያን ፡
የሕግ ፡ መንፈስ ፡ የራቀና ፡ የማይመሳሰል ፡ ነው ፡ ወይም ፡ የጥንታዊው ፡ ቅጣት ፡ አወ
ሳሰን ፡ ዛሬ ፡ ከሚሠራበት ፡ ከዘመናዊው ፡ የሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ የተራራቀ ፡
ነው ፡ ብሎ ፡ መገመት ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ መደነቅ ፡ ወይም ፡ በሕሊና ፡ መውቀስ ፡ እንደ ፡
ቅሌት ፡ የሚቆጠር ፡ ይሆናል ።

የሕጉ ፡ አሳብ ፡ የተመሠረተው ፡ ጥንታዊ ፡ ለሆነው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደህንነቱን ፡
ጠብቆ ፡ ሊኖር ፡ ስለሚችልበት ፡ ዘዴ ፡ አርቆ ፡ በማሰብ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ለነበረው ፡
ለጥንታዊው ፡ አኗኗር ፡ ተስማሚ ፡ ሊሆን ፡ በሚችልበት ፡ መንገድና ፡ ጥፋተኛው ፡ ለፈ
ጸመው ፡ ወንጀል ፡ ንሥሐ ፡ ገብቶ ፡ ይቅርታን ፡ ለማግኘት ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።
ሕጎቹም ፡ ከሕዝቡ ፡ እምነት ፤ ከባሕሉና ፡ ከፍላጎቱ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ግንኙነት ፡ ባለው ፡

ዓይነት ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ። ቅጣቶቹም ፡ ደግሞ ፡ ተብቃይነት ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ ከጥፋት ፡ የሚያርቅ ፡ ንጽሕናን ፡ የሚያስገኙ ፡ ፍርሐትን ፡ በማሳደርም ፡ ጽኑ ፡ ምሳሌነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ መደረጉ ፡ ለዘመኑ ፡ ተስማሚና ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ እንደነበረ ፡ አያጠራጥርም ፤ ተገቢም ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ዓላማቸውም ፡ ክፉዎችን ፡ መቅጣት ፡ ሰላማዊዎችና ፡ ደሀናዎች ፡ ለኑሮአቸው ፡ ዋስትና ፡ እንዲያገኙ ፡ ማረጋገጫ ፡ መስጠትና ፡ ወንጀልም ፡ ተመላልሶ ፡ እንዳይፈጸም ፡ የመከላከል ፡ ግብ ፡ እንደነበረ ፡ በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ ባጠፋው ፡ ጥፋት ፡ ዓይነት ፡ እንዲቀጣ ፡ መደረጉ ፡ የሚወሰኑትም ፡ ቅጣቶች ፡ የተወሰኑበት ፡ ምክንያት ፡ በተቀጭም ፡ በተመልካችም ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ ሊያስገኙ ፡ የሚገባቸውን ፡ ውጤት ፡ በስሜቱ ፡ ላይ ፡ እንዲያሳድሩበት ፡ አጥፊው ፡ ከፈጸመው ፡ ጥፋት ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ ተመሳሳይነት ፡ ያለው ፡ ቅጣት ፡ ሲደርስበት ፡ በጥፋቱ ፡ ያደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ስሜትን ፡ በተጐጂው ፡ ላይ ፡ እንዳደረሰ ፡ እንዲገነዘበው ፡ ለምሳሌ ፡ ሰው ፡ የገደለን ፡ በሞት ፡ የቃጠሎ ፡ አደጋ ፡ ያደረሰን ፡ በእሳት ፡ አስጸያፊ ፡ ነገርን ፡ በመናገር ፡ ለበደለ ፡ ምላሱን ፡ በመቍረጥ ፡ በንጉሥ ፡ ማኅተም ፡ ያላገባብ ፡ የተጠቀመ ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ ለውጦ ፡ የሠራውን ፡ በእጅ ፡ መቍረጥ ፡ ቅጣት ፡ ወራዳ ፡ የሆነ ፡ ነውር ፡ ያለበት ፡ ተግባር ፡ የፈጸመውን ፡ በጨፈቃ ፡ ወይም ፡ በጅራፍ ፡ ግርፋት ፡ አዋራጅ ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ ጥቂት ፡ ቆይቶ ፡ ጊዜው ፡ በመሻሻሉ ፡ ለምሳሌ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ማብራሪያ ፡ እንደሚገልጸው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ጠመንጃን ፡ ለጠላት ፡ አሳልፎ ፡ የሸጠ ፡ በጠመንጃ ፡ የመደብደብን ፡ ቅጣት ፡ የሚወስን ፡ መሆኑ ፡ ሊያስደንቀን ፡ አይገባም ። ለመጨረሻውም ፡ አስተያየታችን ፡ የሐሳባችን ፡ ድጋፍ ፡ የሚሆነን ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በደልም ፡ ሆነ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ በደሉም ፡ ጉዳቱም ፡ የግሉ ፡ እንደሆነ ፡ ያህል ፡ በሚቆጠርበት ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበብ ፡ ታስቦ ፡ ያልተፈጸመ ፡ ድንገተኛ ፡ የሰው ፡ መግደል ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የሟች ፡ ዘመዶች ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አማላጅነት ፡ ለገዳይ ፡ ይቅርታ ፡ ካደረጉ ፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ ከፍሎ ፡ እርቅ ፡ ማድረግን ፡ ሕጉ ፡ መፍቀዱም ፡ እንደዚሁ ፡ ሊያስደንቀን ፡ የሚገባ ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ። አጥፊዎች ፡ ማቅ ፡ (ጆንያ) ለብሰው ፡ በሰውነታቸው ፡ አመድ ፡ ነስንሰው ፡ እኔን ፡ ያየህ ፡ ተቀጣ ፡ እያሉ ፡ ምሕረትንና ፡ ይቅርታን ፡ ለመጠየቅ ፡ በየአደባባዩ ፡ ሲዘዋወሩ ፡ በዘመናችን ፡ አላየንምን ?

እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ የሕግን ፡ ታሪክ ፡ መሠረት ፡ የማያውቁ ፡ ጥራዝ ፡ ነጠቅ ፡ የሆኑ ፡ ተላላፊ ፡ አገር ፡ ጐብኚዎች ፡ እንደሚናገሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የጭካኔን ፡ ወይም ፡ የአረመኔነትን ፡ ጠባይ ፡ የያዘ ፡ ነው ፡ ያሰኛቸው ፡ ጥንታዊ ፡ የሆነውን ፡ የዚሁኑ ፡ መንፈስ ፡ (በተለይም ፡ የሥቅላትን ፡ የእጅ ፡ መቍረጥንና ፡ የግርፋትን ፡ ቅጣት) ፡ ይዞ ፡ የቆየ ፡ መሆኑን ፡ በማየታቸው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ለምሕረትና ፡ ለይቅርታ ፡ ስፊ ፡ የሆነ ፡ ሽሽቶ ፡ የመጠጋትን ፡ የመማጠንን ፡ ልማድ ፡ እንደተቀደሰ ፡ መብት ፡ አድርጎ ፡ የሚጠብቅ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ቅጣትና ፡ በጸጸት ፡ ወይም ፡ የጥፋቱን ፡ ዋጋ ፡ በመክፈል ፡ ማለት ፡ የደም ፡ ጉማ ፡ ከፍሎ ፡ ምሕረት ፡ በማግኘት ፡ ረገድ ፡ ከሕጎች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ባለመረዳታቸው ፡ ነው ፡ ያሰኛል ። ይልቁንም ፡ የብርሃን ፡ ዘመን ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ ባ፲፰ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ [9] መጨረሻ ፡ ግድም ፡ ከፍ ፡ ወዳለው ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ደርሰናል ፡ በሚሉት ፡ በብዙዎቹ ፡ የኤውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ይፈጸም ፡ የነበረውን ፡ ረቂቅ ፡ በሆነ ፡ ጥበባዊ ፡ ዘዴ ፡ ተደራጅቶ ፡ ሕጋዊ ፡ ማሠቃያ ፡

---

[9] በ፲፭፻፲፪ ፡ ከፖርቱጋል ፡ አምባሳደር ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተልኮ ፡ የነበረው ፡ የአልቫሬዝ ፡ ምስክርነት ፡ እንደገለጸልን ፡ በሌላውም ፡ አገር ፡ ይደረግ ፡ እንደነበረው ፡ ሁሉ ፡ «የቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም» እጅግ ፡ ጠንካራና ፡ ጨካኝ ፡ ችኩልም ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ነግሮናል ፡ ስለሆነም ፡ ግን ፡ ጥንታዊያኖቹ ፡ ደራሲዎቻችን ፡ እነ ፡ ጆንስና ፡ ሞንሮዬ ፡ ሂስቶዋር ፡ ዳቢሲኒ ፡ የበሐሻ ፡ ታሪክ ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ከገጽ ፡ ፶፮ ፡ እስከ ፡ ፷፬ ፡ በጻፉት ፡ ላይ ፡ እንደገለጹት ፡ ጨካኝነቱ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ የተረኩትን ፡ ያስተባብሉዋል ።

በሚባለው ፡ ደንብ ፡ በሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ ላይ ፡ ይደርስ ፡ የነበረውን ፡ አሰቃቂ ፡ ሥቃይ ፡
አረማዊ ፡ ጨካኝ ፡ የሚል ፡ ስም ፡ የተሰጠው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ተገል
ግሎበት ፡ የማያውቅ ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

በዚች ፡ በሕግና ፡ ክርስቲያን ፡ በሆኑ ፡ ነገሥታት ፡ ስትተዳደር ፡ በኖረች ፡ አገር ፡
በፍርድ ፡ ፊት ፡ ለቀረበው ፡ ወንጀለኛ ፡ ይሰጠው ፡ የነበረው ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ሊዘነጋ ፡
የሚገባው ፡ አይደለም ፤ ለዚሁም ፡ ማስረጃ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በማንኛውም ፡ ወንጀለኛ ፡
የሞት ፡ ቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ንጉሡ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ እራሱም ፡
እንኳ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ትሞታለህ ፡ ብሎ ፡ መፍረድ ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ ይጥለኛል ፤ በስሕ
ተትም ፡ በሰው ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ብፈርድ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ይፈረድብኛል ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በአምሳሉ ፡ ፈጥሮ ፡ በእስትንፋሱ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሰጠውን ፡ ነፍስ ፡ መው
ሰድ ፡ ለፈጣሪ ፡ እንጂ ፡ ለፍጡር ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ አይደለምና ፡ ለሕሊናዬ ፡
ወቀሳ ፡ እንዳላተርፍ ፡ እኔ ፡ ሰውን ፡ ትሞታለህ ፡ ብዬ ፡ እንዳልፈርድበት ፡ ሕግ ፡ ይፈርድ
በት ፡ ዘንድ ፡ የሕጉ ፡ መጽሐፍ ፡ ይነበብ ፡ እያለ ፡ በችሎቱ ፡ አደባባይ ፡ የፍትሐ ፡ ነገ
ሥቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ካልተነበበ ፡ ይህን ፡ የመጨረሻ ፡ ቅጣት ፡ አይወስንም ። ይህንንም ፡
የሚያደርገው ፡ ሕግ ፡ የተሰጠው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ በማመን ፡ የመነጨውም ፡
ከአበው ፡ ሊቃውንት ፡ በመሆኑ ፡ የመጨረሻ ፡ ፈራጅም ፡ እምላክ ፡ እንደመሆኑ ፡ የመጨ
ረሻውም ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠው ፡ ከእርሱ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ በንጹሕ ፡ ሕሊናው ፡ ሙሉ ፡
እምነትን ፡ አሳድሮ ፡ ነው [10] ፤ ከጥንት ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣው ፡ ልማድ ፡ ተወራርሶ ፡ እስ
ከኛ ፡ ዘመን ፡ ስለደረሰ ፡ ዛሬም ፡ ቢሆን ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ ቅጣት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡
ራሳቸው ፡ ካላጸኑት ፡ የማይፈጸም ፡ ሆኖ ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ጠባይ ፡ የያዙት ፡ የማናቸ
ውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲቀርብላቸው ፡ ግዴታ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡
ሕግ ፡ አሁንም ፡ ይሠራበታል ።

ስለዚህ ፡ እውነቱን ፡ ለመግለጽ ፡ ከተፈለገ ፡ የንጉሦች ፡ ሕግ ፡ የተባለው ፡ መጽሐፍ፡
የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ክፍል ፡ አፈጻጸም ፡ የሚከተለው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የክርስቲ
ያንን ፡ ሥርዓተ ፡ ሕግ ፡ ብርሃን ፡ በመሆኑ ፡ ጥፋት ፡ የግል ፡ ነው ፡ የሚቀጣውም ፡ አጥ
ፊው ፡ ራሱ ፡ ነው ፡ ጥፋቱም ፡ ባደረሰው ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ መካስ ፡ ይገባዋል ፡ የሚለ
ውን ፡ እምነት ፡ ስለሆነ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ የጀመረበትን ፡ የጊዜ ፡ ርቀት ፡ ስንገም
ተው ፡ ለዚያ ፡ ዘመን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ እርቀ ፡ የማስተዋል ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡
እንደ ፡ ከፍተኛ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሚቆጠር ፡ አድናቆትን ፡ ልንሰጠው ፡ ይገባናል ። ስለሆ
ነም ፡ የጥንታዊውን ፡ አኗኗር ፡ በመከተል ፡ በዘመኑ ፡ ይወሰን ፡ የነበረውም ፡ ቅጣት ፡
በዚሁ ፡ መጠን ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ በመሆኑ ፡ ለዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተስማሚ ፡ እንደ ፡
ነበረ ፡ ሳንዘነጋ ፡ የወንጀል ፡ ፖሊቲካ ፡ ተከሎ ፡ ይጠራ ፡ ከነበረውም ፡ መሠረታዊ ፡
አሳብ ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ ተመሳሳይነት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ነበረም ፡ እናስታውሳለን ፡ ከዚ
ህም ፡ በቀር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሕጉ ፡ መሠረታውያን ፡ አሳቦች ፡ የአዲሱ ፡ ዘመን ፡
መንፈስ ፡ እንደሚገምተው ፡ በዘመኑ ፡ ርዝመት ፡ መጠን ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ ያደረገው ፡
የመሻሻል ፡ እርምጃ ፡ ሳያቋርጥ ፡ የተወሰነ ፡ ግምት ፡ ሊሰጠው ፡ በማይቻል ፡ ሁኔታ ፡
ተራቅቆ ፡ የሚገኝ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ፖሊቲካን ፡ ይዞ ፡ እናገኘዋለን ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡

---

10 የኢትዮጵያ ፡ ፕሮቶኮል ፡ እንደሚያስረዳን ፡ በዳኝነት ፡ ተቀምጦ ፡ ተከራካሪዎቹን ፡ ወገኖች ፡ በማጓ
ጓት ፡ የፍርድን ፡ ሥራ ፡ የሚመራውና ፡ ክርክሮችንም ፡ በመወሰን ፡ ብይን ፡ የሚሰጠው ፡ ንጉሡ ፡ ራሱ ፡ ሳይሆን ፡
ከፍ ፡ ላሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የፕሬዚዳንትነት ፡ ተመሳሳይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ እፈ ፡ ንጉሥ ፡ (የንጉሥ ፡ አፍ)
ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ፈራጅ ፡ (ዳኛ) ነው ።

ከተፈጥሮ ፡ በተሠራ ፡ አምባ ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ ተከባ ፡ በኖረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡[11] ግዛት ፡ የምዕራባዊያን ፡ የሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ መግባት ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፡ ጥንታዊው ፡ የአካል ፡ ቅጣት ፡ ፍርድ ፡ እጅግ ፡ እየተቀነሰ ፡ መሄዱንና ፡ ባ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታወጀው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግም ፡ ከአዲሱ ፡ የሥልጣኔ ፡ አስተዳደር ፡ ጋር ፡ በማይጋጭ ፡ ሁኔታ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ቅጣት ፡ ከመወሰን ፡ እጅግ ፡ የተቆጠበ ፡ ለመሆኑ ፡ ተጨባጭ ፡ ማስረጃ ፡ እናገኛለን ።

## ፩ ፤ የመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (፲፱፻፳፫)

የመጀመሪያውን ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ ለመመሥረት ፡ የተደረገው ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ ያረፈው ፡ አስቀድሞ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫን ፡ ሕግ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ይኸም ፡ ተግባር ፡ ፍጹም ፡ ተገቢነት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ መገመት ፡ ይገባዋል ፡ ብለን ፡ እናምናለን ፤ ምክንያቱም ፡ ለአዲሱ ፡ ዘመን ፡ የወንጀል ፡ ሕግ ፡ ፖሊቲካ ፡ ተስማሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ ብቻ ፡ የሚታሰብበት ፡ ሳይሆን ፡ ከጥንታዊ ፡ ልማድ ፡ ለየት ፡ ብሎ ፡ በተቀዳሚነት ፡ መሻሻል ፡ የሚገባው ፡ መሆኑንም ፡ ጭምር ፡ በመገመትና ፡ ለሕዝቡ ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ሊሰጠው ፡ ስለሚገባው ፡ ስለ ፡ መብቱ ፡ አጠባበቅ ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ እንዲኖረው ፡ በዘመናዊ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበብ ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ መሠረታዊነት ፡ በሚፈቅደው ፡ ሁኔታ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ለእንቴርናሲዮናል ፡ ግንኙነትና ፡ ለዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ አሳብ ፡ ተቀባይነት ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ በሯን ፡ ከፍታ ፡ ከዚሁ ፡ ሐሳብ ፡ ጋር ፡ ለመዋሐድ ፡ ቆርጣ ፡ ለተነሣችበት ፡ ዓላማ ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆን ፡ ሕግ ፡ ማዘጋጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ መገኘቱ ፡ ስለሚታመንበት ፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ የታወጀው ፡ አሁን ፡ ያሉት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡[12] የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ በተቀዳጁበት ፡ ዕለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ጽሑፍ ፡ የኛን ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ሥርዓት ፡ በመከተል ፡ የተዘጋጀ ፡ ሆኖ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጣቸው ፡ በ፳፱ ፡ አንቀጾች ፡ የተከፋፈሉ ፡ ደንቦች ፡ ይገኙበታል ፤ እነዚህም ፡ ሕጉን ፡ ለሕዝባቸው ፡ በሰጡት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሐሳብ ፡ የሕጉ ፡ መኖር ፡ ምክንያትና ፡ መንፈሱ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ የሚደርስበትን ፡ ወሰንና ፡ ከሕጉ ፡ የሚጠበቀው ፡ ውጤት ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ እንደሚያስገኝ ፡ በመግለጽ ፡ የሚያስረዱ ፡ ቃላት ፡ ሠፍረውባቸዋል ። የጽሑፉም ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ቅጣቶችና ፡ ስለ ፡ ተቀጭነት ፡ የሚመለከተውን ፡ ጠቅላላውን ፡ መሠረታዊ ፡ ደንብ ፡ ይገልጻል ፤ ፩ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ልዩ ፡ ክፍሉ ፡ ደግሞ ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ በሰዎችና ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ ትርጓሜና ፡ ስለሚወሰነውም ፡ የቅጣት ፡ ልክ ፡ እንዲሁም ፡

---

[11] የፈረንሳይ ፡ ሌጋሲዮን ፡ ፕንሲዮ ፡ በ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በአፊሲዬል ፡ የሰጠውን ፡ ራፖር ፡ ፒየር ፡ አሊፕ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በሰሎሞንና ፡ በንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ዘውድ ፡ ስር ፡ ሆኖ ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ድርጅት ፡ ዘንድ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፳፩ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) በጻፈው ፡ ድርሰቱ ፡ ውስጥ ፡ አብራርቶ ፡ የገለጸውን ፡ ጥርጣሬ ፡ የሌለበትን ፡ የማይታበል ፡ ምስክርነት ፡ ተመልከት ።

[12] የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ በ፲፰፻፹፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከኢጣልያን ፡ ጋር ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ የዐድዋ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ የሆኑት ፡ የሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ ፡ የነበሩት ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ልጅ ፡ የማህለ ፡ ሥላሴ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ፡ ትውልዳቸውም ፡ በቀጥታ ፡ መስመር ፡ ከንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ዘር ፡ የመጣ ፡ ነው ። እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባሕል ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነትን ፡ ዘውድ ፡ በተቀዳጁ ፡ ጊዜ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተባለ ፤ ይህም ፡ የሥላሴዎች ፡ ኃይል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለ ፡ ትንንሽ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ቅጣት ፡[13] አብራርቶ ፡ ያመለክታል ።

የሥልጣኔ ፡ እርምጃና ፡ የትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ወዳጅነትን ፡ ሐሳብ ፡ መግለጫ ፡ የሆነው ፡ የመጽሐፉ ፡ መቅድም ፡ (በቍጥር ፡ ፩-፲፭ና ፡ ፲፮) ላይ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግን ፡ የሚሰጥ ፡ ሕግ ፡ አውጪ ፡ ጥንታዊውን ፡ ሕግ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ማሻሻል ፡ እንዳለበት ፡ ይህንንም ፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ የጥንታዊውን ፡ አሳብ ፡ ሳይለቅ ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ በሚስማማ ፡ ሁኔታ ፡ መዘጋጀት ፡ እንደሚኖርበት ፡ (በ፫ኛው ፡ ቍጥሩ ፡ ላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ደግሞ) ፡ ለሕጉ ፡ ማዘጋጀት ፡ ምሳሌና ፡ መሠረት ፡ እንዲሆኑ ፡ መምሪያ ፡ የተደረጉት ፡ የኤውሮፓ ፡ ሕጎች ፡[14] ለሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆን ፡ ሕግ ፡ ሲወጣ ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ በትክክለኛ ፡ ፈራጅነት ፡ መንፈስና ፡ ጥፋተኛው ፡ እንዲታረም ፡ ወደ ፡ ማድረግ ፡ ዝንባሌ ፡ ማድላት ፡ እንዳለበት ፡ የሚያስረዳን ፡ መሆኑን ፡ ስንመለከት ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደተናገርነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ጥንታዊ ፡ ባሕል ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ በሚሰጠው ፡ ፍትሐዊ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ ከታላቋ ፡ የክርስቲያናዊ ፡ እምነት ፡ ጋር ፡ የተሳሰረ ፡ ሆኖ ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡

[13] የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ የታወጀው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ኦፊሲዬል ፡ ቋንቋ ፡ በሆነው ፡ በአማርኛ ፡ ነው ። ይህም ፡ በእንግሊዝኛና ፡ በኢጣልያንኛ ፡ ቋንቋዎች ፡ ተተርጕሟል ። የእንግሊዝኛው ፡ ትርጕሙ ፡ አልታተመም ። በኢጣልያንኛ ፡ ቋንቋ ፡ የጸፈው ፡ ኢድዋርዶ ፡ ፖሌቲ ፡ የተባለው ፡ ጠበቃ ፡ ነው ፤ ያሳተመውም ፡ ሚላን ፡ በሚገኘው ፡ በሆኢፕሊ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኢል ፡ ኮዲቼ ፡ ፔናሌ ፡ አቢሲና ፡ ኮን ፡ ሌ ፡ ሬላቲቪ ፡ ፎርሚ ፡ ኮንስቲቱቢዮናሬ ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ሆኖ ፡ በግናቸውም ፡ ነጥቡ ፡ የተሟላ ፡ አርግጠኛነት ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ እንኳ ፡ የሕጉን ፡ መንፈስ ፡ ለማወቅ ፡ ለሚፈልጉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አንባቢዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመረጃ ፡ ምንጭ ፡ ለማስገኘት ፡ የሚችል ፡ ድርሰት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የአዲሱን ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ባዘጋጀንበት ፡ ጊዜም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ አግኝተንበታል ። የዛሬይቱን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ ጠቅላላ ፡ አመራር ፡ ስለሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግና ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ በሆኑት ፡ በሚስተር ፡ ናታን ፡ ማሬይን ፡ የተደረሰ ፡ ዘ ፡ ጁዲሺያል ፡ ሲስቴም ፡ ኧንድ ፡ ዚ ፡ ሎውስ ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሮተርዳም ፡ (ውስትሐም) ማተሚያ ፡ ቤት ፡ የታተመ ፡ ጽሑፍ ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድን ፡ የሚመለከቱ ፡ ጽሑፎች ፡ ጥርቅም ፡ እንጂ ፡ የሕግ ፡ ማብራሪያ ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ ጽሑፍ ፡ አይደለም ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ የነበረው ፡ ሚስተር ፡ ገ ፡ ገ ፡ አቤር ሶን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለሚኖሩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ የፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዠኔቭ ፡ ባሳተመው ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ ድርሰቱ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ መግለጫዎች ፡ ሰጥቷል ፤ ይህም ፡ መግለጫ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ የተሰጠ ፡ ተጨማሪ ፡ ማብራሪያ ፡ ቢሆንም ፡ በብዙ ፡ ነጥቡ ፡ ላይ ፡ ተቀባይነትን ፡ ለማግኘት ፡ የሚችል ፡ ነው ።

[14] ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጠቀስናቸው ፡ ድርሰቶች ፡ ላይ ፡ አቤርሶንና ፡ ማሬይን ፡ እንደገለጹት ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታወጀውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ የሠራው ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ አንዳንድ ፡ ማሻሻልና ፡ መጨመር ፡ ከማድረጉ ፡ በቀር ፡ ሕጉን ፡ የቀዳው ፡ ከኢንዶቺን ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ይህም ፡ መግለጫቸው ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በእጥፍ ፡ የወጣው ፡ ሕግና ፡ በመቅድሙ ፡ እንደተገለጸው ፡ አሳባቸውን ፡ የሚያስተባብል ፡ ሆኖ ፡ የተገመተበት ፡ ምክንያት ፡ የሕጉን ፡ መንፈስ ፡ በጥብቅ ፡ መርምሮ ፡ የተረዳ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ መግለጫውን ፡ እንደ ፡ እውነት ፡ ሊቀበለው ፡ አይችልም ፡ የሚያሰኝ ፡ እምነት ፡ ስለሚያስከትል ፡ ነው ። ይህን ፡ ስሕተት ፡ ያስከተለውም ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታወጀው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ የረቂቁን ፡ ሥራ ፡ ለማዘጋጀት ፡ እንዲያግዝ ፡ የተጠራው ፡ አንድ ፡ ሺቡቲ ፡ ይኖር ፡ የነበረና ፡ ለብዙ ፡ ዘመንም ፡ በፈረንሳዊ ፡ ኢንዶቺን ፡ የኖረ ፡ ጠበቃ ፡ ስለነበረ ፡ ረቂቁን ፡ በሠራበት ፡ ጊዜ ፡ የመነሻ ፡ ነጥብ ፡ አድርጎ ፡ የተከተለው ፡ የኢንዶቺንን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ ስላሳደረ ፡ ይመስለናል ። የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮንም ፡ በሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚሰጠው ፡ አሳብ ፡ እጅግ ፡ የተራራቀ ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የጥንታዊው ፡ ሕግ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የተከተለው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የገዶማናትን ፡ አስተዳደር ፡ ሲሆን ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ ዘመናዊ ፡ አስተዳደርና ፡ የሕግ ፡ አመራርን ፡ ስለሆነ ፡ ሕጉ ፡ የመነጨው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ባሕል ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ መሆኑን ፡ በቅርብ ፡ የሚመረምር ፡ ሁሉ ፡ በግልጽ ፡ ሊረዳው ፡ እንደሚችል ፡ የታመነ ፡ ነው ።

መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ እንደ ፡ ድንኳተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ይሆንብናል ፡ ብለን ፡ ልንገምት ፡ አንችልም ። ኤውሮፓውያን ፡ ለሕጋቸው ፡ መሠረት ፡ የሕብረት ፡ ምንጭ ፡ አድርገው ፡ እንደተጠቀሙበት ፡ እንደሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ለፍርዷና ፡ ለሕጉዋ ፡ ድርጅት ፡ መሠረታዊ ፡ አድርጋ ፡ የተጠቀመችበት ፡ የእስክንድርያውን ፡ ምንጭ ፡ በመ ሆኑ ፡ ተመሳሳይነቱ ፡ ያለመራራቁን ፡ እንገነዘባለን ። በብዙዎቹ ፡ ነጥቦች ፡ ላይ ፡ የእኛ ዎቹ ፡ ጥንታዊና ፡ ቋሚ ፡ (ክላሲክ) ሕጎች ፡ አሠራር ፡ የሮማኖ-ኦክሲዴንታልን (የሮማ ውያንንና ፡ የምዕራባውያንን) ፡ መንፈስ ፡ በመከተል ፡ የተደራጀ ፡ እንደመሆኑ ፡ የኢትዮ ጵያም ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የተከተለው ፡ ምሥራቃዊውን ፡ ወይም ፡ እስክንድራዊውን ፡ ልማድ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የሁለቱም ፡ ክፍለ ፡ ዓለማት ፡ አሕ ጉሮች ፡ ሊደርሱበት ፡ ያሰቡትን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ግብ ፡ ሊያደርሰው ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ የሚታመንበትን ፡ አስተያየት ፡ ያተርፍልናል ። በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሠራው ፡ ሕግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተዋይነትንና ፡ ጥንቃቄን ፡ ለሚጠይቀው ፡ ለዘመና ዊው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃና ፡ አዲሶችንም ፡ ሕጎች ፡ ለማዘጋጀት ፡ የብርሃንን ፡ በር ፡ የከፈተ ፡ ከፍተኛ ፡ ሙከራና ፡የሥራ ፡ ጥረት ፡ ስለሆነ ፡ ለአገሪቱ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያስገ ኘው ፡ ጥቅምና ፡ ያበረከተው ፡ አገልግሎት ፡ በቀላሉ ፡ የሚገመት ፡ አይደለም ።

የሕጉ ፡ አሠራር ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጠቃሚነቱን ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ሊያስገኝ ፡ የቻለው ፡ በመቅድሙ ፡ (በቍጥር ፡ ፫ና ፡ ፩-፲ና ፡ ፲፫ ፡ እንዲሁም ፡ በመግቢያው) ፡ እንደ ተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ የወንጀል ፡ አሠራርን ፡ ትርጓሜ ፡ ማለት ፡ ወንጀለኛ ፡ የሚያሰኙትን ፡ ጥፋቶችና ፡ በጥፋተኛውም ፡ ላይ ፡ የሚደርሰውን ፡ የቅጣት ፡ ልክ ፡ ትክክለኛና ፡ እጅግ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዓይነት ፡ ወስኖ ፡ መገኘቱ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ የዳኝ ነቱ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በባሕላዊው ፡ ልማድ ፡ መሠ ረት ፡ ይፈጸም ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ያጋጥም ፡ የነበረውን ፡ ችግር ፡ ዘርዝሮ ፡ በመግለጽ ፡ “እስካሁን ፡ የነበረው ፡ ልማድ ፡ ወንጀለኛ ፡ የሚቀጣበት ፡ በዓይን ፡ በሚታይ ፡ ጥፋት ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ የጥፋቱ ፡ ደረጃ ፡ መጠን ፡ ተመዛዝኖ ፡ የአጥፊው ፡ አላፊነት ፡ ተመርምሮ ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ እንዲያገኝ ፡ የቆመውንም ፡ ሕግ ፡ በመተላለፍ ፡ በሚሆነው ፡ ጥፋት ፡ የመቀጫው ፡ ልክ ፡ በደንብ ፡ ስላልተወሰነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ትእዛዝና ፡ ሕግ ፡ ተላልፎ ፡ ለፍርድ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ፈራጆቹ ፡ ትእዛዝና ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ያውቃሉ ፡ እንጂ ፡ የወንጀሉን ፡ ደረጃና ፡ የቅጣቱን ፡ ልክ ፡ ካለማወቃቸው ፡ የተነሣ ፡ ይህንን ፡ ስላደረገ ፡ ይቀጣል ፡ ቅጣቱን ፡ ግን ፡ መንግሥት ፡ ያውቃል” ፡ እያሉ ፡ ይበይኑ ፡ ስለነበረ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ ቅጣቱ ፡ ተለይቶ ፡ ታውቆ ፡ ይህነን ፡ የመሰለው ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ እንዲቀር ፡ ሕዝቡም ፡ ሕጉ ፡ የሚከለክለውንና ፡ የማይከለክለውን ፡ ያለ ችግር ፡ ለመለየት ፡ እንዲችል ፡ ይህም ፡ ዘመናዊውን ፡ ሥልጣኔ ፡ እየተማረ ፡ ወደ ፡ ትልቅ ፡ የእውቀት ፡ ደረጃ ፡ እንዲደርስ ፡ የሚለውን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ተከትሎ ፡ የተሠራ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ከፍተኛ ፡ ግምትን ፡ ያስገኘው ፡ ሁለተኛው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ የቅጣትን ፡ አወ ሷሰን ፡ ደንብ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዓይነት ፡ መዘርዘሩና ፡ ክባድነቱንም ፡ እጅግ ፡ ማቃለሉ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ቅጣቱን ፡ ከጨካኝነት ፡ ወደ ፡ ርኅራኄ ፡ ተሻሽሎ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ማድረ ጉም ፡ ጭምር ፡ ነው ። የመቀጮው ፡ አከፋፈል ፡ ቅጣት ፡ ከሕዝቡ ፡ የኤኮኖሚክ ፡ ዐቅም ፡ ጋር ፡ የተመዛዘነ ፡ እንዲሆንና ፡ በኢትዮጵያም ፡ በዘመኑ ፡ በሚሠራበት ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡

በጊዜው ፡ ገንዘብ ፡[15] እንዲከፈል ፡ በያንዳንዱ ፡ ተቀጪ ፡ ደረጃና ፡ ካለው ፡ ሀብት ፡ መጠን ፡ ጋር ፡ የተወዳደረ ፡ እንዲሆን ፡ (ቊጥር ፡ ፪ና ፡ ከ፩ ፡ እስከ ፡ ፱ ፡ መቅድም) ፡ በአካል ፡ ማጕደል ፡ ይፈጸሙ ፡ የነበሩ ፡ ቅጣቶችና ፡ ለምልክት ፡ ያህል ፡ ጥቂት ፡ ቀርቶ ፡ የነበረው ፡ የዓይንን ፡ በዓይን ፡ የቋንጃ ፡ መቍረጥን ፡ በቋንጃ ፡ ቆረጣ ፡ ይካካስ ፡ የነበረው ፡ ቅጣት ፡ በፍጹም ፡ እንዲሠረዝ ፡ በማድረግ ፡ ጨርሶ ፡ አስቀርቷል ። የግርፋትን ፡ ቅጣት ፡ ግን ፡ ለማስቀረት ፡ አስቦ ፡ ብዙ ፡ ማመንታት ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ የሌሎችን ፡ አገሮች ፡ ምሳሌ በመከተል ፡ እንደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ በሚፈጸመው ፡ ሁኔታ ፡ ለጊዜው ፡ ሲሠራበት ፡ እንዲቆይ ፡ አድርጓል ፤ ስለሆነም ፡ ግን ፡ በግርፋቱ ፡ ብዛት ፡ ረገድም ፡ ሆነ ፡ ባፈጻጸሙ ፡ በኩል ፡ እንዲሁም ፡ የግርፋትን ፡ ፍርድ ፡ ሊያስከትሉ ፡ በሚችሉት ፡ ወንጀሎች ፡ እጅግ ፡ ከባድነት ፡ ለምሳሌ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ የኃይል ፡ ሥርቆት ፡ የዘረፋ ፡ ተግባር ፡ እንደመፈጸም ፡ ባሉት ፡ ከባድ ፡ ጉዳዮች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ እንዲሆን ፡ ቢያደርግም ፡ ፈራጁ ፡ ዳኛ ፡ የወንጀሉን ፡ ከባድነት ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ነገሩን ፡ ለማቅለል ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደሆነ ፡ በግርፋቱ ፡ ፈንታ ፡ የመቀጫ ፡ ገንዘብ ፡ ለማስከፈልና ፡ ግርፋቱ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ፡ በሚል ፡ አነጋገር ፡ እጅግ ፡ የተቃለለ ፡ እንዲሆንና ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄም ፡ እንዲደረግበት ፡ አጥብቆ ፡ አስቦበታል (የወ ፡ መ ፡ ደ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ እስከ ፡ ፬) ። የግል ፡ ነጻነትን ፡ በማሳጣት ፡ የሚወሰነው ፡ የእስራት ፡ ቅጣትም ፡ እንደዚሁ ፡ በአፈጻጸሙ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ቀላልነት ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ከባድነት ፡ እንዳያዝነብል ፡ አስፈላጊውን ፡ የጥንቃቄ ፡ ሥርዓት ፡ ዘርዝሮ ፡ ያመለክታል (የመ ፡ ወ ፡ ደ ፡ ቍ ፡ ፭) ። በመቀጫ ፡ ስለሚወሰዱ ፡ ወይም ፡ ስለሚወረሱ ፡ ሀብቶች ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ የተመላበትን ፡ ጠንቃቃ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቷል ፤ ይኸውም ፡ በተቀጪው ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ ቅጣት ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ለሕይወቱና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ መኖሪያ ፡ ለዕለት ፡ መኖው ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ቢወሰዱበት ፡ ጉዳት ፡ የሚደርስበት ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ሠራተኛም ፡ የዕለት ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውንበት ፡ መሣሪያው ፡ በቅጣት ፡ ስም ፡ ቢወሰድበት ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ በማመዛዘን ፡ በተቀጪውና ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የኅብረት ፡ መፍረስ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ተደርጎበታል (ከቍጥር ፡ ፳፭ ፡ እስከ ፡ ፴፩) ። ከአገር ፡ የመሰደድ ፡ ወይም ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ የመኖር ፡ ግዴታ ፡ ቅጣት ፡ ለተወሰነ ፡ ዘመን ፡ የሚቀጣ ፡ ሰው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ችሎት ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ ፈራጅ ፡ ዳኛ ፡ እንዳይፈረድ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተከልክሏል (ቍጥር ፡ ፳) ። እንዲሁም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስወስን ፡ ጥፋት ፡ ሲያጋጥም ፡ ተቀጭው ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ከተፈረደበት ፡ በኋላ ፡ ይግባኙን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱ ፡ የተጠበቀለት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ፍርዱንም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ካላጸደቀው ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዳይሆን ፡ በሕጉ ፡ ተወስኖ ፡ ይገኛል ፡ (ቍጥር ፡ ፭) ።

---

[15] እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ እስከ ፡ ፲፰፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ (ከኛ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ወደኋላ ፡ ይቀራል ፡ እንደሚተረከውም ፡ ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ዝና ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተራሮች ፡ ደርሶ ፡ እስኪሰማ ፡ በመዘግየቱ ፡ ነው ፡ ይባላል) መቀጫ ፡ ወይም ፡ ለተበዳይ ፡ካሣ ፡ የሚከፈለው ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ሳይሆን ፡ በከብት ፡ ነበረ ። ከ፲፰፻ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ደግሞ ፡ በዐሞሌ ፡ ጨው ፡ ሲከፈል ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ዘመናዊ ፡ የአስተዳደር ፡ ድርጅት ፡ እንደተቋቋመና ፡ የመገበያያውም ፡ ዘዴ ፡ በተሻሻለ ፡ ሁኔታ ፡ ስለተደራጀ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ማለት ፡ በብር ፡ መከፈል ፡ ጀመረ ። በቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ በብር ፡ ማዕድን ፡ የተሠራው ፡ የአትሪሽ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ በነበረችው ፡ በማሪቴሬዝ ፡ መልክ ፡ የታተመው ፡ ጥሬ ፡ ብር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ገንዘብ ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራበት ፡ መቆየቱ ፡ ይታወሳል ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ዳግማዊ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በመልካቸው ፡ የተቀረጸ ፡ ብር ፡ አሳትመው ፡ እንዲሠራበት ፡ አድርገዋል ። በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ባሁኑ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መልክ ፡ የታተመ ፡ ኦፊሲዬል ፡ የታወቀ ፡ የባንክ ፡ ኖት ፡ ወረቀት ፡ በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ ይገኛል ። የተባሉት ፡ ጥንታዊ ፡ የብር ፡ ገንዘቦች ፡ ለኮሌክሲዮንና ፡ ለጌጣጌጥ ፡ መሥሪያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ሆነው ፡ እስከዛሬም ፡ በብዙ ፡ ይገኛሉ ።

ስለዚህ ፡ በስሕተት ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ ባለማወቅ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ስም ፡ ለማጥፋት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለሰሚዎች ፡ አንዳንድ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ለማቅረብ ፡ ፍላጎት ፡ ያላቸው ፡ ተላላፊ ፡ መንገደኞች ፡ (አገር ፡ ጐብኝዎች ፡) እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ ሳያውቁ ፡ በጥራዝ ፡ ነጠቅነት ፡ ብቻ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ እየፈጠሩ ፡ እንደሚያወሩት ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አካላትን ፡ በመቍረጥ ፡ የሚፈጸሙ ፡ የተቀጭው ፡ ሕይወት ፡ እስኪ. ያልፍ ፡ ድረስ ፡ የመግረፍ ፡ በእሳት ፡ ግሎ ፡ በቀላ ፡ ብረት ፡ ገላን ፡ በመጥበስ ፡ ልዩ ፡ ምል ክት ፡ የመስጠት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በሚነድ ፡ እሳት ፡ በማቃጠል ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ አሰቅ ይቶ ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ የመግደል ፡ ቅጣት ፡ ይፈጸማል ፡ የሚሉት ፡ ሰሚን ፡ ለማስደነቅ ፡ ወይም ፡ አንዳች ፡ መቆጣጠር ፡ ያልተደረገበት ፡ ጥንታዊ ፡ አፈ ፡ ታሪክን ፡ በመከተል ፡ እየተነሳሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከእውነተኛው ፡ የወንጀል ፡ ሕግ ፡ አስተዳደር ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ የመነጨ ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ።

እውነተኛውን ፡ የታሪክ ፡ ምንጭ ፡ ተከታትለው ፡ የተረዱ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ የሕጉ ፡ አሠራር ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ የተመላበት ፡ መሆኑን ፡ መስክረው ፡ የዚህ ፡ ዓይ ነት ፡ አፈጻጸም ፡ ያለመኖሩን ፡ በማረጋገጥ ፡ ምስክርነታቸውን ፡ ከመስጠታቸውም ፡ በቀር ፡ ጥንታዊውን ፡ ልማድ ፡ ለማስቀረትና ፡ እጅግ ፡ ወደ ፡ ተሻሻለ ፡ እርምጃ ፡ ለመሻ ገር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቆራጥነትንና ፡ መሰዋዕትነትን ፡ እንደጠየቀ ፡ ለመረዳት ፡ ከግምት ፡ በላይ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸውልናል ።[16]

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ተሻሽሎ ፡ በዘመናዊ ፡ ሁኔታ ፡ እስከተሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ጨካኝ ፡ መስሎ ፡ ቢታይም ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ ግምት ፡ ሊያስከትል ፡ የቻለው ፡ እንደ ፡ ኤሮፓ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ እየተራመደ ፡ ሳይሻሻል ፡ በመቆ የቱና ፡ ጥንታዊውን ፡ ባሕል ፡ ለመተው ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ያጋጠመው ፡ ከመሆኑም ፡ ይልቅ ፡ ቅጣቱ ፡ ከሕዝቡ ፡ ስሜት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ለመሆን ፡ እንዲችል ፡ በተቀጭው ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ፍራቻን ፡ የሚያሳድር ፡ የኃጢአት ፡ ማውረጃ ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰን ፡ ሆኖ ፡

---

[16] ኤል ፡ ቀራን ፡ አቢሲኒያ ፡ አን ፡ ዘ ፡ ኢቭ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ (ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ፍርድ) ለንደን ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ገጽ ፡ ፴፫ ፡ በጻፈው ፡ ድርሰትና ፡ ሔንሪ ፡ ደ ፡ ሞንፍሬድ ፡ (በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የተባረረው ፡ (አፍሪክ ፡ ኗር ፡ ኢትዮፒ ፡ ኤ ፡ ማዳጋስካር) ጥቁር ፡ አፍሪካ ፡ ኢትዮ ጵያና ፡ ማዳጋስካር) በሚል ፡ አርዕስት ፡ በለሞንድ ፡ ኮሌክሲዮን ፡ በባለቀለም ፡ ድርሰት ፡ (፫ሪስ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ከገጽ ፡ ፫፻፶ ፡ እስከ ፡ ፫፻፶፫) ፡ በጻፉት ፡ ድርሰት ፡ የገለጹትን ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ የሆነ ፡ አፈታሪክ ፡ የተመላበትን ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ ፈንጠዝያ ፡ በሙሉ ፡ ኃይልና ፡ በግልጽ ፡ መቃወምና ፡ እንደቁም ፡ ነገር ፡ ያለመ ቁጠር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ኤም ፡ አቤርሰን ፡ የተባለው ፡ ከኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ የነበረው ፡ በነበረውም ፡ የሥራ ፡ አላፊነት ፡ ምክንያት ፡ ጉዳዩን ፡ በቅርብ ፡ ተከታትሎ ፡ ለመረ ዳት ፡ የሚያስችለው ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ድርጅት ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ ማብራሪያ ፡ ለዠኔቭ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ባቀረበው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ (በ፲፱፻፴፯ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ዓ ፡ ም) ባሳተመው ፡ ጽሑፍ ፡ በገጽ ፡ ፩፻፯ ፡ ላይ ፡ በኢት ዮጵያ ፡ ስለሚኖሩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ የዳኝነት ፡ አስተዳደር ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ሕጉ ፡ አረማዊና ፡ ጨ ካኝ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ የሚወራውን ፡ መሠረት ፡ የሌለውን ፡ አፈታሪክ ፡ በፍጹም ፡ በማስተባበል ፡ በአጻጻፉ ፡ ዘዴ ፡ እጥረት ፡ የተነሳ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ አስተያየት ፡ ቢሰጠውም ፡ እንደ ፡ እውነቱ ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ስሜት ፡ የማያስከትል ፡ አንዳችም ፡ ጉድለት ፡ የሌለበት ፡ መሆኑን ፡ አስረድቷል ። እንዲሁም ፡ ከ፲፱፻፲፱ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ትኖር ፡ የነበረችውና ፡ እንደገናም ፡ በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተመልሳ ፡ እዚ ያው ፡ የምትገኘው ፡ ማዳም ፡ ሳንድፎርድ ፡ ኢትዮፒያ ፡ አንደር ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጻፈችው ፡ ድርሰቷ ፡ በገጽ ፡ ፹፩ ፡ ላይ ፡ የገለጸችልን ፡ አንዳችም ፡ አድልዎ ፡ በሌለበት ፡ ፍጹም ፡ እው ነተኛ ፡ በሆነው ፡ ምስክርነቱዋ ፡ የዚህ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ እውነተኛ ፡ ተግባር ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ቅን ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተና ፡ ቆራጥነት ፡ የተመላበት ፡ ጀግንነትን ፡ የጠየቀ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ነዋሪ ፡ መታሰቢያ ፡ የሚሆን ፡ ነው ፡ ስትል ፡ አረጋግጣልናለች ፤ ይህም ፡ አስተያየት ፡ የራሱዋ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፕሮፌ ሰር ፡ ኤን ፡ ቤንትዊች ፡ በግንቦት ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በገጽ ፡ ፪፻፳፬ና ፡ በተከታዩ ፡ ኮንቴምፖራሪ ፡ ሬቪው ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በጻፈው ፡ ድርሰቱ ፡ ላይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉን ፡ ማብራሪያ ፡ ሲሰጥ ፡ የማዳም ፡ ሳንድ ፎርድን ፡ አሳብ ፡ የደገፈ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸልናል ።

በመቆየቱ ፡ የሚወሰነውም ፡ የቅጣት ፡ ዓይነት ፡ ለአገሩ ፡ ባዕድ ፡ ለሆነ ፡ ለእንግዳ ፡ ተመ
ልካች ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ በመገመቱ ፡ ለፍርድ ፡ አሠራር ፡ በታሪክም ፡ ሆነ ፡ በባሕላዊ ፡
ልማድ ፡ ረገድ ፡ ይፈጸም ፡ የነበረው ፡ የቅጣት ፡ ዓይነት ፡ ከሌላው ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ በመታ
የቱ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ ግን ፡ በኤሮፓ ፡ አገር ፡ በረቂቅ ፡ ዘዴና ፡ በዘመናዊ ፡ ጥበብ ፡ ተሸ
ፍኖ ፡ በመታየቱ ፡ ብቻ ፡ ቀላል ፡ ይምሰል ፡ እንጂ ፡ በሠለጠነው ፡ ኤሮፓ ፡ አገር ፡ የሚፈ
ጸመውን ፡ አሠቃቂና ፡ ከሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ የራቀውን ፡ ከባዱን ፡ የማሠቃየት ፡ ቅጣት ፡
በሥራ ፡ ላይ ፡ አውሎት ፡ እንደማያውቅ ፡ ማመን ፡ ይገባናል ። ባሕላዊ ፡ የሆነውም ፡ የቅ
ጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ልማድ ፡ ለመቆየት ፡ የቻለው ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ቅጣት ፡ ከልማዳቸው ፡
ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ የኖረ ፡ ጥንታዊ ፡ ሕዝቦች ፡ ለኑሯቸው ፡ ጸጥታ ፡ ዋስትና ፡ ሊሆን ፡ የሚ
ችል ፡ መስሎ ፡ ስለታያቸውና ፡ ይህን ፡ እምነታቸውንም ፡ ለመለወጥ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጅ
ባቸው ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ብንል ፡ አስተያየታችን ፡ የተሳሳተ ፡ ሊ
ሆን ፡ አይገባውም ።

ለሕጉ ፡ አሠራር ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ የያዘ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለውን ፡ ግምት ፡
የሚሰጠው፣ ሦስተኛው፣ ነጥብ፣ ደግሞ፣ የአዘጋጃጀቱ፣ ቅጥ፣ (ፎርም) ጥበባዊ፣ ዘዴ፣ እጅግ፣
የሚመሰገን ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያ ፡ የሆነው ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ ቅጣት ፡
በተቀጭው ፡ አቅም ፡ መጠንና ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ የግል ፡ ሆኖ ፡ በትክክለኛ ፡ ሚዛን ፡
ላይ ፡ እንዲያርፍ ፡ ያደረገው ፡ ጥረት ፡ ሲሆን ፡ በአጥፊው ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ በማኅበራዊ ፡
ኑሮው ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ክብር ፡ በሚያከናውነው ፡ ሥራ ፡ ከፍተኛነትና ፡ በሀብቱ ፡ ም
ንጭ ፡ ተመዛዛኝ ፡ ሆኖ ፡ እንዲወሰን ፡ ማድረጉ ፡ ነው ። ይህም ፡ የመነጨው ፡ በከፍተኛ ፡
ደረጃ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሹም ፡ እንደ ፡ ሹመቱ ፡ ደረጃ ፡ ከፍተኛነት ፡ አዋቂም ፡ ሰው ፡ እንደ
እውቀቱ ፡ ሀብታሙም ፡ ባለው ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡ መጠን ፡ የሚወሰንበት ፡ ቅጣት ፡ ከአ
ቅሙ ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ፡ ከሚለው ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ መሆኑን ፡
በግልጽ ፡ የሚያሳየው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ እኩልነት ፡ እንዲኖር ፡ የሕጉም ፡
አፈጻጸም ፡ ሚዛናዊ ፡ መንፈስ ፡ የተመላበት ፡ እንዲሆንና ፡ የተረጋገጠ ፡ አወሳሰን ፡ እንዲ
ኖረው ፡ የተደረገውን ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያሳየ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በመቅድሙም ፡
ላይ ፡ መንፈሳዊነት ፡ በተመላበት ፡ በተለመደ ፡ አነጋገሩ ፡ ሲገልጽ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡
"...... በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ ዛሬ ፡ ካለው ፡ ሕዝብ ፡ አውቆ ፡ ከሚያጠፋው ፡
ሳያውቅ ፡ የሚያጠፋው ፡ ሰው ፡ ይበዛልና ፡ ሳያውቅ ፡ በሚያጠፋው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡
ቅጣት ፡ መወሰን ፡ አእምሮን ፡ ያለመገመት ፡ እንዳይሆን ፡ ደግሞ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ በፈ
ቃዱ ፡ የሚሠራውን ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ያለፈቃዱ ፡ በድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ወይም ፡ በቸል
ተኛነት ፡ ከሚሠራው ፡ ጥፋት ፡ ጋር ፡ ያለፈቃዱም ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ በድን
ገተኛ ፡ አደጋና ፡ በዝንጋታ ፡ የሚደረገውን ፡ መለየት ፡ ስለሚገባ ፡ ......ጌታችን ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ሲያስተምር ፡ በቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ እንደሚነበበው ፡ ብዙ ፡
የሚያውቅ ፡ በብዙ ፡ ይቀጣል ፡ ጥቂት ፡ የሚያውቅ ፡ ግን ፡ በጥቂቱ ፡ ይቀጣል ፡ ብሏል ።
እንደዚሁም ፡ ሰለስቱ ፡ ምእት ፡ እንደ ፡ አእምሮው ፡ መጠን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡
መጠን ፡ ሰውን ፡ መቅጣት ፡ እንዳይገባ ፡ አውቀው ፡ በሕፃንና ፡ በሰካር ፡ በእብድና ፡ በዝ
ንጉ ፡ ከሚፈረደው ፡ ፍርድ ፡ አእምሮ ፡ ባለው ፡ በትልቅ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚፈረደውን ፡
ፍርድ ፡ ለይተዋልና ....... ።" ለስድብ ፡ ወንጀል ፡ የስድብ ፡ ካሳ ፡ የሚወሰነው ፡ እንደ ፡
ተሰዳቢው ፡ ማዕርግና ፡ እንደ ፡ ስድቡ ፡ ከባድነት ፡ እየታየ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የተራው ፡
ሰው ፡ እንደባለማዕርጉ ፡ ሰው ፡ ትንሹ ፡ ስድብ ፡ እንደ ፡ ትልቁ ፡ ስድብ ፡ ካሣ ፡ አይቆረ
ጥም ።

እንዲሁም ፡ የተሾመም ፡ እንደ ፡ ክብረቱ ፡ አዋቂም ፡ እንደ ፡ እውቀቱ ፡ እንዲቀጣ ፡
እንጂ ፡ እንደ ፡ ተራው ፡ እንደ ፡ አለአዋቂው ፡ ሰው ፡ ካሣ ፡ ብቻ ፡ ከፍሎ ፡ በእውቀቱ ፡ ተመ
ክቶ ፡ በድፍረት ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ሳይቀጣ ፡ እንዳይቀር ፡ እርሱንም ፡ አጥግቦ ፡ ከመ

በደል ፡ ካደረሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የሚከሰው ፡ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ለድኃና ፡ ለትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲሆን ፡ ከካሣው ፡ እንደ ፡ ማዕርጉ ፡ ዓይነትና ፡ እንደ ፡ እውቀቱ ፡ መጠን ፡ መቀጫ ፡ ይጨመርበት ፡ (ከቍጥር ፡ ፲፬ ፡ እስከ ፡ ፳) ።

የሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የሹመትና ፡ የማዕርግ ፡ ደረጃ ፡ ካሉ ፡ ከመኳንንት ፡ እስከ ፡ መሳፍንት ፡ ከጦር ፡ አለቃ ፡ እስከ ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ ከጠቅላይ ፡ አገረ፡ገዥ፡እስከ፡ጭቃ፡ሹም፡የሲቪል፡ (ተራውና፡ጥቍር፡ራሱ) ወይም፡የወታደር፡ክፍል፡ የሆኑ፡ሁሉ፡የመሳፍንትና፡የንጉሥ፡ልጆችም፡ሳይቀር፡ከባላምባራስ፡እስከ፡ራስ፡የሹመት፡ ማዕርግ ፡ ስም ፡ ያላቸው ፡ ከዳኞችም ፡ ከተራ ፡ ወንበር ፡ እስከ ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ መጨረሻውም ፡ ተራ ፡ ሕዝብ ፡ ከሀብታሙና ፡ ከከፍተኛው ፡ ባለጸጋ ፡ እስከ ፡ ተራው ፡ ድኃ ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ እንደየደረጃቸው ፡ በመዘርዘር ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸም ፡ በሚቀጡ ፡ ጊዜ ፡ የወንጀሉን ፡ ዓይነትና ፡ ለተበዳዩ ፡ የሚከፈለው ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ ሳይቀር ፡ የሚከፍሉትን ፡ መቀጫ ፡ እንደየማዕርጋቸውና ፡ እንደየደረጃቸው ፡ መድቦ ፡ የወንጀሉንም ፡ ዓይነትና ፡ የአፈጻጸሙን ፡ ሁኔታ ፡ እየገለጸ ፡ በአመጸኛነት ፡ በእብሪተኛነት ፡ በምቀኛነት ፡ በተንኰለኛነት ፡ በቂመኛነት ፡ በጥጋበኛነት ፡ በጠበኛነት ፡ በሰበበኛነት ፡ በአጥቂነት ፡ ወንጀል ፡ ሲፈጸም ፡ ወይም ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ በደል ፡ ሲያደርስ ፡ ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ወይም ፡ የአልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነትን ፡ ሙብት ፡ ከመጠኑ ፡ አሳልፎ ፡ በመገልገል ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛው ፡ ሊሠራው ፡ ካሰበው ፡ ተግባር ፡ በላይ ፡ አሳልፎ ፡ በመፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ አፈጻጸምና ፡ አፈጻጸሙ ፡ ባስከተለው ፡ ውጤት ፡ መጠን ፡ እያመዛዘነ ፡ ከመጨረሻው ፡ ዝቅተኛ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ከፍተኛ ፡ የሚደርሰውን ፡ የመቀጫ ፡ ልክ ፡ በመወሰን ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሮ ፡ በማስረዳት ፡ የሚደነግግ ፡ ክፍል ፡ ነው ፤ (ከ፶፪ ፡ እስከ ፡ ፩፻፵፰) ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ለማወቅ ፡ ባለመቻል ፡ (ከቍ ፡ ፲፪ ፡ እስከ ፡ ፳፩) ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ጥፋቱን ፡ አውቆ ፡ ለሚጸጸት ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ የእምነት ፡ ቃሉን ፡ ለሚሰጥ ፡ (ቍጥር ፡ ፵፪ና ፡ ተከታዩ) የቅጣት ፡ ቅነሳ ፡ እንዲደረግለት ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሮ ፡ አመልክቷል ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ እንግዲህ ፡ ቅጣትን ፡ በጥፋት ፡ መጠን ፡ በተቀጭውም ፡ ዐቅም ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሚሆንበት ፡ ዘዴ ፡ ወንጀሉን ፡ ለመሥራት ፡ ባነሳሱት ፡ ምክንያቶች ፡ በአካባቢዎቹ ፡ ሁኔታዎችና ፡ በአጥፊውም ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ መጠን ፡ አስተካክሎና ፡ አብራርቶ ፡ የሚወስን ፡ ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መገኘቱ ፡ ከተያዘ ፡ ዘመናዊና ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ ለመሥራት ፡ አስቸጋሪው ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ ተቃንቶና ፡ ተደራጅቶ ፡ ለመገኘት ፡ ችሏልና ፡ የሕጉን ፡ አሠራር ፡ ከማሻሻልና ፡ ያንኑ ፡ የቀድሞውን ፡ ሕግ ፡ አስፋፍቶና ፡ አብራርቶ ፡ ከመጻፍ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሁኔታ ፡ ሊያጋጥም ፡ አይችልም ።

በመጨረሻውም ፡ ለሐሳባችን ፡ መደምደሚያ ፡ አድርገን ፡ የምንገልጸው ፡ ባ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሠራው ፡ የቀድሞው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በልዩ ፡ ክፍሉ ፡ ላይ ፡ በሚገባ ፡ ተጣርተውና ፡ በግልጽ ፡ ተደራጅተው ፡ በዝርዝር ፡ የተገለጹ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተጠናቀው ፡ ይገኛሉ ፤ በተለይም ፡ ሦስቱን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ መሠረታዊያን ፡ ነገሮች ፡ በሚገባ ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚችሉ ፡ ማረጋገጫዎች ፡ እንዲገኙ ፡ አድርጓል ፤ እነዚህም ፡ በመንግሥት ፡ ጸጥታና ፡ በሕዝብ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (፩ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ከቍጥር ፡ ፩፻፷ ፡ እስከ ፡ ፪፻፸፪) በሰዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (፪ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፸፫ ፡ እስከ ፡ ፬፻፲፩) በገንዘብ ፡ በሀብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (፫ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ከቍጥር ፡ ፬፻፲፪ ፡ እስከ ፡ ፬፻፲፰) የገለጸ ፡ ከመሆኑም ፡ በቀር ፡ በዘልማድ ፡ ዘወትር ፡ ስለሚሠሩት ፡ ወንጀሎችም ፡ የሚወሰኑትን ፡ ቅጣቶች ፡ በመዘርዘር ፡ ወስኖ

አቸው ፡ ይገኛል ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ (በ፳ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ከቍጥር ፡ ፬፻፳፱ ፡ እስከ ፡ ፬፻፹፯) ስለ ፡ ትንንሽ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ቅጣትና ፡ ለሕዝብ ፡ መመላለሻ ፡ በሆኑት ፡ መንገዶች ፡ የቆመውን ፡ ደንብ ፡ በመተላለፍ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ የሚወሰኑትን ፡ ቅጣቶች ፡ ለይቶ ፡ በመዘርዘር ፡ ያመለክታል ። በዚህ ፡ ዓይነት፡ አሠራር፡ እንዲህ ፡ ሕጉ፡ በአስፈላጊው ፡ ጊዜ ፡ ተሻሽሎና ፡ ተስፋፍቶ ፡ እንደጊዜው ፡ ፍላጐት ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል በትን ፡ መንገድ ፡ አስቀድሞ ፡ በሚገባ ፡ መሥርቶ ፡ አቆይቶልናል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የቆየን ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራ ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆነው ፡ ለአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ መሪ ፡ ሆኖን ፡ ከመገኘቱም ፡ በላይ ፡ ለሥራችን ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ነጥቦችን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ያቆየልን ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘነው ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፉ ፡ መርምረን ፡ በቂ ፡ አስረጂዎችን ፡ ካገኘንበት ፡ በኋላ ፡ እርሱኑ ፡ በማሟላትና ፡ ከከፍተኛ ፡ ጥንታቱ ፡ አርመንና ፡ አሻሽለን ፡ ከማስፋፋት ፡ በቀር ፡ የአዲሱ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ጠቅላላ ፡ ድርጅት ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ከፍተኛ ፡ ድካም ፡ አልጣለብንም ።

ስለሆነም ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ለመሸጋገር ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ ለዘመናዊው ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ (ቴክኒክ) ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ያለመገኘቱ ፡ የታመነ ፡ ነው ። በአጻጻፉ ፡ ጥበብ ፡ ላይ ፡ ጥንታዊ ፡ የሆኑትን ፡ ልማዶች ፡ ባለመልቀቅ ፡ የጠንካራነትን ፡ ያለመሻሻልንና ፡ የፎርማሊዝምን፡ (የተወሰኑ ፡ ቅጦችን ፡ የማክበርና ፡ መቀበል) ጠባይ ፡ እንደያዘ ፡ ይገኛል ፤ ለምሳሌ ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅጣቶችና ፡ ስለ ፡ መቀጫ ፡ ገንዘብ ፡ አወሳሰን ፡ የተገለጸው ፡ አጻጻፍ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ካለው ፡ የፊዎዳል ፤ (ለወታደራዊ ፡ ርዳታና ፡ አገልግሎት ፡ ርስተ ፡ ጕልት ፡ የጌታና ፡ ገባር ፡ አስተዳደር) ዘመን ፡ ሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ፤ (ከቍጥር ፡ ፶፪ ፡ እስከ ፡ ፩፻፵፱) እንዲሁም ፡ የቅጣትን ፡ ማቅለልና ፡ ማክበድ ፡ ጕዳይ ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ስለ ፡ ይቅርታና ፡ በቂ ፡ ምክንያትን ፡ የማቅረብ ፡ ጕዳይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የአሠራሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ጥበብ ፡ በጥፋት ፡ መጠን ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ቅጣትን ፡ ለመወሰን ፡ በማያስችል ፡ ጥበባዊ ፡ (ቴክኒካዊ) ዘዴ ፡ የተሠራ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ፡ (ከቍጥር ፡ ፵፮ ፡ እስከ ፡ ፶፩ ፡ ፩፻፵፯እና ፡ ፩፻፶፩) ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ መግደልን ፡ ወንጀል ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ስለ ፡ ካሣው ፡ አከፋፈል ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ጥንታዊ ፡ የሆነውን ፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ የመክፈል ፡ ደንብ ፡ ያልለቀቀ ፡ ከመሆኑም ፡ በቀር ፡ ይቅርታ ፡ በሚያስገኝም ፡ ሆነ ፡ በማያስገኝ ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ አገዳደል ፡ የሰው ፡ መግደል ፡ ወንጀል ፡ ቢፈጸምም ፡ ለሟች ፡ ወገኖች ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ ከገዳዩ ፡ እንቀበላለን ፡ ብለው ፡ ከተስማሙ ፡ በወንጀለኛው ፡ ላይ ፡ የሚፈጸመው ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ቀሪ ፡ መሆኑን ፡ ስለሚያመለክትና ፡ የቀድሞውን ፡ ባሕል ፡ ያልለቀቀ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳይ ፡ ሲሆን ፡ (ከቍጥር ፡ ፬፻፩ ፡ እስከ ፡ ፬፻፲፱) በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ጥንታዊ ፡ ልማድና ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ ሊመሳሰል ፡ በሚገባው ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ የዛሬውን ፡ የሕዝብ ፡ ፀጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ ዘዴ ፡ በሚገባ ፡ አስተካክሎ ፡ ለመወሰን ፡ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ አስተዳደር ፡ መፍጠር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ይህን ፡ ልማድ ፡ ጨርሶ ፡ ለማስቀረት ፡ ለአዲሱ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ሳያጋጥመው ፡ አላለፈም ።

## ፫ ፤ ስለ ፡ ጉድለት ፡ እርማቶችና ፡ ተጨማሪ ፡ ሆነው ፡ ስለወጡ ፡ “ዐዋጆች” ።

የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ማዘጋጀት ፡ ሥራ ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነውን ፡ ሕግ ፡ ለማው
ጣት ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠውን ፡ ታሪካዊ ፡ እርምጃ ፡ ካለፈው ፡ በኋላ ፡ ከጥንታ
ዊና ፡ ከልማዳዊ ፡ የባሕል ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ዘመናዊ ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ ለመሸጋገር ፡ የገጠመ
ውን ፡ ከባድ ፡ መሰናክል ፡ በቆራጥነት ፡ ያለፈም ፡ ቢሆን ፡ ከቶ ፡ ሁሉንም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡
ሊያስብበትና ፡ አጠቃሎ ፡ ለማሟላት ፡ የማይችል ፡ በመሆኑ ፡ በሕጉ ፡ መቅደም ፡ ላይ ፡
እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ያልተመለከቱ ፡ አዲስ ፡ ነገሮች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ሊፈ
ጸም ፡ ስለሚገባው ፡ ጉዳይ ፡ በተጨማሪነት ፡ የሚሰጡትን ፡ የማሟያ ፡ ውሳኔዎች ፡ በዝር
ዝር ፡ መግለጽ ፡ ግዴታ ፡ ሆኖበት ፡ ተገኝቷል ። ምክንያቱም ፡ ዘርዝሮ ፡ ሲገልጽ ፡ “በየጊ
ዜው ፡ አዲስ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ መምጣት ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ” ፡ ያል
ተጻፈ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሲገኝ ፡ ለጊዜው ፡ በአነጋገሩ ፡ የሚመሳሰለው ፡ በዚሁ ፡ አካሄድ ፡
ይወሰን ፤ በአነጋገሩ ፡ ሳይመሳሰል ፡ በትርጓሜና ፡ በምስጢር ፡ የሚመሳሰለው ፡ ግን ፡
በዳኛው ፡ እውቀት ፡ ምርመራ ፡ እየተወሰነ ፡ ይሠራበት ፡ (መቅድም ፡ ፲፩) ፤ በሌላ ፡
በኩል ፡ ደግሞ ፡ በነገርና ፡ በትርጓሜ ፡ የማይመሳሰል ፡ ፈጽሞ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ያጋጠመ ፡
እንደሆነ ፡ ግን ፡ ከትልቁ ፡ ችሎት ፡ ደርሶ ፡ ነገሩ ፡ ይቆረጥ ፡ (መ ፡ ፲፪) ይላል ። ሕጉ ፡
ለተሠራበት ፡ ዘመን ፡ ላለው ፡ የጊዜ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡
ይህ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበባዊ ፡ ዘዴ ፡ በሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ እጅግ ፡ የተቀራ
ረበ ፡ ተመሳሳይነት ፡ ያለው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በጊዜው ፡ ለነበሩትም ፡ ግዴታዎች ፡
በቂ ፡ ምክንያትን ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑን ፡ ለአዲሱ ፡ ዘመን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ው ፡ ዘመናዊ ፡
ሕግ ፡ ለሚሠራበት ፡ በመጨረሻው ፡ ዝግጅት ፡ ጊዜ ፡ ታርሞ ፡ ተቃንቶና ፡ ተሟልቶ ፡
ደንበኛ ፡ ውጤት ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚረዳ ፡ ዋነኛ ፡ ምንጭ ፡ ሊሆነው ፡ ቢችልም ፡ የቀድ
ሞው ፡ አጻጻፍ ፡ ለዛሬው ፡ ዘመን ፡ ሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ማንኛውም ፡
ጉድለት ፡ ሳይኖርበት ፡ ተሟልቶ ፡ መቅረብ ፡ ለሚገባው ፡ ድርጅት ፡ አጥጋቢ ፡ ሆኖ ፡
ባለመገኘቱ ፡ ጠባብ ፡ ከሆነው ፡ ከሕግ ፡ መሠረትነት ፡ ጋርም ፡ ሆነ ፡ የተሟላና ፡ ጉድ
ለት ፡ የሌለው ፡ በቂ ፡ አጥጋቢነትን ፡ በመስጠት ፡ የሥልጣን ፡ መለየትን ፡ ጉዳይ ፡ በሚ
መለከት ፡ ረገድ ፡ ማለት ፡ የፈራጅን ፡ የአስተዳደርንና ፡ የሕግ ፡ አውጭን ፡ ክፍሎች ፡
የሥልጣን ፡ ድልድል ፡ በመለየት ፡ ረገድ ፡ ዘመናዊ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ያላቸውን ፡
አገሮች ፡ የአጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ በመከተል ፡ ፋንታ ፡ ሕግ ፡ መስጠትን ፡ ማስፈጸምንና ፡ በተሰ
ጠው ፡ ሕግ ፡ መፍረድን ፡ በአንድ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አጠቃሎ ፡ በመያዝ ፡ ፕሬቶሪያን ፡
(የጥንት ፡ ሮም ፡ ከተማ ፡ ዳኝነት) ወደ ፡ ተባለው ፡ ወደ ፡ ጥንታዊው ፡ የሮማዊያኖች ፡ ደንብ ፡
አፈጻጸም ፡ ዝንባሌ ፡ አድልቶ ፡ በመገኘቱ ፡ ከዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡
ያለመታየቱ ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ ግን ፡ ለሕጉ ፡ አሠራር ፡ የመጀመሪያ ፡ መነሻ ፡
ነጥብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ እንደሚያስረዳው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ከመቀ
ጠል ፡ የማያቋርጥና ፡ የማይቆም ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ ለጊ
ዜውና ፡ ለዘመኑ ፡ ተስማሚ ፡ በሆነ ፡ ዓይነት ፡ እያሻሻሉ ፡ መሔድ ፡ እንጂ ፡ የቀድሞው ፡
ዘመን ፡ ሕግ ፡ ለአዲሱ ፡ ዘመን ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ያለመገኘቱን ፡ የሕጉ ፡ አሠራር ፡ ራሱ ፡
የተረዳው ፡ በመሆኑ ፡ ቀድሞ ፡ የነበረውን ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ እንደዘመኑና ፡
እንደጊዜው ፡ እንደ ፡ ሰውም ፡ እውቀት ፡ ማደግ ፡ እንደኑሮውም ፡ መሻሻል ፡ መጠን ፡
ሕጉም ፡ እየተሻሻለና ፡ እየታደሰ ፡ እንዲሔድ ፡ (መቅድም ፡ ፱) ፡ የስድብና ፡ የአካል ፡
ጉዳይ ፡ ካሣ ፡ የነፍስ ፡ ገዳዩና ፡ የሌላውም ፡ ወንጀለኛ ፡ ሁሉ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ እንዲታ

ደስ ፡ የተደረገው ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ እንደ ፡ ጊዜውና ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ አኳኋን ፡ እያያችሁ ፡ ሥሩ ፡ ብለው ፡ ያዘዙትን ፡ (መ ፡ ፩) በመከተል ፡ የተሠራ ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ የቀድሞው ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወደፊት ፡ እየተሻሻለና ፡ እየተሟላ ፡ የሚሔድ ፡ እንጂ ፡ የመጨረሻ ፡ አለመሆኑን ፡ ገልጾ ፡ አመልክቷል ፤ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በቍጥር ፡ (፫ ፡ ወ ፡ መ) ፡ እንደተነገረው ፡ ለምሳሌ ፡ የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ ለጊዜው ፡ ጸንቶ ፡ እንዲቆይ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ሲገምት ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ልማድ ፡ ለማሻሻል ፡ እጅግ ፡ ጥንቃቄ ፡ ባለው ፡ በቀስታ ፡ እርምጃ ፡ መራመድ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ እንደ ተረዳውና ፡ እንደዚሁም ፡ አዲስ ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ያለመረዳትና ፡ ያለማወቅ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ (ቍ ፡ ፲፩ ፡ እና ፡ ተከታዩ) ፡ በገንዘብ ፡ ስለሚከፈለው ፡ መቀጮ ፡ አከፋፈልና ፡ ስለአወሳሰኑ ፡ በተደረገው ፡ ጥብቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ (ቍ ፡ ፶፫ ፡ እና ፡ ተከታዩ ፡ ፩፻፶፰ ፡ እና ፡ ፩፻፶፱) ፡ ወይም ፡ የስድብን ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ማድረስንና ፡ የነፍስ ፡ ግዳይን ፡ ወንጀል ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ (ቍ ፡ ፪፻፸፫—፫፻፴፱—፬፻፬ ፡ እና ፡ ተከታዩ) እየተሻሻለ ፡ የሚለወጥ ፡ ደንብ ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚታሰብበት ፡ መሆኑን ፡ ሳይገነዘበው ፡ ያለፈ ፡ አይደለም ።

ከኢጣልያን ፡ ወረራና ፡ በወረራውም ፡ ጊዜ ፡ ኢጣልያን ፡ አውጥቶት ፡ ከነበረው ፡ ሕግ ፡ በኋላ ፡ የአገሪቱ ፡ ነጻነት ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተመልሶ ፡ በተቋቋመ ፡ ጊዜ ፡ የብሔራዊ ፡ አስተዳደር ፡ ድርጅት ፡ እንደተጀመረ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከ፲፱፻፴፬ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየጊዜው ፡ እየታወጁ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራ ፡ በኦፊሲየል ፡ ጋዜጣ ፡ እየተደራጁ ፡ የወጡት ፡ የወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ማሟያ ፡ የሆኑት ፡ ተጨማሪ ፡ ሕጎችና ፡ ደንቦች ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በብዙ ፡ ይገኛሉ ፤ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ዋናዋናዎቹን ፡ ብቻ ፡ ለመጥቀስ ፡ ያህል ፡ ባርነትን ፡ ስለማስቀረት ፡ የወጣውን [17] ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ተጨማሪ ፡ አዋጅ ፡ ስለ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ መቋቋምና ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ የሆኑ ፡ ወታደሮች ፡ ስለሚፈጽሙት ፡ ወንጀል [18] ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ የሕዝብ ፡ ጸጥታን ፡ በማወክ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ አዋጅ [19] ፡ ሐሰተኛ ፡ ገንዘቦችን ፡ በመሥራትና ፡ ማስረጃዎችን ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛነት ፡ በመለወጥ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ [20] ፡ ፈንጂ ፡ ነገሮችን ፡ መርዛም ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ የሚያፈዙ ፡ ነገሮችን ፡ የቁማር ፡ ጨዋታዎችንና ፡ ሎተሪዎችን ፡ ስለ ፡ መቆጣጠር ፡ የወጣ ፡ አዋጅ [21] ፡ በሕዝብ ፡ መመላለሻ ፡ መንገዶችና ፡ በአደባባዮች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለማድረስ ፡ ወንጀል ፡ የወጣ ፡ አዋጅ [22] ፡ ስለዘዋሪዎችና ፡ ሥራ ፡ ፈቶች ፡ ስለ ፡ ወሮበሎች ፡ መቆጣጠር ፡ የወጣ ፡ አዋጅ [23] ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ እስር ፡ ቤቶች ፡ (ወህኒ ፡ ቤቶች) አቋቋምና ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ [24] ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ በየጊዜው ፡ የታወጁትን ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

---

17 ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ ቍጥር ፡ ፳፪ ፡ ነሐሴ ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታወጀውን ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በማብራራት ፡ ግራቭን ፡ ረቡው ፡ ደ ፡ ክሪሚኖሎጊ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ፖሊስ ፡ ቴክኒክ ፡ በሚል ፡ መጽሔት ፡ በ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በቍጥር ፡ ፩ ፡ በገጽ ፡ ፪፻፸፱ ፡ እና ፡ ፪፻፹ ፡ ስለ ፡ ባርነት ፡ ጉዳይን ፡ ይህንኑ ፡ ለማስቀረት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ወሰደችው ፡ እርምጃ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልከት ፡

18 ቍጥር ፡ ፳፰ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ተመልከት ።

19 ቍጥር ፡ ፩ ፡ ጥር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ አዋጅ ።

20 ቍጥር ፡ ፸፯ ፡ ግንቦት ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ እና ፡ ቍጥር ፡ ፺፩ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጆች ።

21 ቍጥር ፡ ፲፱ ፡ ሐምሌ ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ቍጥር ፡ ፳፬ ፡ መስከረም ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ቍጥር ፡ ፸፯ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ።

22 ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ እና ፡ ፴፰ ፡ ሰኔ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ እና ፡ መጋቢት ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ።

23 ቍጥር ፡ ፹፱ ፡ ግንቦት ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ።

24 ቍጥር ፡ ፺፰ ፡ ጥር ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ።

አቋቋምና ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ድርጅት ፡ የተሰጡትን ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አፈጻጸምን ፡ የሚመለከቱትንና [25] ፡ ለምሳሌም ፡ ስለ ፡ ዐቃቤያነ ፡ ሕግ ፡ መቋቋምና ፡ ስለ ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን [26] ፡ የወጣውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አዋጆች ፡ ሳንዘረዝር ፡ ለቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ማሟያ ፡ የወጡት ፡ ተጨማሪ ፡ የሕግ ፡ አዋጆች ፡ ለዘመናዊው ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ አስቸኳይ ፡ ሆነው ፡ ለተገኙት ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ የተደራጁ ፡ ሆነው ፡ እንዲገኙ ፡ ለማድረግ ፡ የተፈጸመውን ፡ ድካምና ፡ ጥረት ፡ በግልጽ ፡ ሊያስረዳን ፡ ችሏል ።

ስለሆነም ፡ ግን ፡ በጠቅላላው ፡ አፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ በሚችልበት ፡ መንገድ ፡ ችግርን ፡ ያስከተለ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ሲፈጽሙ ፡ የሚገባቸውን ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ አጠቃሎ ፡ ባለመያዙ ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ያላቸውን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነጥቦች ፡ ለማሟላት ፡ ባለመቻሉ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለይቶ ፡ በማሳወቅ ፡ ረገድም ፡ ሆነ ፡ በአወሳሰናቸው ፡ በኩል ፡ በሕግ ፡ ተደንግገው ፡ ሊገለጹ ፡ የሚገባቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ የተዘበራረቁ ፡ አድርጓቸው ፡ መገኘቱ ፡ ለዘመኑ ፡ አስቸኳይ ፡ ሆነው ፡ ለተገኙትም ፡ መሠረታዊያን ፡ ጉዳዮች ፡ ሕጉን ፡ አሟልቶና ፡ አጠቃሎ ፡ በማቅረብ ፡ ረገድ ፡ በቂና ፡ አጥጋቢ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም ። በዚህ ፡ ሁኔታም ፡ በጠቅላላው ፡ ክፍሉ ፡ መገኘት ፡ ይገባቸው ፡ የነበሩት ፡ የብሔራዊው ፡ ሕግ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸምና ፡ የሕጉ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ስለሚጋጭበት ፡ ስለሚገናኝበትና ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ አላፊነትና ፡ ስለ ፡ ጥፋተኛነት ፡ ሁኔታና ፡ ቅጥ ፡ (ፎርም) ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወንጀለኞችና ፡ ደጋግመው ፡ ወንጀልን ፡ በሚሠሩ ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡ አድርገው ፡ በያዙ ፡ አጥፊዎች ፡ ላይ ፡ ሊወሰድ ፡ ስለሚገባው ፡ እርምጃና ፡ ስለሚወሰነውም ፡ የቅጣት ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ በይርጋ ፡ ስለሚቀርበትና ፡ ስለሚሠረዝበት ፡ ደንብ ፡ ዘመናዊ ፡ ለሆኑ ፡ ሕጎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገርን ፡ ስለ ፡ ያዘው ፡ ቅጣትን ፡ በገደብ ፡ ስለማገድ ፡ በአመክሮ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለመፍታትና ፡ እንደገና ፡ ስለመሠየም ፡ ይህን ፡ ለመሳሰሉት ፡ ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ዋነኛ ፡ መሠረታዊን ፡ ጉዳዮች ፡ ለሆኑት ፡ ፕሮብሌሞች ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ፍች ፡ የሚሰጥ ፡ ድንጋጌ ፡ ለይቶ ፡ ሳይገልጽ ፡ በመቅረቱ ፡ ያሠራሩ ፡ ቅንጅት ፡ (ሲስቴም) የተለያየና ፡ የተያይዞ ፡ ያልተደራጀ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። እንዲሁም ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ መገኘት ፡ ይገባቸው ፡ የነበሩት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ መሠረታዊያን ፡ ነገሮች ፡ ሳይሟሉ ፡ በመቅረታቸው ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ መብቶች ፡ አጠባበቅ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ በሕዝባዊ ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ የሕዝብ ፡ ጤንነትን ፡ የመገናኛ ፡ መሥመሮችንና ፡ መንገዶችን ፡ በፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎችና ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በኤኮኖሚክ ፡

---

[25] ቍጥር ፡ ፪ ፡ ጥር ፡ ፳፫ ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ ግንቦት ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡ ሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ቍ ፡ ፩፻፪ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ቍ ፡ ፩፻፵፱ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ የወጡትን ፡ አዋጆች ፡ ተመልከት ።

[26] የአዋጅ ፡ ቍ ፡ ፳፱ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እና ፡ ተጨማሪ ፡ አዋጆች ፡ ቍ ፡ ፩፻፲፰ ፡ እና ፡ ፩፻፳፫ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ እና ፡ ሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፌደራል ፡ ነገር ፡ የሆኑ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀልን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከት ፡ በአዋጅ ፡ ቍ ፡ ፩፻፴ ፡ (ሀ) እና ፡ ፩፻፵፩ ፡ መስከረም ፡ ፲፩ ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ እና ፡ መስከረም ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተዘርዝሮ ፡ ይገኛል ። የወንጀልን ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚያብራሩ ፡ ወይም ፡ ስለሚያሻሽሉ ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ በጠቀስነው ፡ በማሬን ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ምዕራፍ ፡ ፳ ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴ ፡ እና ፡ ለጣቂዎቹን ፡ ይመለከቷል ። ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ በየጊዜው ፡ የወጡትን ፡ ንውሳን ፡ ደንቦችና ፡ ትእዛዞችን ፡ መጥቀስ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፤ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ በ፲፱፻፵፪ ፡ የወጡ ፡ ትእዛዞች ።

ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ ሊወሰድ ፡ የሚገባውን ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ እርምጃ ፡ ሳያመለክት ፡ አልፏል ።

## <u>፬ ፤ አዲሱን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ስለ ፡ ተሰጡ ፡ መሪ ፡ ትእዛዞች ።</u>

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መጋቢት ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮንን ፡ ጉባኤ ፡ በከፈቱ ፡ ጊዜ ፡ ልዑል ፡ የኢ ፡ ን ፡ ነ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስና ፡ የዘውድ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ባሉበት ፡ ሚኒስትሮችና ፡ ከፍተኛ ፡ ሹማንንቶች ፡ በተገኙበት ፡ ባደረጉት ፡ ንግግር ፡ የሰጡትን ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ የተከተለ ፡ የተሟላ ፡ አጥጋቢና ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ዘመናዊና ፡ አዲስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለመመሥረት ፡ የመነሻ ፡ መሠረት ፡ የሆኑን ፡ ነጥቦች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ዘርዝረን ፡ ያመለከትናቸው ፡ ነዋሪ ፡ ሕጎች ፡ ነበሩ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ በንግግራቸው ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተፈጸሙትን ፡ የሕግ ፡ ማዘጋጀትን ፡ ሥራዎች ፡ ከፍተኛነት ፡ ጠቅሰዋል ።[27]

ንግግራቸውን ፡ በመቀጠል ፡ "ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ ካሻሻልን ፡ በኋላ[28] ፡ ላለፉት ፡ ዘመናት ፡ ያስገኘውን ፡ ፍሬ ፡ በማስታወስ ፡ ለዛሬው ፡ ጊዜያችን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ በማሰብና ፡ ለመጪውም ፡ የሚጠቅመውን ፡ ለማደራጀት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ የሆነውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የንግድ ፡ የወንጀል ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥቶች ፡ ፍትሕ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲደራጅ ፡ ስናስብ ፡ .... በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየቀደሙ ፡ መሄድ ፡ ለሕዝባችን ፡ እድገት ፡ ለሕይወታችንም ፡ ዋና ፡ ቍልፍ ፡ ሆኖ ፡ መቆጠር ፡ ይገባዋል ። .... ባንድ ፡ ወገን ፡ የመንግሥታችንን ፡ አቋዋም ፡

---

[27] የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ጉባኤ ፡ በተቋቋመ ፡ ጊዜ ፡ ስለተደረገው ፡ የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያደረጉትን ፡ ንግግር ፡ አብራርተው ፡ በመግለጽ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ጋዜጣዎች ፡ ታትመዋል ፡ በመጋቢት ፡ ፳፮ ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የወጣው ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሄራልድ ፤ ሚያዝያ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ የታተመውን ፡ የዛሬይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልከት ። እኛም ፡ ረቩዊ ፡ ኢንቴርናሲዮናል ፡ ደ ፡ ክሪሚኖሎዢ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ፖሊስ ፡ ቴክኒክ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ በሰጠነው ፡ ርዕስ ፡ አንቀጽ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ገጽ ፡ ፪፻፶ ፡ እና ፡ <u>ረቩዊ ፡ ፔናል ፡ ሱዊስ</u> ፡ በተባለ ፡ መጽሔት ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ገጽ ፡ ፫፻፶፰ ፡ በጻፍነው ፡ <u>አዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያና ፡ የአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ዝግጅት</u> ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ገልጸናል ።

[28] የሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዘመናት ፡ ታሪክ ፡ ላለው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ ከታሪኩ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ የመጀመሪያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሰጡት ፡ የዛሬው ፡ መሪ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነትን ፡ ዘውድ ፡ በተቀዳጁ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ሐምሌ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ። ሕገ ፡ መንግሥቱንም ፡ ያወጀው ፡ ድንጋጌ ፡ እንጋገር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሐሳብና ፡ ግብ ፡ ምን ፡ እንደነበረ ፡ በግልጽ ፡ የሚያስረዳን ፡ ነው ። ቃሉም ፡ «በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ በሕዝብ ፡ ኅብረት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ተመርጠን ፡ ዘውድንና ፡ ዙፋኑን ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ተቀብለን ፡ ስንቀባ ፡ ለዚሁ ፡ ታማኝ ፡ ለመሆን ፡ ለመረጠን ፡ ፈጣሪያችን ፡ የምንመልሰው ፡ ወረታ ፡ የተቀበልነውን ፡ አደራ ፡ እኛም ፡ ሠርተን ፡ ጠብቀን ፡ ተከታያችንም ፡ በሕግ ፡ እንዲቀበለንና ፡ በደንብ ፡ እንዲሠራ ፡ ለሀገራችንም ፡ በመልካም ፡ አስተዳደር ፡ በሕግ ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ደንብ ፡ ከማቆም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምንመልሰው ፡ ወረታ ፡ ስለሌለን ፡ ... ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ታላቅ፡ የሆነ ፡ አደራ ፡ ስለተቀበልን ፡ መንግሥታችን ፡ የሚጸናበትን ፡ የሕዝባችን ፡ ኑሮ ፡ የሚሻሻልበትንና ፡ ሕዝባችን ፡ ወደ ፡ ታላቅ ፡ ሥልጣኔና ፡ የደስታ ፡ መንገድ ፡ ተመርቶ ፡ ነፃ ፡ የሆኑና ፡ የሠለጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ያገኙትን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚያገኝበትን ፡ ማወጅና ፡ ማሠራት ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ አስተውለን» ..... (ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የጠቀስነውን ፡ የገርንጉል ፡ ዱፐሬን ፡ ድርሰት ፡ ገጽ ፡ ፫፱ ፡ እና ፡ ተከታዩን ፡ ተመልከት) ።

ሕግ ፡ [29] ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመምራት ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የሕዝባችንን ፡ ኑሮ ፡ ለማሻሻል ፡ ከዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በመቀራረብና ፡ በመረዳዳት ፡ እየሠሩ ፡ ለመኖር ፡ በባሕርም ፡ በንግድም ፡ የሚደረገው ፡ መገናኛ ፡ አስገዳጅ ፡ የሚያደርገውን ፡ ነገር ፡ ለማ ቋቋም ፡ ስንል ፡ ያቀድነውን ፡ ፕሮግራም ፡ እየተከታተልን ፡ ለመፈጸም ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሠረታዊ ፡ ሕጎች ፡ በትምህርት ፡ በንግድና ፡ በባሕር ፡ ከምንገናኛቸው ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ካሁኑ፡በበለጠ፡አኳኋን፡ማቀራረብና፡ትይዩ፡ማድረግ፡አስፈላጊነቱ፡ ተገልጿል፤እነዚህንም፡ ግንኙነቶች፡በጽኑ፡መሠረት፡ለማቋቋምና፡ ለማጠንከር፡ የሕግን፡ ግልጽነትና፡ እርግጠኛ ፡ ኖስትና፡ በሚሰጥ፡ ሁኔታ፡ ማዘጋጀት፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝበናል” ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፤

ስለ ፡ ሕጉ ፡ ማዘጋጀት ፡ ጉዳይ ፡ ከልንተለው ፡ የሚገባን ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ የትኛ ውን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ መከተል ፡ እንደሚገባው ፡ በመሪ ፡ ትእዛዛቸው ፡ ሲገልጹልን ፡ አዲስ ፡ በታወጀው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መቅድም ፡ ላይ ፡ እንደተናገሩት ፡ “ኢትዮጵያ ፡ ከመላው ፡ ዓለም ፡ ተቀዳሚ ፡ የሚሆን ፡ የሕግ ፡ አውጭነት ፡ ቢኖራትም ፡ እንኳ ፡ ለሕዝባችን ፡ በሚስማማው ፡ መጠን ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ከሚገኙት ፡ ሕጎች ፡ የተሻሉትን ፡ እየመረጥን ፡ ባገራችን ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ለማድረግ ፡ ችላ ፡ ብለን ፡ አናው ቅም ። ስለሆነም ፡ .... የኮሚሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ መነሻ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ ሳይቋረጥ ፡ የመጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግና ፡ ልማድ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል” ፡ ብለው ፡ የተናገሩት ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ ከንውን ፡ መሠረታዊ ፡ የመነሻ ፡ ነጥብ ፡ ሆኖ ፡ እንዳገለገለ ፡ ሁሉ ፡ ለአዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ዝግጅትም ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ አገልግሎ ናል [30] ። ሕጉን ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ የተጠሩት ፡ የኤውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ መሆናቸውም ፡

[29] በጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ በተደረገው ፡ የ፳፭ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ በተሰበሰቡበት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ባደረጉት ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ ላይ ፡ የዛሬ ፡ ፳፬ ፡ ዓመት ፡ በፈቃዳቸው ፡ የሰጡት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ አስተ ዳደር ፡ መሠረቱ ፡ በጠንከረ ፡ ዓምድ ፡ ላይ ፡ ያቆየ ፡ መሆኑን ፡ በማስታወስ ፡ «በሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሰበብ ፡ ሕዝባችን ፡ ያደረገውን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃና ፡ የደረሰበትን ፡ የዕውቀት ፡ ደረጃ ፡ በመመልከት ፤ እንደ ገና ፡ ደግሞ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ ማሻሻልና ፡ ለሚመጣው ፡ ዘመን ፡ በቂ ፡ መሪነት ፡ የሚኖረው ፡ ሕገ ፡ መንግ ሥት ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ተረድተን ፡ አዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ስንሰጥ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው» ሲሉ ፡ የተናገሩት ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድናቆትን ፡ ባስከተለው ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ አሻሽለው ፡ የሰጡት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያደረገችውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርምጃና ፡ መሻሻል ፡ የሚያስ ረዳ ፡ ከመሆኑም ፡ በቀር ፡ መጀመሪያ ፡ ከተሰጠው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ይበልጥ ፡ የተሻሻለና ፡ ለዘመኑ ፡ ተስ ማሚ ፡ የሆነ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አሻሽሎ ፡ መስጠት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዘመናዊ ፡ ኑሮ ፡ የቀን ፡ ያህል ፡ ጥቅም ፡ እንደሚያስገኝ ፡ ለመረዳት ፡ አዳጋች ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ። በ፩፻፴፩ ፡ አንቀጽ ፡ የተመደበው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፵፱ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ አዋጅ ፡ ጸድቆ ፡ በጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፲፭ኛው ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አፈሲዬል ፡ በሆኑት ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋዎች ፡ ታትሞ ፡ ይገኛል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ያደረጉት ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ በኢትዮጵያና ፡ በፈረንሳዊ ፡ ንግድ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አማካይነት ፡ በፈረንሳዊኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጕሞ ፡ ፓሪስ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ቍ ፡ ፴፩ ፡ ከገጽ ፡ ፲፩ ፡ እስከ ፡ ፳፭ ፡ ይገኛል ። እኛም ፡ (ግራ-ዥን) ላቪ ፡ ዡሪዲስየር ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ በኦክቶበር፡ ፲፱፻፶፭፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በቍጥር ፡ ፪፻፵፭—፪፻፵፮ ፡ በገጽ ፡ ፲፭—፳፫ ፡ እና ፡ ፳፭—፴ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩና ፡ አዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በሚል ፡ እርእስታችን ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየታችንን ፡ ገልጸናል ። ከዚ ህም ፡ በቀር ፡ በማድሪድ ፡ ከተማ ፡ ሬቪስታ ፡ ደ ፡ ማድሪድ ፡ እስትሪያ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ ቍጥር ፡ ፵፯—፵፰ በእስፓኛል ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጕሞ ፡ ታትሟል ።

[30] ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የመንግሥታቸው ፡ የሥራ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑት ፡ የየክፍሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በሙሉ ፡ ተሰብስበው ፡ በተገኙበት ፡ የመጀመሪያውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በፊርማቸው ፡ ባጸደቁ ፡ ጊዜ ፡ ባደረ ጉት ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ ላይ ፡ እንደገለጹት ፡ «ሕግ ፡ ለሰው ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የሚጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ አይስተውም ። መከበር ፡ መጠቀምም ፡ የሚገኙት ፡ በሕግ ፡ መተካከል ፡ የተነሳ ፡ ነው ። መዋረድም ፡ መጎዳትም ፡ የሚመጡት ፡ ከሕግ ፡ መጓደል ፡ የተነሳ ፡ ነው ። ግፍና ፡ በደል ፡ የሚበዙት ፡ ሕግ ፡ ባለመቆሙ ፡ ነው ። ...» ብለው ሲናገሩ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተገለጹትን ፡ መሠረታዊያን ፡ ነገሮች ፡ አቁመዋል ። ... ፩ኛ ፡ የሕግ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ወይም ፡ ቀጭንነቱ ፡ ለማንም ፡ ቢሆን ፡ የማያዳላ ፡ ትክክል ፡ እንዲሆን ፡ ... ፪ኛ ፡ ሕግ ፡ ማስፈለጉ ፡ ማንኛውም ፡ የትዳር ፡ አኳኋን ፡ ተሻሽሎ ፡ የተደላደለና ፡ በታመነ ፡ መሠረት ፡ እንዲሆን ፡ ነውና ፡ ሁሉንም ፡ አሻሽሎ ፡ የሚያደላድል ፡ ዕውቀት ፡ ነው ። የኢትዮጵያም ፡ አስተዳደር ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ወደ ፡ ዕውቀትና፡ወደ፡ሲቪሊዜሽን፡ ጥበብ፡የተመራ፡ እንዲሆን፡ ... ፫ኛው፡ መሠረታዊ፡ አሳብ፡ ደግሞ፡ ይህን፡ኃይለ፡ቃል፡ ስንዘጋ፡የምንገልጸው፡ነው። (ከዚህ፡ቀደም፡የጠቀስነውን፡የገርንጕል፡ዲፕሬይን፡ ድርሰት፡ ገጽ፡ ፹፫ ፡ ተመልከት) ።

ኢትዮጵያ ፡ ለዛሬው ፡ ሲፃንቲፊካዊ ፡ (የሥነ ፡ ፍጥረቶች ፡ ትክክለኛ ፡ ምርምር ፡ ዕውቀት) ዘመን ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ አውጥታ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ያላትን ፡ ፍላጎት ፡ የሚመሰክር ፡ ሲሆን[31] ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ ከማድረግ ፡ ልምድ ፡ የተገኘው ፡ ዕውቀት ፡ ቅርስ ፡ (ኤክስፔሪያንስ) መታሰቢያነቱን ፡ ይዞ ፡ መኖር ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ባለመዘንጋት ፡ ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣው ፡ ወደር ፡ የሌለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ባሕላዊ ፡ እምነት ፡ ለዘመናዊው ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ የመነሻ ፡ ነጥብ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። ስለዚህ ፡ ሕጉ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ የትክክለኛነታቸው ፡ ዝና ፡ የታወቀላቸው ፡ ቢሆን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ መገልበጥ ፡ እነዚህ ፡ ዝነኛ ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱት ፡ ባዕድ ፡ ሕጎች ፡ የመነጩበትንና ፡ በጊዜ ፡ ብዛትም ፡ እየተሻሻሉ ፡ ተጣርተው ፡ የተገኙበትን ፡ ታሪክና ፡ የፖለቲካ ፡ ምንጭ ፡ አገልግሎታቸው ፡ የተመደበው ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ባሕል ፡ ላለው ፡ ሕዝብ ፡ መሆኑን ፡ ያለመገመትና ፡ በቀጥታ ፡ ተወስደው ፡ ለሌላ ፡ ቢሰጡም ፡ እጅግ ፡ ልዩነትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ በመሆናቸው ፡ ጉዳትን ፡ እንጂ ፡ ጥቅምን ፡ የማያስገኙ ፡ መሆናቸውን ፡ እንዳለመገንዘብ ፡ ይቆጠራል።

ሕግ ፡ ሲባል ፡ የባሕል ፡ መታሰቢያ ፡ መስታዮት ፡ መሆንና ፡ እንዲሁም ፡ ይህንኑ ፡ ባሕል ፡ የሚያሻሽልና ፡ አጽድቆ ፡ የሚያኖር ፡ ሐውልት ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። አንድ ፡ አገር ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የሚቆጠር ፡ የግል ፡ ጠባይና ፡ የግሉ ፡ የሆነ ፡ ፍላጎት ፡ ያለው ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ጤናማ ፡ እድገቱንና ፡ ሕብረታዊ ፡ እርምጃውን ፡ እንዲያገኝ ፡ የተረጋገጠ ፡ ዋስትና ፡ ለመስጠት ፡ ይህንኑ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ መከተል ፡ ተገቢ ፡ መሆኑ ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ።

ይህም ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ እርቆ ፡ አስተዋይ ፡ የሆኑት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የመጀመሪያውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ባወጁ ፡ ጊዜ ፡ "ይኸውም ፡ ያቆምነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ሳይሆን ፡ ከአገር ፡ ልማድ ፡ ሳይፋለስ ፡ ከሰለጠኑት ፡ መንግሥት ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ የተያያዘና ፡ የተቀራረበ ፡ ስለሆነ ፡ ከመሳፍንቶቻችንና ፡ ከመኳንንቶቻችን ፡ እውቀት ፡ ካላቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተወላጆችም ፡ አሳቡን ፡ እየረዱን ፡ ተስማምተንበታል" ሲሉ ፡ በተናገሩት ፡ ቃል ፡ ተገልጾ ፡ እናገኘዋለን ። በንግግራቸውም ፡ ውስጥ ፡ "ሰው ፡ ይጀምራል ፡ እንጂ ፡ የመጨረስ ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው ፤" የሚለው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ አግኝቶ ፡ ለሁሉም ፡ ነዋሪና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅምን ፡ የሚያስገኝ ፡ በመሆን ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ የሚተላለፍ ፡ እንደሚሆን ፡ በአጀማመሩ ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ እንግዲህ ፡ አዲሱን ፡ ሕግ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ባጭሩ ፡ ተፈላጊና ፡ ተስማሚ ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ የመነሻ ፡ ነጥብ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ መሠረታዊና ፡ ፍጹም ፡ ብሔራዊ ፡ በመሆን ፡ ለአገሪቱ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ባሕላዊ ፡ ልማድና ፡ በአፈጻጸሙም ፡ ረገድ ፡ ለጊዜውና ፡ ለአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ ማዘጋጀት ፡ አስገዳጅ ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ማስረጃ ፡

---

[31] አዲሶቹን ፡ ሕጎች ፡ ያዘጋጁት ፡ ሊቃውንት ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ፤-

ለንግድ ፡ ሕግና ፡ ለባሕር ፡ ሕግ ፡ ረቂቆች ፡ ማዘጋጀት ፡ ሥራ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዣን ፡ ኤስካራ ፡ (ፓሪስ) ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ለግዴታዎች ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬኔ ፡ ዳቪድ ፡ (ፓሪስ) ፡ ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ (ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አቋቋምና ፡ ስለ ፡ ሥልጣን ፡ ድልድል) ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕጎች ፡ ረቂቅ ፡ ድርጅት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዣን ፡ ግራቨን ፡ (ዠኔቭ) ነበሩ ፤ በኋላም ፡ የንግድን ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ አዘጋጅተው ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ከማድረሳቸው ፡ በፊት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዣን ፡ ኤስካራ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ስለተለዩ ፡ ፕሮፌሰር ፡ አልፍሬድ ፡ ዠፍሬ ፡ (ኤክስ—ማርሴይ) የተጀመረውን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ አደረሱት ።

ማቅረብ ፡ አይቻልም ። ይህ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነው ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እንደገና ፡ የማደስ ፡ ተግባር ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ እምነት ፡ አክብሮ ፡ የመጠበቅን ፡ ግዴታ ፡ የሚያስከትል ፡ እንደመሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ሊጠቅም ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበብና ፡ ዘዴ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነው ፡ እየተመረጠ ፡ በመቀላቀል ፡ ለሕጉ ፡ አቋም ፡ ሕይወትን ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማድረግ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የተቋቋመው ፡ ኮሚሲዮን [32] ፡ እርዳታ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድጋፍ ፡ የሰጠው ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከፍተኛ ፡ መሰና ክል ፡ የገጠመው ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ለመድረስ ፡ በቅቷል ። የሥራውም ፡ ክንውን ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ እንደተገመተ ፡ ስንመኝ ፡ እንዲሁም ፡ ለሕግ ፡ አዘጋጅነት ፡ የተቋቋመውም ፡ ኮሚሲዮን ፡ ሆነ ፡ የሁለቱ ፡ ፓርለማ ፡ አባሎች ፡ ጉባኤ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እውነተኛ ፡ ፍላጎት ፡ የሚበቃ ፡ ልማድና ፡ ባሕ ልዋንም ፡ የጠበቀላት ፡ ለአዲሱ ፡ ዘመን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ የሚስማማ ፡ ሳለፈው ፡

[32] የሥራውን ፡ አቋቋምና ፡ የእርምጃውንም ፡ መከናወን ፡ ድርጅት ፡ ረቡው ፡ ፔናል ፡ ሱዊስ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በጻፍነው ፡ በገጽ ፡ ፩፻፪ ፡ እና ፡ በተከታዩ ፡ ላይ ፡ ገልጸናል ። ይህም በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተቋቋመው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ከፍ ተኛ ፡ ጉባኤ ፡ ፳፭ ፡ የሚሆኑ ፡ አባሎች ፡ ነበሩት ፤ ከነዚሁም ፡ አብዛኞቹ ፡ ኢትዮጵያዊያን ፡ ሊቃውንቶች ፡ ሲሆኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ ያሉበት ፡ ነው ። ከአባሎቹም ፡ መካከል ፡ የሕግ ፡ የዳኝነትና ፡ የንግድ ፡ አስተዳደር ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ይገኙባቸዋል ። የተሰጣቸውም ፡ ሥራ ፡ ሦስቱ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ አዘጋጅ ፡ የሆኑት ፡ ሊቃውንቶች ፡ (ኤክስፐርቶች) የሚያዘጋጁትን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ መመርመርና ፡ በጉባኤው ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ አሳብ ፡ በመስጠት ፡ አንዱ ፡ ሕግ ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ሳይጋጭ ፡ በተመሳሳይነትና ፡ በኅብረት ፡ እንዲራመድ ፡ በመ ቆጣጠርና ፡ በመጠባበቅ ፡ ሥራውን ፡ በቅርብ ፡ እየተከታተሉ ፡ በመምራትም ፡ በጉባኤ ፡ እየተሰበሰቡ ፡ ረቂቆ ቹን ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ማጽደቅ ፡ ነው ። ይህ ፡ ጉባኤም ፡ የአገሩን ፡ ጥንታዊ ፡ ባሕል ፡ ጠንቅቀው ፡ የሚያውቁ ፡ ከፍተኛ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንቶች ፡ የታላላቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ የፍርድ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዢዎች ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በማገልገል ፡ ኤክስፔሪያንስ ፡ ያደረጉ ፡ የመንግሥት ፡ የሕግ ፡ አማካሪዎች ፡ የሆኑ ፡ ኤውሮፓዊያን ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንቶችና ፡ ከፍተኛ ፡ ዳኞች ፡ ጠበቆች ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ መሪዎች ፡ የእንዱስ ትሪና ፡ የንግድ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ መሪዎች ፡ ያሉበት ፡ ነው ። ኮሚሲዮኑ ፡ በሚቀርብለት ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ላይ ፡ ጠቅላላ ፡ አሳቡን ፡ የመስጠትና ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሕግ ፡ ዝግጅት ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ የሥራ ፡ ውጤት ፡ ነጥብ ፡ የማስያዝ ፡ ሥልጣን ፡ ነበረው ። የሕጉ ፡ አርዕስቶች ፡ ሥራ ፡ ከተጣራ ፡ በኋላ ፡ ለወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ዝግጅት ፡ ምርመራ ፡ እንደተደረገው ፡ ዐይነት ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ለፓርላማ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ በጠቅላላ ፡ አሳቡ ፡ ላይ ፡ ተነጋግሮና ፡ አሳብ ፡ ለአሳብ ፡ ተለዋውጦ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ ነበረበት ። የሕ ጉን ፡ ረቂቅ ፡ የማዘጋጀት ፡ የዕለትና ፡ የዘወትር ፡ ሥራ ፡ ለሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ ምክትል ፡ ኮሚቴ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ እዚያው ፡ በሕግ ፡ ማዘጋጃው ፡ ክፍል ፡ ነዋሪ ፡ ሆኖ ፡ የተቋቋመ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ስላለው ፡ አባሎቹ ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ የሚቀርበውን ፡ ረቂቅ ፡ በቅርብ ፡ እየተከታተሉና ፡ እያጣሩ ፡ ለጠቅላላው ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሚቀ ርበውን ፡ የመጨረሻ ፡ ረቂቅ ፡ እየመረመሩ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጡበታል ። ይህም ፡ ቅልቅል ፡ በሆኑ ፡ አባሎች ፡ የተቋቋ መው ፡ ምክትል ፡ ኮሚቴ ፡ ከጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የተውጣጣ ፡ ሆኖ ፡ አባሎቹ ፡ ከኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በኩል ፡ የሀገሩን ፡ ባሕልና ፡ ሕጉን ፡ ጠንቅቀው ፡ የሚያውቁ ፡ ከፍተኛ ፡ ሊቃውንቶች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ከሆኑት ፡ ደግሞ ፡ የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንቶችና ፡ ዳኞች ፡ ሆነው ፡ ከነዚህ ፡ መካከል ፡ እኩሉ ፡ አንግሎ ፡ ሳክ ሰን ፡ የተባለውን ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ የሚደግፍ ፡ ሲሆን ፡ እኩሉ ፡ ደግሞ ፡ ኮንቲናንታል ፡ የተባለውን ፡ የፈረንሳዊ ፡ ምንጭ ፡ የሆነውን ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ የሚደግፉ ፡ ነበሩ ፤ ስለሆነም ፡ በሕግ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ረገድ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ተኛ ፡ የሆን ፡ የትምህርት ፡ ደረጃና ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ሊቃውንቶች ፡ ነበሩ ። በዚህም ፡ ሁኔታ ፡ ድርዋ ፡ ኮንፓሬ ፡ የተባለው ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበብ ፡ በጥንቃቄ ፡ ሊከናወን ፡ ችሏል ። ምክትል ፡ ኮሚቴ ፡ የተባለው ፡ ጉባኤ ፡ በክቡር ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሰብሳቢነት ፡ ከኤክስፔርቱ ፡ ጋር ፡ ስብሰባ ፡ ያደርግ ፡ ስለነበረ ፡ ለሥራው ፡ መልካም ፡ እርምጃ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠ ውን ፡ እርዳታና ፡ ድጋፍ ፡ ያደረገ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አፈጻጸሙንም ፡ በቅርብ ፡ እየተከታተለ ፡ በመምራት ፡ ያደረገው ፡ እርዳታ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ዝርዝር ፡ ምርመራ ፡ (ትርጉሙንም ፡ ጭምር) በመከታተልና ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ በማጣራት ፡ የመጨረሻ ፡ ነጥቡን ፡ እንዲያገኝ ፡ እያደረገ ፡ አሳቡ ፡ ኢትዮጵያዊ ውን ፡ ጠባይ ፡ እንዳይለቅ ፡ እየጠበቀ ፡ አጣርቶና ፡ አጠናቆ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሆነው ፡ የኤክስፔርቶቹ ፡ ረቂቅ ፡ በተጣራ ፡ ሁኔታ ፡ ለፓርለማ ፡ እንዲቀርብ ፡ ያደረገው ፡ ይኸው ፡ ምክትል ፡ ኮሚቴ ፡ ነው ። ትክክለኛውንና ፡ መል ካሙን ፡ የመከተልና ፡ ተከትሎም ፡ ወዳሰበው ፡ ግብ ፡ ለማድረስ ፡ የነበረው ፡ ቅን ፡ መንፈስ ፡ «ኤኩዊኤት ፡ ቦኒ» የሚለውን ፡ የሮማዊያንን ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበብ ፡ ለራሱ ፡ ባሕልም ፡ መሠረት ፡ አድርጎት ፡ በመገኘቱ ፡ የተሻ ለውንና ፡ የሚቻለውን ፡ በመፈለግ ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ኃይል ፡ ሳይቆጥብ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ወዳሰበበት ፡ ዐላማ ፡ እንዲደርስ ፡ ለማድረግ ፡ የቻለው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ምክትል ፡ ኮሚቴ ፡ የእውነተኛ ፡ ድካሙ ፡ ውጤት ፡ ነው ።

ታሪክና ፡ ለመጪውም ፡ ጊዜ ፡ አጥጋቢ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ አምኖበት ፡ የተቀበለ ውና ፡ ያጸደቀው ፡ ስለሆነ ፡ ውጤቱ ፡ አስደሳች ፡ እንደሆነ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

## (ለ) <u>አዲሱ ፡ ሕግ ፡ አቋሙ ፡ መሠረታዊያን ፡ ሐሳቦቹና ፡ መንፈሱ</u> ፡—

በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፷፫ኛ ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ ቀን ፡ ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታወጀው ፡ አዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ካሉት ፡ አዲስ ፡ ሕጎች ፡ የመጀመሪያ ፡ ሆኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የነጻነት ፡ ባዓል ፡ መታሰቢያ ፡ በተከበረበት ፡ ጥንታዊ ፡ የንጉሥ ፡ አገዛዝ[33] ፡ መንግሥቱዋ ፡ ተመልሶ ፡ በተቋቋመበት ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ። የዚህም ፡ የአዲስ ፡ ዘመን ፡ ሕግ ፡ ከፍተኛ ፡ ጠቃሚነት ፡ ሕጉ ፡ በታወጀበት ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባደረጉት ፡ ንግግርና ፡ የሕጉ ፡ መጽሐፍ ፡ አርእስት ፡ ሆኖ ፡ በታተመው ፡ ቃላቸው ፡ ላይ ፡ የተገለጸ ፡ ስለሆነ ፡ በታሪክ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጠቃሚነት ፡ በመገመት ፡ ይህንኑ ፡ ቃል ፡ በሙሉ ፡ ገልብጠን ፡ ከዚሁ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ አባሪ ፡ በማድረግ ፡ በመጨረሻ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ አሳትመነዋል ። በዚህም ፡ ንግግር ፡ ውስጥ ፡ “የሕግን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ ሰብስቦና ፡ በአንድ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ቀምሮ ፡ መወሰን ፡ በማናቸውም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ አስቸጋሪ ፡ ተግባር ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ሕጉ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ከአገሩ ፡ ሕይወትና ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ በጽኑ ፡ ተመሥርቶ ፡ እንዲገኝ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ በሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ፍትሕን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዛሬ ፡ በእኛ ፡ ዘመን ፡ ያለውን ፡ የሕዝባችንንና ፡ ከእኛም ፡ በኋላ ፡ የሚመጣውን ፡ የትውልድ ፡ ኑሮ ፡ እየለወጠ ፡ ከሚሄደው ፡ ከማኅበራዊ ፡ ሕይወት ፡ ከኤኮኖሚክና ፡ ከሲያንቲፊክ ፡ (ከሥነ ፡ ፍጥረቶች ፡ ትክክለኛ ፡ ምርምር ፡ ዕውቀት) ኃይሎች ፡ ጋር ፡ እየተስማማ ፡ መሄድ ፡ ስላለበት ፡ ነው ። በዓለም ፡ ላይ ፡ የሳይንስ ፡ ጥበብ ፡ እያደገ ፡ በመሄዱ ፡ መጠን ፡ ለዘመናዊው ፡ ኑሮ ፡ ያበረከታቸው ፡ የተወሳሰቡ ፡ ነገሮች ፡ በተስፋፉበትና ፡ የሕጎች ፡ ብዛት ፡ እያደገ ፡ በሄደበት ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ በደንብ ፡ ለማስኬድ ፡ የሚወጡት ፡ ሕጎች ፡ በሚገባ ፡ እንዲፈጸሙ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ በሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ነገር ፡ ርኅራኄንና ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ አስተያየትን ፡ የያዘ ፡ እንዲሆን ፡ ይገባል ። ማናቸውም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ፍትሕን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እያደጉ ፡ የሚሄዱትን ፡ አዳዲስ ፡ አሳቦች ፡ ማሰብ ፡ የተገባ ፡ ነው ። ተገቢ ፡ የሚሆነውም ፡ ፍትሕንና ፡ ነጻነትን ፡ ወንጀልን ፡ መከላከልንና ፡ መጨቆንን ፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ማድረግን ፡ የያዙትን ፡ መሠረታዊያኑን ፡ ነገሮች ፡ መንፈስ ፡ በመከተል ፡ ነው ። ቅጣት ፡ ግድ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፡ ደግሞም ፡ ‘አጥፊ ፡ ሲቀጣ ፡ የሚያየው ፡ ብልህ ፡ ይሆናል’ እንደተባለው ፡ ሁሉ ፡ ለሌላው ፡ አጥፊ ፡ ትምህርት ፡ እንዲሆን ፡ ነው ። ይህ ፡ ዛሬ ፡ በአዋጃችን ፡ ያወጣነው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ከሚሰጣቸው ፡ ከነዚህ ፡ መሠረታዊያን ፡ አሳቦች ፡ ጋር ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ የተስማማ ፡ ሆኖ ፡ ባሁኑም ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡ በመጭው ፡ ትውልድ ፡ ለተወደዱት ፡ ዜጎቻችን ፡ እንዲገኝላቸው ፡

[33] ሞአ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ... በነገሥን ፡ በ፳፬ኛው ፡ ዓመት ፡ ዛሬ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ተሰጠ ፡ .... ልዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ሆኖ ፡ በተለይ ፡ በወጣው ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፵፰ ፡ የ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣ ፡ ልዩ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ አዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ አቋም ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ <u>ረቩዊ ፡ እንቴርናሲዮናል ፡ ደ ፡ ፖሊቲክ ፡ ክሪሚኔል</u> ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ኒዮርክ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (አ ፡ ኤ ፡ አ) ቍጥር ፡ ፲፪ ፡ ሌዢስላሲዮን ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲—፩፻፲፬ ፡ እና ፡ ፩፻፲፰ ፡ የሰጠነውን ፡ መግለጫ ፡ ተመልከት ።

በማሰብ ፡ እኛም ፡ ራሳችን ፡ አላፊነቱን ፡ ወስደን ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አደረ ግን ፤” የሚል ፡ ቃል ፡ የሚገኝበት ፡ ሲሆን ፤-

እንግዲህ ፡ ለሕጉ ፡ መግቢያ ፡ መቅድም ፡ እንዲሆን ፡ በመጀመሪያው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ እንደተፈጸመና ፡ ይህንን ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የሕጉ ፡ ጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ በጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ መሥመሩ ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ እንደተከናወነ ፡ የአዲሱ ፡ ዘመንስ ፡ የወንጀለኛ ፡ አቀጣጥ ፡ ፖሊቲካ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ ትክክለኛውን ፡ ፍች ፡ ለማግኘት ፡ እንዲቻል፡ ለመረዳት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ መግለጫዎች ፡ እንመልከት ።

<u>፩ ፤ የሕጉ ፡ አመሠራረትና ፡ የአሠራሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ቅንጅት ፡ (ሲስቴም) ።</u>

1. የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ለሥራው ፡ ውጤት ፡ ከንውን ፡ መሠረታዊ ፡ ነጥብ ፡ አድርጎ ፡ የተነሣው ፡ ለአገሩ ፡ ጸጥታና ፡ ለወደፊት ፡ እድገቱ ፡ ለነዋሪውም ፡ ሕዝብ ፡ ዕድል ፡ የሚያገለግል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ከፍተኛነት ፡ ያለው ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ግልጽ ፡ የተሟላና ፡ በጥንቃቄ ፡ የተስተካከለ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡ የሚለውን ፡ ሐሳብ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሕጉ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥፋቶች ፡ እንዲሁም ፡ በአድራጊዎቹ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙትን ፡ ቅጣቶችና ፡ ጥንቃቄዎች ፡ አስተካክሎ ፡ ይወስናል ፡ (የወ ፡ መ ፡ ሕ ፡ ቍጥር ፡ ፪) የሚል ፡ ቃል ፡ የተጻፈበት ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ ወንጀልን ፡ ለሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ በዘልማድ ፡ የሚሠራውን ፡ የፍርድ ፡ አካሄድ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማስቀረትና ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ሥርዓት ፡ ከሕጉ ፡ የመነጨ ፡ እንዲሆን ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ ለዳኞችና ፡ ለሕዝብም ፡ እውነተኛ ፡ መምሪያ ፡ ለመሆን ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከዛሬ ፡ ዘመን ፡ ሕጎች ፡ እንዲያውም ፡ ታላላቅ ፡ ከሚባሉት ፡ መካከል ፡ አብዛኞቹ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ በሆኑት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ጉድለት ፡ ይገኝባቸዋል ፡ ለምሳሌ ፡ የብሔራዊው ፡ ሕግ ፡ ከሌላው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በሚገናኝበት ፡ የአፈጻጸም ፡ ሥልጣን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ የማይሠራ ፡ ስለመሆኑ ፡ ከሕጉ ፡ ስለመለየት ፡ የተሻለውን ፡ ሕግ ፡ መርጦ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለማድረግ [34] ፡ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ትርጓሜ ፡ የሕግ ፡ መጣሱ ፡ ተግባር ፡ ስለተሠራበት ፡ ጊዜና ፡ ወንጀል ፡ ስለተፈጸመበት ፡ ስፍራ [35] ፡ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ በሐሳብና ፡ በግዙፍ ፡ ሁኔታ ፡ ስለመተባበር ፡ ስለ ፡ ግብረ ፡ አበርነት [36] ፡ በሕግ ፡ ስለተፈቀዱ ፡ ስለማያስቀጡና ፡ ይቅርታ ፡ ስለሚያሰጡ ፡ ወንጀሎች ፡ ለወንጀል ፡ ሥራ ፡ አላፊ ፡ ስለመሆንና ፡ ስላለመሆን ፡ በሕግ ፡ ስለተፈቀዱ ፡ የቅጣት ፡ ማቅለልና ፡ የማክበድ ፡ ሁኔታዎች [37] ፡ ወይም ፡ ቅጣትን ፡ ስለማ

---

[34] አዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የሕጉን ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ሕጉ ፡ የሚጸናበትን ፡ የጊዜ ፡ ሁኖቴ ፡ አጠናቆ ፡ በመግለጽ ፡ ያመለክታል ፡ ከቍጥር ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፳፱ ።

[35] ከቍጥር ፡ ፳፫ ፡ እስከ ፡ ፳፭ ፡ የተገለጸውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

[36] የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ በመደበኛውም ፡ ነገር ፡ ሆን ፡ ከቍጥር ፡ ፴፪ ፡ እስከ ፡ ፵ ፡ ታትመው ፡ በሚወጡ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ ከቍጥር ፡ ፵፩ ፡ እስከ ፡ ፵፯ ፡ ዘርዝሮ ፡ በግልጽ ፡ ያመለክታል ።

[37] ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ የተመደበው ፡ ክፍልና ፡ ከቍጥር ፡ ፷፪ ፡ እስከ ፡ ፹፱ ፡ ለተቀጭንትና ፡ በወንጀል ፡ አላፊነት ፡ ያሉትን ፡ ግንኙነቶች ፡ በሚመለከት ፡ ረገድ ፤ ከቍጥር ፡ ፵፰ ፡ እስከ ፡ ፷፫ ፡ ይህም ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ከቍጥር ፡ ፩፻፹፫ ፡ እስከ ፡ ፩፻፺፱ ፡ አንድ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ተመድቦለታል ።

ቆምና ፡ የተወሰነውን ፡ ቅጣት ፡ በገደብ ፡ ስለማቆየት [38] ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ስለ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ነጥቦች ፡ ሳያሟሉ ፡ የተጻፉ ፡ ሕጎች ፡ በመገኘታቸው ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ አሳዛኝ ፡ ጉድለት ፡ እንዳይገኝበት ፡ አስበን ፡ በማሟላትና ፡ በማረም ፡ አጥጋቢ ፡ በሆነ ፡ ዓይነት ፡ እንዲቀርብ ፡ በተለይ ፡ አስበን በታል ። በኤሮፓ ፡ አገሮች ፡ ሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ግዙፍ ፡ ጉድለት ፡ ለምን ፡ ተደረገ ፡ ተብሎ ፡ ለሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ የሚሰጠው ፡ ምላሽ ፡ የረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ እምነት ፡ (ዶክትሪን) ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ልምድ ፡ የተፈረዱ ፡ ነገሮችን ፡ ሰብስበው ፡ የያዙ ፡ የጕሪስፕሩዳንስ ፡ (የሰው ፡ ልጅ ፡ ፍጹም ፡ ሕግ ፡ አስተዳደር ፡ ፍልስፍና) ጽሑፎች ፡ በብዙ ፡ ስለሚገኙና ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ያለችግር ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ እንዲችል ፡ በመደረጉ ፡ እንዲሁም ፡ ቍጥራቸው ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ የሕግ ፡ ጠቀስ ፡ ድርሰቶች ፡ ተለቅመውና ፡ ተጠራቅመው ፡ በመታተማቸው ፡ በብዛት ፡ ስለሚገኙ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ስለሚያውቃቸው ፡ የሕግ ፡ ማብራሪያ ፡ ጽሑፎችና ፡ የመማሪያ ፡ መጻሕፍት ፡ በመገኘታቸውም ፡ የሕጉን ፡ ትርጓሜ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ያለችግር ፡ መረዳት ፡ ስለሚቻል ፤ ከዚህም ፡ ለተረፈው ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተቋቋሙት ፡ አጠራጣሪና ፡ አከራካሪ ፡ የሆኑትን ፡ የሕግ ፡ ነጥቦች ፡ እየተረጐሙና ፡ እያብራሩ ፡ የማያጠራጥር ፡ ትርጉም ፡ በመስጠት ፡ ለመወሰን ፡ ስለሆነ ፡ አንዳንድ ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ የማይታዩ ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ጉዳዮችም ፡ ሳይሟሉ ፡ ቢቀሩ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እንደሚብራሩ ፡ ይታመናል ፡ የሚል ፡ ነው ። ሲያንስ ፡ ጕሪዲክና ፡ ጕሪስፕሩዳንስ ፡ (የዳኝነትና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ፍጹም ፡ ሕግ ፡ አስተዳደር ፡ ፍልስፍና ፡ ምርምር ፡ ዕውቀት) ከፍ ፡ ወዳለ ፡ ደረጃ ፡ የደረሱ ፡ ስለሆነ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ ሆነው ፡ የዚሁ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ እንደሆኑ ፡ ያህል ፡ ሊቆጠሩ ፡ ይገባቸዋል ፡ የሚል ፡ እምነትም ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ በሌሉበትና ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከጥንታዊ ፡ ባሕልና ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ ጨርሰው ፡ ካልተላቀቁ ፡ አገሮች ፡ የአዲሱ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ መንፈስ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ስለሚሆንባቸው ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ውስጥ ፡ የተሻሻለው ፡ ጨርሶ ፡ የቀረው ፡ ወይም ፡ የተለወጠው ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ የትኛው ፡ እንደሆነ ፡ ገልጾ ፡ ማብራራት ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆናል ፤ ስለዚህ ፡ ሕጉ ፡ ተሟልቶ ፡ በጽሑፍ ፡ ሠፍሯል ፡ ዳኞች ፡ የሕግ ፡ ሰዎችና ፡ ፍርድ ፡ ጠያቂዎችም ፡ ያላንዳች ፡ ድካምና ፡ ችግር ፡ በማንኛውም ፡ ነጥቡ ፡ ሊገለገሉበት ፡ ሊጠቅሱትና ፡ ፍችውንም ፡ በቀላሉ ፡ ሊረዱት ፡ ይችላሉ ።

(ሀ) የሕጉ ፡ መጽሐፍ ፡ አሠራር ፡ ቅንጅት ፡ ሁሉ ፡ ዘወትር ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዓይነት ፡ በክፍሎች ፡ በንኡስ ፡ ክፍሎች ፡ በቍጥሮችና ፡ በንኡስ ፡ ቍጥሮች ፡ የተመደበ ፡ ሆኖ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ የሚያቀራርበው ፡ ግንኙነት ፡ በግልጽ ፡ ስለሚታይና ፡ ለየአንዳንዱም ፡ ቍጥር ፡ የየራሱ ፡ አርእስት ፡ ተሰጥቶት ፡ ስለሚገኝ ፡ አመዳደቡ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ዓላማ ፡ የሚያዘነብል ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በአሁኑ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ቤሎ ፡ የተባለው ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ የዤኔቭን ፡ የሕግ ፡ ጽሑፍ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ እንዲሁም ፡ በቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ ኤውገ*ን ፡ ሑቤርና ፡ ካርል ፡ እስቱስ ፡ የሱዊስን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሲያዘጋጁ ፡ የተከተሉትን ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ጥበብ ፡ ምሳሌ ፡ አድርገን ፡ በመከታተል ፡ ይህንንም ፡ ሕግ ፡ ባዘጋጀንበት ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ መደበኛውን ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከተል ፡ በማድረግ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ያለችግርና ፡ በቀላሉ ፡ በሥፍራው ፡ እንዲገኝ ፡ ትርጉማቸው ፡ ያልተብራራና ፡ የሚያስቸግር ፡ ቃላት ፡ እንዳይኖሩበትና ፡ ሕዝባዊ ፡ ቋንቋ ፡ ሆኖ ፡ በተለመደው ፡ አነጋገር ፡ የተገለጸ ፡ እንዲሆን ፡ ኢትዮጵያም ፡ የዘወትር ፡ ልማዱዋ ፡ ሆኖ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሕግ ፡ ጽሑፍዋና ፡ የቤተ ፡

[38] ሁለት ፡ ንኡስ ፡ ክፍሎች ፡ ተመድበዋል ፡ ከቍ ፡ ፩፻፺፬ ፡ እስከ ፡ ፪፻፲፩ ፡ ከቍ ፡ ፪፻፲፪ ፡ እስከ ፡ ፪፻፵፯ ።

ክህነትና ፡ የሕግ ፡ ቋንቋዋ ፡ በሆነው ፡ በግእዝ ፡ አጻጻፍ ፡ ነገርን ፡ በምሳሌና ፡ በተረት ፡ የመተርጐም ፡ ባሕልዋ ፡ እንዲጠበቅላት ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ አድርገናል ።

እንደሌሎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጐች ፡ ክፍል ፡ ሁሉ ፡ አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግም ፡ እጅግ ፡ ዘመናዊ ፡ ከሆኑት ፡ ሌሎች ፡ ሕጐች ፡ ጋር ፡ ሊኖረው ፡ የሚገባውን ፡ ግንኙነትና ፡ ልዩነት ፡ በማስተያየት ፡ ጥናት ፡ በክሪሚኖሎጂ (የወንጀለኞችና ፡ የወንጀል ፡ ዕውቀት ፡ ጥናትና ፡ ምርምር) መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ የተቋቋመ ፡ ሆኖ ፡ እጅግ ፡ ቀላልና ፡ ለሁሉም ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በሚገባ ፡ አነጋገር ፡ የተዘጋጀ ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ ነው ።

በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥም ፡ ደግሞ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወንጀል ፡ በሚፈጸምበት ፡ ዓይነት ፡ የአፈጻጸሙን ፡ ሁኔታና ፡ የሚወሰነውንም ፡ የቅጣት ፡ ዓይነት ፡ ከአወሳሰኑ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ተገልጾ ፡ በመዘርዘርና ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጓሜውን ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቡን ፡ በመግለጽ ፡ አንዱን ፡ ከአንዱ ፡ በመለየትና ፡ በክፍል ፡ በንዑስ ፡ ክፍል ፡ በዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ በመመደብ ፡ እንዲገለጽ ፡ የተደረገበት ፡ ዋነኛው ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ መሆኑ ፡ ይታያል [39] ፡ እንዲሁም ፡ የአመዳደቡ ፡ ፈሊጥ ፡ ግልጽ ፡ እንዲሆን ፡ በተለይ ፡ ስለታሰበበት ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ አንዱ ፡ ነገር ፡ የተለየ ፡ ጉዳዩን ፡ ይዞ ፡ በየሥፍራው ፡ እንዲገኝ ፡ "መሠረቱ" ፡ በሚል ፡ ቃል ፡ እንዲነሳና ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ፍችው ፡ በዚያው ፡ አርዕስተ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ለመገኘት ፡ እንዲችል [40] ፡ መደበኛ ፡ ወይም ፡ ተራ ፡ ሊባሉ ፡ ከሚችሉት ፡ ወንጀሎች ፡ የተለዩ ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ ከሚባሉት ፡ ወንጀሎች ፡ መካከል ፡ በመውጣት ፡ ለየብቻቸው ፡ ተለይተው ፡ ለየራሳቸው ፡ በተመደበላቸው ፡ አንቀጽና ፡ ምዕራፍ ፡ ክፍልና ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተነጥለው ፡ እንዲገኙ ፡ በማድረግ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ማለት ፡ የተዛመደ ፡ ግንኙነትና ፡ ተመሳሳይነት ፡ ያላቸው ፡ ወንጀሎች ፡ በየዓይነታቸውና ፡ በየወገናቸው ፡ ተነጣጥለው ፡ ሥፍራ ፡ ሥፍራቸውን ፡ እንዲይዙ ፡ ተደርገው ፡ ይገኛሉ ። በዚህም ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ የተመደቡበት ፡ ጉዳዮች ፡ ለመጀመሪያ ፡ ተመልካች ፡ ባንድ ፡ አፍታ ፡ የሚገኙ ፡ መሆናቸውን ፡ ለማስረዳት ፡ ያህል ፡ ስለሰው ፡ መግደልና ፡ ስለአደራረጉ ፡ በተመደበው ፡ ምዕራፍ ፡ ያለውን ፡ ያጻጻፍ ፡ ዘዴ (ከቍጥር ፡ ፭፻፳፪ ፡ እስከ ፡ ፭፻፳፱) ፡ በፅንስ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ወንጀል ፡ ስለማስወረድ (ከቍጥር ፡ ፭፻፳፱ ፡ እስከ ፡ ፭፻፴፫) ፡ በሰው ፡ አካልና ፡ በሰው ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ወንጀሎች ፡ (ከቍጥር ፡ ፭፻፵፯ ፡ እስከ ፡ ፭፻፵፱) ፡ በሀብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ከቍ ፡ ፮፻፴፩ ፡ እስከ ፡ ፮፻፴፯) ፡ ወይም ፡ በዕዳ ፡ ምክንያትና ፡ በአከሣሥር ፡ ጉዳይ ፡ አሠራር ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፮፻፹ ፡ እና ፡ ተከታዩ) ፡ ምሳሌ ፡ አድርገን ፡ ጠቅሰናቸዋል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜም ፡ ሕጋዊው ፡ ድንጋጌ ፡ ራሱ ፡ በአንቀጽ ፡ ስም ፡ አቀማመጥ ፡ የቅጣት ፡ ማካበድን ፡ ወይም ፡ ማቅለልን ፡ ደንብ ፡ አለያይቶ ፡ የያዘ ፡ በመሆኑ ፡ ዳኛው ፡ ወዲያውኑ ፡ ሊያገኘው ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ የተሠራ ፡ ነው [41] ።

---

[39] የሕጉ ፡ እትም ፡ በቍጥሮቹ ፡ አቅጣጫ ፡ ሊገኝ ፡ ይገባው ፡ የነበረውን ፡ የአስተታተም ፡ ሥርዓት ፡ ሳይከተል ፡ በተቀላቀሉ ፡ ቍጥሮች ፡ አመዳደብ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ስፍራውን ፡ እንደያዘ ፡ በማየታችን ፡ የተሰማንን ፡ ቅሬታ ፡ እንገልጸለን ፡ ይኸውም ፡ ለአቀማመጡ ፡ መልካም ፡ አያያዝና ፡ ለጠቅላላ ፡ አቀራረቡ ፡ መልክ ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡ ያለመገኘቱ ፡ አሳዝኖናል ።

[40] ለምሳሌ ፡ ስለ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍሉ ፡ ቍጥር ፡ ፵፩ ፡ ፶፯ ፡ ፹፩ ፡ ፹፭ ፡ ፩፻፳ ፡ ፩፻፴፫ ፡ ፩፻፴፭ ፡ ፩፻፷፩ ፡ ፩፻፸ ፡ ፩፻፺፬ ፡ ፪፻፲፫ ፡ ፪፻፷፭ ፡ ፪፻፺፪ ፤ ለልዩ ፡ ክፍሉ ፡ ደግሞ ፡ ፬፻፲ ፡ ፭፻፳፩ ፡ ፭፻፴፯ ፡ ፭፻፸፬ ፡ ፮፻፷፯ ፡ ስለ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ ፯፻፴፫ ፡ እና ፡ ፯፻፸፫ ፡ ተመልከት ።

[41] እንዲሁም ፡ ቅጣትን ፡ ስለሚያከብዱ ፡ ሁኔታዎች ፡ ፪፻፸ ፡ ፫፻፴ ፡ እና ፡ ፫፻፴፬ ፡ ፫፻፶ ፡ ፫፻፹፩ ፡ ፫፻፺፩ ፡ ፬፻፳፯ ፡ ፭፻፲፫ ፡ እና ፡ ፭፻፲፮ ፡ ፭፻፸፪ ፡ ፭፻፹፯ ፡ ፭፻፺፰ ፡ ፮፻፩ ፡ ፮፻፭ ፡ እና ፡ ፮፻፳ ፡ ፮፻፳፪ ፡ ፮፻፶፩ ፡ እና ፡ ፮፻፶፩ ፡ ፮፻፸ ፡ እና ፡ ፯፻፸፰ ፡ ቅጣትን ፡ ስለማቅለል ፡ ፹፯ ፡ ፫፻፹ ፡ ፭፻፴፫ ፡ ፭፻፹፩ ፡ ፮፻፳፪ ፡ ቍጥሮችን ፡ ተመልከት ።

(ለ) የሕጉን ፡ አጻጻፍ ፡ ግልጽ ፡ ለማድረግ ፡ እጅግ ፡ የታሰበበት ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳው ፡ አንደኛው ፡ ነጥብ ፡ ደግሞ ፡ የዘመናዊ ፡ ሕጎች ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሥርዓት ፡ የሆነውን ፡ ግዙፍነት ፡ የሌለውን ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ ጠቅላላና ፡ ድርቅና ፡ የሌለው ፡ ትርጓሜ ፡ የመስጠትን ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ጥንታዊው ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ የተለያየ ፡ ቊጥር ፡ እየሰጡ ፡ ነገሩን ፡ መዘርዘር ፡ ለአንባቢዎች ፡ ዘወትር ፡ ከባድና ፡ እንዲያውም ፡ ጐዶሎነትን ፡ የሚያስከትል ፡ ሆኖ ፡ እንዳይገኝ ፡ ማድረጋችን ፡ ነው [42] ። አብዛኛውን ፡ ጊዜም ፡ በጠቅላላዎቹ ፡ አንቀጾች ፡ ውስጥ ፡ የሠፈሩት ፡ የሕጎቹ ፡ የአነጋገር ፡ ምስጢር ፡ ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ ፍችና ፡ ትርጓሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ በማድረግ ፡ የድንጋጌዎቹ ፡ ውጤትና ፡ ግብ ፡ የሕግ ፡ አውጭውም ፡ አሳብ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለአንባቢው ፡ በግልጽ ፡ እንዲገባው ፡ ተደርጓል ። በተለይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ ያልታወቁ ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ ፍች ፡ ያልተሰጣቸው ፡ አዲስ ፡ ወንጀሎች ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ተጽፈው ፡ በሚገኙበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሠሩበትን ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉበትን ፡ ድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ አብራርቶ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ለነገሩ ፡ እንግዳ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎችም ፡ ቢሆን ፡ ፍችአቸው ፡ በእጅ ፡ ሊዳሰስ ፡ በሚችልበት ፡ ዘዴ ፡ ለማስረዳት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ተገልጸው ፡ እንዲገኙ ፡ አድርገናል ። የዚህም ፡ የአዲሱ ፡ ሕግ ፡ መንፈስ ፡ የብሔራዊውን ፡ ሕይወት ፡ በጥልቅ ፡ የሚነካው ፡ ስለሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ጠቃሚነቱን ፡ እንደማይዘነጋው ፡ እናምናለን ።

የዘብ ፡ ጥበቃን ፡ የወታደር ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝን ፡ ታማኝነትን ፡ በማጓደል ፡ የወታደር ፡ ክብርን ፡ የሚቀንስን ፡ ወንጀል ፡ በመሥራት ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰንበትን ፡ ደንብ ፡ አስተካክሎ ፡ በመግለጽ (ቊ ፡ ፫፻፲፮ ፡ እና ፡ ፫፻፲፯ ፡ ፫፻፳ ፡ ከ፫፻፳፫ ፡ እስከ ፡ ፫፻፳፯ ፡ ፫፻፴፰ና ፡ ፫፻፴፱) ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የመንግሥትን ፡ ግብርና ፡ ቀረጥ ፡ ከመክፈል ፡ እምቢተኛ ፡ በመሆን ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ድፍረት ፡ በመፈጸም ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ በሞኖፖል ፡ ረገድ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቊጥር ፡ ፫፻፳ና ፡ ፫፻፳፩) ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ምልክቶችን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ በመለወጥ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፫፻፴፫) ምስክርን ፡ በማግባባት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፬፻፵፱) አንድ ፡ እሥረኛ ፡ እንዲያመልጥ ፡ በመርዳት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፬፻፶፯) የምርጫ ፡ ድምፅ ፡ የመስጠትን ፡ የመምረጥን ፡ መብት ፡ በመንካት ፡ ስለሚፈጸም ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፬፻፳፭ ፡ እስከ ፡ ፬፻፳፰) በምርጫ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የመደለያ ፡ ስጦታ ፡ ወንጀል ፡ የምርጫ ፡ ድምፅ ፡ በመስጠት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ የማጭበርበር ፡ ሥራ ፡ በአመዘጋገብ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚሠራ ፡ የማጭበርበር ፡ ወንጀል ፡ (፬፻፳፩) ወይም ፡ ደግሞ ፡ ወንጀለኛ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ አደጋን ፡ የሚያስከትል ፡ በመሆኑ ፡ የወንጀል ፡ ቅጣትን ፡ የሚያደርስ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ (ቊ ፡ ፬፻፸፭) ፡ የክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ ረዳትና ፡ መጠጊያ ፡ በመሆን ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፬፻፸፫) ፡ በተከለከሉ ፡ መጓሪያዎች ፡ በመነገድ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፬፻፸፮) ፡ የሕክምናንና ፡ የጤና ፡ አጠባበቅን ፡ ሥራ ፡ ያላገባብ ፡ በመሥራት ፡ ስለሚፈጸም ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፭፻፲፭) ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ በትክክል ፡ ያልተለዩ ፡ ወንጀሎችን ፡ ሁሉ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ አብራርቶ ፡ በመጻፍ ፡

[42] ይህን ፡ ለመረዳትና ፡ ነገሩን ፡ ለማመን ፡ ስለ ፡ ማጭበርበርና ፡ እምነትን ፡ ስለማጉደል ፡ የተጻፉትን ፡ የፈረንሳይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፬፻፭ ፡ እና ፡ ፬፻፳ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ስርቆትና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነቶቹ ፡ ስለ ፡ አመዳደቡ ፡ ሁኔታም ፡ ዝነኛ ፡ የሆነውን ፡ የዚሁ ፡ ሕግ ፡ ከቊጥር ፡ ፫፻፹፭ ፡ እስከ ፡ ፫፻፺፱ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ማንበብ ፡ በቂ ፡ ነው ። የዚሁ ፡ አጻጻፍ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ ግን ፡ የሱዊስ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሌብነትን ፡ በ፩፻፴፯ ፡ ውንብድናን ፡ ደግሞ ፡ በ፩፻፴፱ ፡ ቊጥር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ወስኖት ፡ ይገኛል ። የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ የተጠቃለለ ፡ ፍች ፡ የመስጠት ፡ ዐላማ ፡ እንዲኖረው ፡ የሚፈልግ ፡ በመሆኑ ፡ (ይህም ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ የመገኘት ፡ ሥርዓት) ስለሆነ ፡ ጉዳዩን ፡ በዝርዝር ፡ ያስረዳል ፤ ለምሳሌ ፡ ቊጥር ፡ ፭፻፴ ፡ እና ፡ ፭፻፴፭ ፡ ፭፻፴፮ ፡ እና ፡ ፭፻፴፯ ፡ ፭፻፵፭ ፡ እና ፡ ፭፻፶፱ ፡ ከ፭፻፺፰ ፡ እስከ ፡ ፭፻፺፱ ፡ ተመልከት ።

ረገድ ፡ ቅጣት ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ወንጀሎችና ፡ የቅጣቱን ፡ አወሳሰን ፡ ደንብ ፡ ለይቶ ፡ ማስረዳት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ በቃጠሎ ፡ ወይም ፡ በሚፈነዱ ፡ ነገሮች ፡ አደጋ ፡ ማድረስን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፬፻፹፫) ፡ በመገናኛዎችና ፡ በሕዝብ ፡ መሠላለሻ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (፬፻፺፱) ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ በሰው ፡ አካልና ፡ በሰው ፡ ጤና ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የማድረስ ፡ ወንጀሎችን ፡ (ቍ ፡ ፭፻፴፯) ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ሰውን ፡ በማይገባ ፡ አገል ጋይ ፡ ስለማድረግ ፡ (ቍ ፡ ፭፻፷፭) ፡ በመሸሸግና ፡ በመንጠቅ (ቍ ፡ ፮፻፴፯ና ፡ ፮፻፷፰) ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የሴት ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሰው ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ ተገዥ ነት ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ (ቍ ፡ ፭፻፺፫ና ፡ ፭፻፺፬) ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ የወንጀል ፡ አሠራር ፡ ዘዴዎች ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ግዙፍ ፡ በሆነ ፡ ዓይነት ፡ መግለጽና ፡ በዝርዝር ፡ ማስረዳት ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑ ፡ ተገምቷል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ የሐሰት ፡ ገንዘብን ፡ ባገር ፡ ስለማስገባት ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ስለመያዝ ፡ ከስፍራ ፡ ወደ ፡ ስፍራ ፡ ስለማዘዋወር ፡ ስለመያዝ ፡ በስጦታ ፡ ስለማቅረብ ፡ በጠቅላላው ፡ በገንዘብና ፡ በኤኮኖሚክ ፡ ረገድ ፡ በሕዝብ ፡ እምነት ፡ በመጠ ቀም ፡ የሚሠሩት ፡ ወንጀሎች ፡ ምን ፡ ዓይነቶች ፡ እንደሆኑ ፡ (፫፻፸) ፡ በግልጽ ፡ በማስ ረዳት ፡ መርዛም ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ በሰው ፡ ምግብም ፡ ሆነ ፡ በከብት ፡ ድርቆሽ ፡ የሰውን፡ ጤንነት ፡ ሊጐዱ ፡ የሚችሉ ፡ ነገሮችን ፡ በመሥራት ፡ በማውጣት ፡ ወይም ፡ እንዲዘዋ ወሩ ፡ በማድረግ ፡ (ቍ ፡ ፭፻፲ና ፡ ፭፻፲፪) ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ መልካም ፡ በሆነው ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ ኀፍረተ ፡ ነገሮችን ፡ የሚያሳዩ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ አሳትሞ ፡ በማውጣት ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ በግልጽ ፡ በማሳየት ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፮፻፱ ፡ እስከ ፡ ፮፻፲፩) ፡ የመሳሰሉትንም ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚፈጸሙ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊና ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። በመጨረሻውም ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ አቋሙ ፡ ልማድ ፡ እጅግ ፡ ለተለያየ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ሆኖ ፡ አብዛኛው ፡ ክፍሉም ፡ በረሃማ ፡ ጠፍ ፡ ለሆነ ፡ አገር ፡ ባለቤት ፡ የሌለውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብትን ፡ በመውሰድ ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፮፻፴፯) በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ ሰዶ ፡ በማበላሸት ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፮፻፴፱) ፡ በሕዝብ ፡ እምነት ፡ አጭበርብሮ ፡ ያላገባብ ፡ በመጠቀም ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፷፩) እና ፡ በየጊዜውም ፡ የማኅበራዊው ፡ የኢኮኖሚክና ፡ የሥልጣኔ ፡ እድገት ፡ በድንገት ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ መሄዱን ፡ በምንመለከትበት ፡ አገር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴው ፡ እጅግ ፡ ተራቅቆ ፡ ሠብ ዛት ፡ የሚችለው ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ወንጀል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ ግልጽ ፡ ስለሆነ ፡ (ቍ ፡ ፮፻፸፫) ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ መክ ሰርና ፡ በአጭበርባሪነት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲደርስ ፡ የማድረግን ፡ ወንጀሎች፡ በሚመለከተው፡ ጉዳይ ፡ (ቍ ፡ ፮፻፹፩ና ፡ ፮፻፹፪) እጅግ ፡ የተብራራ ፡ ድንጋጌ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የመስጠትን ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊነት ፡ ገምተን ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሁሉ ፡ በየክፍላቸውና ፡ በየምዕ ራፋቸው ፡ እንዲገኙ ፡ አድርገናል ፡ የደንብ ፡ መተላለፍን ፡ ትንንሽ ፡ ወንጀሎች ፡ በሚመ ለከተው ፡ ረገድም ፡ ከባለሥልጣን ፡ የሚሰጡትን ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነዶች ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ በመስጠት ፡ (ቍ ፡ ፯፻፶፭) በሌላ ፡ ሰው ፡ ሰላማዊ ፡ እረፍትና ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ በማድረስ ፡ (ቍ ፡ ፯፻፸) ፡ መንገዶችንና ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ስፍራዎችን ፡ ስለመጠ በቅና ፡ በነዚሁም ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ሁከት ፡ (ቍ ፡ ፯፻፹፪) ፡ የሰውን ፡ ሀብት ፡ በማበ ላሸት ፡ ወይም ፡ በማራከስ (ቍ ፡ ፰፻፶ና ፡ ፰፻፲) ፡ ስለሚፈጸሙት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀሎች ፡ ምሳሌ ፡ በመስጠትና ፡ ግዙፍ ፡ ለሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ግልጽነት ፡ ባለው ፡ አነጋገር፡ ዘርዝሮ ፡ በማስረዳት ፡ ሕጉን ፡ የተሟላ ፡ ማድረግም ፡ ጥቅሙ ፡ በትንሹ ፡ የማይገመት ፡ መሆኑን ፡ ተመልክተናል ።

የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ የአሠራር ፡ ፈሊጥ ፡ (ሜቶድ) ጥንታዊ ፡ ከሆነው ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበብና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንፈስ ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ እጥፍ ፡ የሆነ ፡ ጥቅምን ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ እንገምታለን ፤ ይኸውም ፡ ለዳኞቹና ፡ ለፍርድ ፡ ጠያቂው ፡ በተረጋገጠ ፡ ሁኔታ ፡ ተብራርቶ ፡ የተገለጸ ፡ በመሆኑ ፡ በቀላሉ ፡ እንዲረዱትና ፡ እንዲገባቸው ፡ የሚያደርግ ፡ ወዲያው ፡ ለፍርድ ፡ ጠያቂው ፡ በቂ ፡ ዋስትናን ፡ የሚያስገኝለት ፡ ሆኖ ፡ መዘጋጀቱ ፡ ነው ።

(ሐ) ለሕግ ፡ ቃላቶች ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባውን ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ ማግኘት ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ችግርን ፡ ያደረሰ ፡ በመሆኑና ፡ ይህም ፡ ጉዳይ ፡ ለሕጉ ፡ አሠራር ፡ መሠረታዊ ፡ ምንጩ ፡ ስለሆነ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜም ፡ በቂ ፡ ፍች ፡ ሊገኝለት ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ይገመት ፡ ስለነበረ ፡ በአሠራሩ ፡ ዘዴ ፡ (ቴክኒክ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጹትን ፡ ፈሊጦች ፡ መከተል ፡ ግድ ፡ ሆኗል ። እንደ ፡ እውነቱም ፡ ጥንታዊና ፡ እሮጌ ፡ የሆነው ፡ የቀድሞዎቹ ፡ የሀገሪ ፡ ክፍል ፡ ሀገር ፡ መነጋገሪያ ፡ የነበረው ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ የአገሩ ፡ የአድሚኒስትራሲዮንና ፡ የፍርድ ፡ ቋንቋ ፡ በመሆን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ኦፊሲየል ፡ ቋንቋ ፡ የሆነው ፡ ዐማርኛ ፡ በአዲሱ ፡ የሕግ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የሰፈሩትን ፡ የሕግ ፡ ዘዴ ፡ የተመላባቸውን ፡ ቃላት ፡ አብራርቶ ፡ ለማስረዳትም ፡ ሆነ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ቃል ፡ ተገቢውን ፡ ትርጉሙ ፡ ለመስጠት ፡ እጅግ ፡ የሚያጥር ፡ ሆኖ ፡ መገኘቱ ፡ አያጠራጥርም ። እንደምሥራቃዊ ፡ ቋንቋዎች ፡ ሁሉ ፡ አጭርና ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ለአጭር ፡ አሳብ ፡ መግለጫ ፡ ያህል ፡ የተፈጠረ ፡ መነጋገሪያ ፡ እንጂ ፡ ለዘመናዊ ፡ ሕጎች ፡ ምስጢራዊ ፡ ቃላት ፡ ማብራሪያ ፡ ለመሆን ፡ የሚበቃ ፡ ትርጉም ፡ ለማግኘት ፡ የሚችል ፡ ስፌ ፡ የሆነ ፡ የመፍቻ ፡ ቊልፍ ፡ ሊኖረው ፡ የማይችል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እንደዚሁ ፡ ላለው ፡ ጠባብ ፡ ቋንቋ ፡ በቂ ፡ ማብራሪያ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚቻልበትን ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ፈጥሮና ፡ አበጥሮ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቋንቋ ፡ አነጋገር ፡ በሚስማማ ፡ ሁኔታ ፡ ገልጾ ፡ በመጽሐፉ ፡ ላይ ፡ ማስፈር ፡ የማይቻል ፡ ተግባር ፡ ሆኖ ፡ መገኘቱ ፡ በግልጽ ፡ ይታያል ።

የሕጉን ፡ የዐማርኛ ፡ ትርጉም ፡ የማስተካከል ፡ ሥራና ፡ (እንዲሁም ፡ የሕጉ ፡ ኦፊሲየል ፡ ቋንቋ ፡ እንግሊዝኛውም ፡ ጭምር ፡ ስለሆነ) የሁለቱም ፡ ትርጉም ፡ ሥራ ፡ ሕጉን ፡ ራሱን ፡ ለመሥራት ፡ ከተደረገውም ፡ ድካም ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ከባድና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥረትን ፡ የጠየቀው ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ባለው ፡ አስተያየት ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቋንቋ ፡ እድገትና ፡ ለሕጉም ፡ አጻጻፍ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ቅርስ ፡ እንዳተረፈላት ፡ እናምናለን ።

የሕጉን ፡ አጻጻፍ ፡ እጅግ ፡ የተራዘመና ፡ የተስፋፋ ፡ አድራጎት ፡ የታየው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የገለጽነው ፡ ምክንያት ፡ መሆኑ ፡ የታመነ ፡ ነው ። በዚህም ፡ የተነሣ ፡ በኤውሮፓ ፡ ከደረሰበት ፡ ወቀሳ ፡ አንደኛው ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል [43] ። ነገር ፡ ግን ፡ በእንደዚሁ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ መገመት ፡ የሚገባው ፡ የሕጉን ፡ ጽሑፍ ፡ ረጅምነት ፡ ሳይሆን ፡ (ይህም ፡ ቢሆን ፡ የደንብ ፡ መተሳሰፍን ፡ ጉዳይ ፡ ከሚመለከቱት ፡ ሕጎች ፡ ጭምር ፡ ፭፻፭ ፡ ቊጥሮችን ፡ ብቻ ፡ የያዘ ፡ ስለሆነ ፡ ከአብዛኞቹ ፡ ሕጎች ፡ የበለጠ ፡ ብዛት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይገባም) እነዚሁንም ፡ ቢሆን ፡ በቊጥር ፡ አስጣጡ ፡ ረገድም ፡ ቢሆን ፡ በያዙት ፡ ስፍራ ፡ ትይዩ ፡ በሰው ፡ ሠራሽ ፡ ዘዴ ፡ ለማስረዘም ፡ ሆነ ፡ ለማሳጠር ፡ በቀላሉ ፡ የሚቻል ፡ እንደነበረ ፡ ሳይዘነጋ ፡ የአጻጻፉን ፡ ግልጽነት ፡ የአነጋገሩን ፡ ቀልጣፋነት ፡ በጠቅላላ ፡ አጻጻፉም ፡ ያለውን ፡ የማስረዳት ፡ ቀላልነት ፡ ጭምር ፡ መመልከት ፡ ይጠቅ

---

[43] ኤ ፡ ኣንቶኖ ፡ ፊሦሉስ ፡ እኖሪዎ ፡ ደ ፡ ድሬች ፡ ፔናል ፡ ዩ ፡ ሲዎንቬ ፡ ፔናሊስ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ (አ ፡ ኤ ፡ አ) ፲፱፻፶፰ ፡ የጻፈውን ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፰ ፡ ይመለከቷል ።

ማል ። ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ እንግዲህ ፡ የሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ የአሠራር ፡ ቅንጅት ፡ የወ ንጀልን ፡ ሕግ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በሥርዓት ፡ መድቦና ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ፡ በመሆኑ ፡ በሚታይበት ፡ የማስረዳት ፡ ኃይል ፡ ረገድ ፡ በአጻጻፉ ፡ መንፈስ ፡ ጠንካራነትና ፡ በግልጽነቱ ፡ ሊመሰገን ፡ የሚገባው ፡ ነው ።

2. በዘመናችን ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባው ፡ የክሪሚኖሎግ ፡ ሲያንስ ፡ (የወንጀልና ፡ ወንጀ ለኞች ፡ ምርምርና ፡ ጥናት ፡ ዕውቀት) አጻጻፍን ፡ የሚመለከተው [44] ፡ የሕግ ፡ አቀ ራረብ ፡ ግልጽ ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ፡ እያሉ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ድምጻቸ ውን ፡ ሲያሰሙ ፡ የኖሩትን ፡ ጠያቂዎች ፡ አሳብ ፡ ለማስደሰት ፡ በሚቻልበት ፡ ረገድ ፡ ሁሉ ፡ ሕጉ ፡ በተሟላ ፡ ሁኔታ ፡ ስለቀረበና ፡ ጠቅላላ ፡ አቋሙም ፡ በጽኑ ፡ መሠረት ፡ ስለደረጀ ፡ ይህ ፡ ዓላማ ፡ ተደርሶበታል ፡ ብለን ፡ እናምናለን ። የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ በቆራጥነት ፡ ለመከተል ፡ ያስቻለንም ፡ የነገሥታት ፡ ሕግ ፡ የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ የተመሠረተበት ፡ ባሕል ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ ባጥፊው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ በሚለው ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ስለሆነና ፡ ብዙዎቹ ፡ የኤውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ሕጋቸውን ፡ እንዳያድሱ ፡ መሰናክል ፡ የሆኑባቸው ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ጽሑፎችና ፡ የሕግን ፡ እምነት ፡ የዘወትር ፡ ልማድ ፡ አድርገው ፡ የሚከተሉ ፡ አጻጻፎች ፡ በብዛት ፡ ያልሠፈሩበት ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

በኛ ፡ ላይ ፡ እንደሚደርሰው ፡ ሁሉ ፡ ነገሩን ፡ ሳይረዱ ፡ አስቀድሞ ፡ በመፍረድ ፡ ደመና ፡ ያልተሸፈነው ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንፈስ ፡ ለፍርድ ፡ ሥራው ፡ አመራር ፡ ትክክ ለኛ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፤ ሊፈጸም ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ የሚያስበውን ፤ ቀናውን ፡ መንገድ ፡ ለመከተል ፡ ተስማሚ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ የሚያምንበትን ፡ ማንኛውንም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያላንዳች ፡ መጠራጠር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ ያለው ፡ ቆራጥነቱ ፡ የማያወላውል ፡ ነው ፡ ማንኛውንም ፡ ለማሻሻልና ፡ ለማደስ ፡ ያለው ፡ ፍላጎቱም ፡ ሊሻ ሻልና ፡ ሊታደስ ፡ ይገባዋል ፤ የተባለው ፡ ነገር ፡ ጥቅምን ፡ የሚያስገኝ ፡ ስለመሆኑ ፡ በቂ ፡ መተማመኛ ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚያስችለው ፡ ካረጋገጠ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አይመለስም ።

አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አድልዎ ፡ በማያስከትል ፡ አሠራርና ፡ በአፈጻ ጸሙም ፡ ረገድ ፡ ውጥንጥቅ ፡ የሆኑ ፡ ፍችዎችን ፡ በማይጠይቅ ፡ ዘዴ ፡ ሊደራጅ ፡ የቻለው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፤ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አድላዊ ፡ የሚቆጠ ሩትንና ፡ ለወንጀል ፡ ሕግ ፡ አቋቋምም ፡ ሆነ ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ እድገት ፡ ተቃ ራኒ ፡ የሆኑትን ፡ የአመዳደብ ፡ ልዩነቶች ፡ አስቀርቷቸዋል ። እንደዚህም ፡ ....

(ሀ) የሕጉ ፡ መተላለፍ ፡ ተግባሮች ፡ የተለያዩ ፡ ጠባይ ፡ አላቸው ፡ እየተባለ ፡ በሦ ስት ፡ ክፍል ፡ አለያይቶ ፡ የመመደብ ፡ አሠራር ፡ ከፈረንሳዊ ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ልምድ ፡ ውስጥ ፡ ተወስዶ ፡ ሲሠራበት ፡ እንደቆየው ፡ ሁሉ ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ጥፋት ፡ ሕግ ፡ ተላላፊነት ፡ በሚሉ ፡ ቃላት ፡ አከፋፍሎ ፡ በመጻፍ ፡ ፋንታ ፡ በነዚህ ፡ በሦስቱ ፡ ቃላት ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ልዩነት ፡ ያለመኖሩን ፡ ተገንዝበው ፡ በፈረንሳዊኛው ፡ ቃል ፡ "እን

---

[44] በተለይ ፡ ይህን ፡ ነጥብ ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ላ ፡ ዴፋንስ ፡ ሶሲያል ፡ ኑቬል ፡ በሚል ፡ አርዕ ስት ፡ ኤም ፡ አንሴል ፡ የጻፈውን ፡ ፓሪስ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታተመውን ፡ መሠረታዊ ፡ ድርሰት ፡ ተመልከት ። እንዲሁም ፡ ኧንትሮዱክሲዮን ፡ ገኖሪዳክ ፡ ኦ ፡ ፕሮብሌም ፡ ሜዲኮ ፡ ፕሲኮሎዢክ ፡ ኤ ፡ ሶሲያል ፡ ዱ ፡ ዴሌን ካን ፡ አክት ፡ ደ ፡ ፕረሚዬ ፡ ኩር ፡ እንቴርናሲዮናል ፡ ደ ፡ ክሪሚኖሎዢ ፡ ፓሪ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፲፱፻፶፮ ፡ ኤ ፡ ድሯ ፡ ፔናል ፡ ኤ ፡ ዴፋንስ ፡ ሶሲያል ፡ ረቩዊ ፡ ፔናል ፡ ሱዊስ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፲፱፻፶፩ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ግራቨን ፡ የጻፈውን ፡ የሚጠቅስ ፡ ነው ።

ፍራክሲዮን" ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ትርጉሙ ፡ ደግሞ ፡ "አፌንስዝ" በሚሉ ፡ ቃላት ፡ በማጠቃለል ፡ ሕግን ፡ የመተላለፉ ፡ ተግባር ፡ ባስከተለው ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ ለጥፋቱ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነውን ፡ ቅጣት ፡ በየደረጃው ፡ መድቦ ፡ በመስጠት ፡ ተሠርቷል ፤ እንዲሁም ፡ አነስተኛ ፡ የሆኑትን ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ተግባሮች ፡ በፈረንሳዊኛው ፡ አነጋገር ፡ "ኮንትራቫንሲዮን" ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ትርጉሙ ፡ ደግሞ ፡ "ፔቲ ፡ አፌንስዝ" በሚሉ ፡ ቃላት ፡ በማጠቃለልና ፡ የተለየ ፡ አርእስት ፡ በመስጠት[45] ፡ ለብቻቸው ፡ አጠቃሎ ፡ መድቧቸዋል ። ምክንያቱም ፡ እጅግ ፡ አነስተኛ ፡ የሆኑ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ተግባሮች ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ የማይቆጠሩ ፡ ክብርን ፡ የማይነኩ ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ የሚቀርቡት ፡ ለበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሲሆን ፡ በፍርዱ ፡ አሰጣጥ ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ አፈጻጸማቸውም ፡ ረጅም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ የማይጠይቅና ፡ እንደቀረቡ ፡ ወዲያውኑ ፡ የሚወሰኑ ፡ በመሆናቸው ፡ ወንጀል ፡ ተብለው ፡ ከሚጠሩት ፡ ነገሮች ፡ ጥቂት ፡ የተለዩ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሕግ ፡ መተላለፍ ፡ ተግባሮችን ፡ የሚመለከቱት ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ሕግ ፡ ተጠቃለው ፡ የተሠሩ ፡ ስለሆነ ፡ የአፈጻጸማቸው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ የሚወስነው ፡ ድንጋጌ ፡ አፈጻጸም ፡ የተረጋገጠ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ የሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ ጥናት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላላው ፡ ክፍሉም ፡ ሆነ ፡ (፯ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቍጥር ፡ ፺፪፻፺ና ፡ ተከታዩ) የደንብ ፡ መተላለፍን ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚመለከተው ፡ ልዩ ፡ ክፍሉ ፡ (፰ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፴፫ና ፡ ተከታዩ) የዚህን ፡ ዓይነት ፡ አመዳደብ ፡ ተስማሚነት ፡ ለመረዳት ፡ እጅግ ፡ ቀላል ፡ ይሆናል ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ያለፉትን ፡ (ቀዳሚዎቹን) ጽሑፎች ፡ የሚያሟሉ ፡ ስለሆኑ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ የተመደቡትን ፡ አርእስቶች ፡ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ የሚያስማሙና ፡ በትክክለኛ ፡ ሚዛን ፡ ላይ ፡ መሥርተው ፡ የያዙ ፡ ናቸው ።

ሕጉ ፡ ራሱም ፡ በተወሰነ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ ካንደኛው ፡ ጋር ፡ እየተጠቃቀሰ ፡ የሚገናኝበትን ፡ ነጥብ ፡ አስተካክሎ ፡ የያዘ ፡ ነው ፡ (ቍ ፡ ፹፯ ፤ ፫፻፴፩ ፤ ፲፱፻፵፰ ፤ ፲፱፻፹፱ ፤ ፳፻፲፱ ፡ እና ፡ ፳፻፲፫) ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ እምንትም ፡ ሆነ ፡ የተጻፈውን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋል ፡ ተግባር ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አሠራር ፡ ጥቅምን ፡ ለማስገኘት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ሕግ ፡ አውጭም ፡ የኛኑ ፡ አሳብ ፡ የሚደግፍ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። የአጻጻፉም ፡ ዘዴ ፡ እጅግ ፡ በተቃለለ ፡ ሁኔታ ፡ የተፈጸመ ፡ መሆኑ ፡ ለመጀመሪያው ፡ ተመልካች ፡ በግልጽ ፡ የሚታይ ፡ ነው ።

---

[45] «እንፍራክሲዮን» ማለት ፡ በሕግ ፡ የተከለከለውን ፡ መሥራት ፡ ወይም ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ስለመኖሩ ፡ በሕግ ፡ የታዘዘውን ፡ ያለመሥራት ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ የተከለከለው ፡ ወይም ፡ የታዘዘው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ በታወጁ ፡ ልዩ ፡ ሕጐችና ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ የሚያስቀጣ ፡ መሆኑ ፡ ተገልጿል ፤ (ቍ ፡ ፭፫ ፡ እና ፡ ቍ ፡ ፲ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩) «ኮንታራቫንሲዮን» ማለት ፡ ግን ፤ በአዋጅ ፡ በሕጋዊ ፡ ማስታወቂያና ፤ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ የተሰጠውን ፡ ግልጽ ፡ የሆነውን ፡ ክልከላ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወይም ፡ በነዚሁ ፡ ግልጽ ፡ ጽሑፎች ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረውን ፡ ሳይፈጽሙ ፡ በመቅረት ፡ በደንቦቹ ፡ ላይ ፡ የታወጁትን ፡ ጉዳዮች ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ ያለመፈጸም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፲፱፻፶፩) ስለ ፡ ከባድ ፡ ወንጀሎችም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ቀላል ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ጥፋቶች ፡ የሚወስነው ፡ ቅጣት ፤ የአጥፊውን ፡ አደገኛነት ፤ ወንጀሉን ፡ ለመሥራት ፡ ያነሳሱትን ፡ ምክንያቶች ፤ የጠባዩንም ፡ ወራዳነትና ፡ ይህንንም ፡ የመሳሰለውን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመከተል ፡ ሲሆን ፡ የሚቀጣውም ፡ እንዲታረም ፡ እንዲሻሻልና ፡ ከወንጀለኛነት ፡ ጠባዩ ፡ ድኖ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲመለስ ፡ ለማድረግ ፡ መሆኑ ፡ ተገልጿል ። የሱዊስን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቅ ፡ ባዘጋጀ ፡ ጊዜ ፡ እስቱስ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ አሠራር ፡ አቅድ ፡ ተከትሎ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በጊዜው ፡ ላለው ፡ ሁኔታ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ ታይቷል ፡ የሚል ፡ ተቃራኒ ፡ አሳብ ፡ ስለቀረበበት ፡ ዘዴውን ፡ ለውጦታል ፤ ይህንንም ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የአሠራሩን ፡ ሲስቴም ፡ በሚመለከተው ፡ ፕሮብሌም ፡ ላይ ፡ አሳባችንን ፡ በሰፊው ፡ ከመግለጻችንም ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ሲስቴም ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ በማወዳደር ፡ «ላክላሲፊካሲዮ ፡ ዴ ፡ እንፍራክሲዮን ፡ ዱዊ ፡ ኮድ ፡ ፔናል ፡ ኤ ፡ ሰዜኤፌ ፡» በሚል ፡ አርዕስት ፡ ረቩዊ ፡ ፔናል ፡ ሱዊስ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ ልዩ ፡ ቍጥር ፡ ስለ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሎጎዝ ፡ ምስጋና ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፶፭ ፡ በተለይም ፡ በ፪ኛው ፡ አርዕስት ፡ ከገጽ ፡ ፴፫ ፡ እስከ ፡ ፵፫ ፡ ዝርዝር ፡ ማብራሪያ ፡ ሰጥተናል ፡ (ግራቬን) ።

(ለ) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እጅግ ፡ የታወቀውን ፡ “የቅጣት ፡ ውሳኔ” በተባለውና ፡ “የማስጠንቀቂያ ፡ ውሳኔዎች” በተባሉት ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ልዩነቶች ፡ መካከል ፡ የተለያየ ፡ መደብ ፡ በመስጠት ፡ በሁለት ፡ ላይ ፡ በማለያየት ፡ መ ድቦ ፡ የመሥራትን ፡ ዘዴ ፡ አስወግዷል ። እነዚህን ፡ ሁለቱን ፡ ጉዳዮች ፡ አለያይቶ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራ ፡ በመስጠት ፡ የመሠራት ፡ ዘዴ ፡ የመነጨው ፡ ከስዊስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መ ቅጫ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበብ ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ ራሳቸው ፡ በራሳቸው ፡ የሚያጠግቡና ፡ በቂ ፡ (ፖዚቲቭ) ተብለው ፡ ለሚጠሩት ፡ ለመጀመሪያዎቹ ፡ ሕግጋቶች ፡ አሠራር ፡ ምሳሌነትን ፡ የሰጠ ፡ ነው[46] ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ መሠረታዊያን ፡ ድንጋጌዎች ፡ መ ካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ለማስረዳት ፡ የሚሰጠው ፡ ትርጉም ፡ እጅግ ፡ የተወሳሰበ ፡ ፍችን ፡ የሚያስከትል ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ተመሳሳይነታቸውን ፡ ወይም ፡ ልዩነታቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ አስቸጋሪና ፡ የሕጉን ፡ መንፈስ ፡ የሚያቃውስ ፡ ፕሮብሌም ፡ እንደሚያጋጥም ፡ ብዙዎቹ ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ ተርድተውታል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አውጭም ፡ ይህንኑ ፡ በመገንዘብ ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ውስብስብ ፡ የሆነ ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ ሳይከተል ፡ ሕጉን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚቻልበትን ፡ ቀና ፡ መንገድና ፡ ለሚገለገሉበትም ፡ ሰዎች ፡ በግልጽ ፡ እንዲገባቸው ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ በመፈለግ ፡ “ዲቪዚዮን ፡ ቢ ፡ ፓርቲት” ከሁለት ፡ ከፍሎ ፡ የመመደብ ፡ ሥርዓት ፡ የተባለውን ፡ አሠራር ፡ መከተል ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ አብራርቶ ፡ ገልጿል ። ይህንን ፡ ነጥብ ፡ በተለይ ፡ ለማጥናት ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሮም ፡ ተሰብስቦ ፡ የነበረው ፡ የእንቴርናሲዮናል ፡ ኮቫንሲዮን ፡ (የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ጉባኤ) እጅግ ፡ የጋለ ፡ ክርክር ፡ አድርጎ ፡ አንዳችም ፡ ተስማሚና ፡ አስታራቂ ፡ ውጤት ፡ ሳያስገኝ ፡ መቅረቱ ፡ የሚዘነጋ ፡ አይደለም[47] ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፤ የሕጉ ፡ አጻጻፍ ፡ ንድፈ-ሐሳብ ፡ (ቴዎሪክ) ከሚሆን ፡ ይቅል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውል ፡ (ፕራቲክ) ቢሆን ፡ የበለጠ ፡ ጥቅምን ፡ ያስገኛል ፡ ብሎ ፡ ያሰበውና ፡ በዚህም ፡ አሳብ ፡ የጸናው ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉት ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የሕግ ፡ አሠራርን ፡ ጥበብ ፡ ብቻ ፡ ወደሚመለከተው ፡ ቴክኒካዊ ፡ ሥርዓትና ፡ ከሁለቱ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ቅጦች ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ልዩነቶች ፡ ወይም ፡ ግንኙነቶች[48] ፡ ለማብራራት ፡ ወደሚያደረገው ፡ ጥረት ፡ በማድላት ፡ ፋንታ ፡ እያንዳንዱ ፡ ተቀጭ ፡ ከፈጸመው ፡ ጥፋት ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሚሆነውን ፡ የቅጣት ፡ ልክ ፡ በሚገባ ፡ አደላድሎ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ማስፈር ፡ የተሻለ ፡ ጥቅምን ፡ ያስከትላል ፡ ወደሚለው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ያዘነበለው ፡ ያጥፊውን ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ የወንጀሉ ፡ አሠራ

---

[46] ግራቨን ፡ ሌፔን ፡ ኤ ፡ ሌ ፡ መዙዊር ፡ ዱዊ ፡ ድሯ ፡ ፔናል ፡ ሱዊስ ፤ ሰክሪቲ ፡ ጁዮሪዲቺ ፡ ኢን ፡ ኦኖሬ ፡ ዴላ ፡ ቼዳም ፤ ፓንዱ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፲፱፻፶፪ ፡ ሁለተኛ ፡ ቮሊዩም ፡ ለብቻ ፡ ተለይተው ፡ የታተሙ ፡ ጥቅሶችንና ፡ በተለይም ፡ የሐሳቡን ፡ ማጠቃለያ ፡ ጽሑፍ ፡ ገጽ ፡ ፶፫ ፡ ተመልከት ።

[47] ረቩዊ ፡ እንቴርናሲዮናል ፡ ደ ፡ ድሯ ፡ ፔናል ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቁጥር ፡ ፬ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹፩ ፡ ለፕሮብሌም ፡ ደ ፡ ልኡኒፊካሲዮን ፡ ደ ፡ ላ ፡ ፔን ፡ ኤ ፡ ዴ ፡ መዙዊር ፡ ደ ፡ ሱዊረቴ ፡ ኤ ፡ ሴ ፡ ዛክት ፡ ኦፊሲየል ፡ ዱዊ ፡ ኮንግሬ ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ሮም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፲፱፻፶፯ ፡ የታተመውን ፡ ፕሮፌሰር ፡ ግራስፒኚ ፡ የሰጠውን ፡ ጠቅላላ ፡ ራፖር ፡ ተመልከት ።

[48] ይህን ፡ ነጥብ ፤ በፈረንሳዊኛ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የነበረው ፡ የመጀመሪያው ፡ ዋነኛ ፡ ረቂቅ ፡ ይበልጥ ፡ በተብራራ ፡ ሁኔታ ፡ ገልጾት ፡ ነበረ ፤ በጽሑፉም ፡ ላይ ፡ የተገለገለበት ፡ ቃል ፡ «ሳንክሲዮን» በሚባለው ፡ እንጂ ፡ «ፔን» በሚለው ፡ ቃል ፡ አልነበረም ። ሁለቱም ፡ ቃላት ፡ በዐማርኛ ፡ እተረጓጎማቸው ፡ የማይለዩ ፡ ሆነው ፡ ተቀላቅለዋል ። የእንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ ደግሞ ፡ «አንኩር» ወይም ፡ «ኤፓሲኩል» የሚለውን ፡ ቃል ፡ ፓኒሽመንት ፡ ፔናሊቲስ ፡ ፓኒሼብል ፡ የሚል ፡ ልማዳዊ ፡ ትርጉም ፡ ሰጥቶታል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የእንግሊዝኛውንና ፡ የዐማርኛውን ፡ ኦፊሲየል ፡ ትርጉም ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ ታርሞ ፡ በፈረንሳዊኛ ፡ ቋንቋ ፡ የታተመው ፡ ሕግ ፡ የእነጋገሩን ፡ መሠረታዊ ፡ ስሜት ፡ ሳይለቅ ፡ ፔን ፡ የሚለውን ፡ መዙዊር ፡ በሚል ፡ ቃል ፡ ተክቷል ።

ር ፡ ልማድ ፡ ውስጥ ፡ ተለይተው ፡ የተመደቡትን ፡ አጥፊዎች ፡ የአንትሮፖቢዎሎጊክ ፡ የፕሲኮሎጊክ ፡ (የሰው ፡ ልጅ ፡ ልማዶች ፡ ዕድሮች ፡ እምነቶች ፡ አምልኮቶች ፡ ዘርና ፡ እድገቶች ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አእምሮና ፡ ስሜት ፡ ጠባይ ፡ ዕውቀት) ግላዊ ፡ ስሜትና ፡ የግል ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ የሚያስችል ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳቱም ፡ ጭምር ፡ ነው ። የወንጀል ፡ ክፍል ፡ ዳኛ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ አጥፊው ፡ ወንጀሉን ፡ ለመሥራት ፡ ያነሳሱት ፡ ምክንያቶች ፡ አጠራጣሪዎች ፡ መሆናቸውን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ (ቍጥር ፡ ፺፩) ጥፋተኛው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ ሲሆን ፡ ወንጀሉን ፡ ከመሥራቱ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታና ፡ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩ ፡ እንዲጣራ ፡ ስለአእምሮውም ፡ ትክክለኛነት ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ የሕክምና ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ እዞ ፡ ከነዚህ ፡ ምርመራዎች ፡ የተገኙትን ፡ ውጤቶች ፡ የመከተል ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ስለሚወስነውም ፡ ቅጣት ፡ እነዚሁኑ ፡ የምርመራ ፡ ውጤቶች ፡ እንደዋና ፡ ማስረጃ ፡ አድርጎ ፡ የመያዝ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ መሆኑንና ፡ ይህም ፡ አፈጻጸም ፡ በጠቅላላው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ጥፋተኞች ፡ (ቍ ፡ ፺፰ ፡ እና ፡ ፩፻፳፩) ላይ ፡ የሚጸና ፡ መሆኑ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተለይቶ ፡ የተደነገገው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጹትን ፡ ምክንያቶች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ለተፈጸመው ፡ ጥፋት ፡ ተመሳሳይና ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነውን ፤ የወንጀል ፡ ሥራን ፡ መከላከልን ፤ አጥፊው ፡ እንዲታረምና ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ እንዲመለስ ፡ የማድረግን ፤ ወንጀል ፡ እንዳይሠራ ፡ አስቀድሞ ፡ የመጠበቅን ፡ ድንጋጌ ፡ ተስማሚና ፡ ተገቢ ፡ ውጤት ፡ በሚያስገኝ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ከተቻለ ፡ ለሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ የሚሰጠው ፡ ልዩ ፡ የአጠራር ፡ ሥም ፡ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የለውም ።

(ሐ) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ለቅጣት ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የሚያገለግሉት ፡ የእስር ፡ ቤቶች ፡ አመዳደብ ፡ የተለያየ ፡ እንዲሆን ፡ ማለት ፡ ለቀላል ፡ ቅጣትና ፡ ለከባድ ፡ ቅጣት ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የሚሆኑ ፡ እስር ፡ ቤቶችና ፡ ወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደራቸውም ፡ ሆነ ፡ አመሠራረታቸው ፡ የተለያየ ፡ እንዲሆን ፡ ይህም ፡ የተለያየ ፡ አስተዳደርና ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ተለይቶ ፡ እንዲገለጽ ፡ የሚለውን ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ አሳብ ፡ ሳይከተል ፡ ከአዲሱ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያስወገደበት ፡ ምክንያት ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ አፈጻጸም ፡ ተስማሚ ፡ ካለመሆኑም ፡ ይልቅ ፡ እስር ፡ ቤቶችን ፡ የሚያበዛ ፡ በመሆኑ ፡ ለየአንዳንዱ ፡ ዓይነት ፡ እስር ፡ ቤት ፡ አስተዳደርና ፡ ጥበቃ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ልዩ ፡ እውቀት ፡ ያላቸውን ፡ ሠራተኞች ፡ ለማዘጋጀትና ፡ ቅጣትንም ፡ በተለያየ ፡ ሁኔታ ፡ ለማስፈጸም ፡ እጅግ ፡ የተወሳሰበ ፡ ችግርን ፡ የሚያስከትል ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ ነው ።

በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ጥናት ፡ ያስገኘው ፡ ውጤት ፡ የቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ እንዲመራ ፡ ማድረግ ፡ የብዙ ፡ አገሮች ፡ ባሕላዊ ፡ ልማድ ፡ መሆኑን ፡ በተለይም ፡ በስዊስ ፡ ሕግ ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ለማሻሻል ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ ሁሉ ፡ ከባድ ፡ ችግርን ፡ ያስከተለ ፡ ሲሆን ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ወጥቶ ፡ የነበረውም ፡ የቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ልዩነት ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ያደረሰው ፡ ችግር ፡ በቀላሉ ፡ የሚገመት ፡ አልሆነም[49] ።

---

49 ይህን ፡ ፕሮብሌም ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ነጥቦች ፤ እንፎርማሲዮን ፡ ፔኒታንሲየር ፡ ሱዊስ ፡ እር ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፤ በተለይም ፡ የቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ይሁን ፡ ስለሚለው ፡ አሳብ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተጻፉትን ፡ ልዩ ፡ ቍጥሮችና ፡ እንዲሁም ፡ የእስር ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ተሻሽሎ ፡ እንዲለወጥ ፡ በቀረበው ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ሱዊስ ፡ አልዶርፍ ፡ በተባለው ፡ አገር ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተደረገው ፡ ሰፊ ፡ ክርክር ፡ የሚገልጸውን ፡ ራፖር ፡ ቍጥር ፡ ፰ንና ፡ ሌላውንም ፡ ተመልከት ።

በተጨማሪም ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ነጥብ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ቅንጅት ፡ የተከተለው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሕጐች ፡ አሠራር ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የአፈጻጸም ፡ ችግርና ፡ በገንዘብ ፡ ወጭ ፡ ረገድም ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ በመገንዘብ ፡ አፈጻጸሙን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የግል ፡ ነጻነት ፡ የሚያሳጡ ፡ ቅጣቶች ፡ ዓይነትና ፡ ደረጃ ፡ ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ ቅጣቱ ፡ የሚፈጸመው ፡ እስረኛው ፡ የዕለት ፡ ሥራን ፡ በማከናወን ፤ ቢያንስም ፡ ቢያድግም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲፈጸምበት ፡ በማድረግ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ እንደተገለጸው ፡ "ሲምፕል ፡ ኢምፕሪዝንመንት ፤ ሪጉረስ ፡ ኢምፕሪዞንመንት" ቀላል ፡ እሥራትና ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ በተባለ ፡ የቅጣት ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ደረጃ ፡ (ቍ ፡ ፩፻፭ ፡ እና ፡ ፩፻፮) ፡ ተከፋፍሎ ፡ በመመደብ ፡ ማለት ፡ (በሱዊስ ፡ አገር ፡ እንደሚደረገው) እስረኛው ፡ ክፍት ፡ በሆነ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ የእርሻ ፡ ወይም ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎችን ፡ እንዲያከናውን ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ የተቀጭውን ፡ ጠባይ ፡ አደገኛነትና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮም ፡ ላይ ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ ከባድነት ፡ በመገመት ፡ ዝግ ፡ በሆኑ ፡ ሥፍራዎች ፡ በጥብቅ ፡ እየተጠበቀ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎችን ፡ እንዲሠራ ፡ የማድረግ ፡ አስተዳደር ፡ ነው ። ይህ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ የሚያሳጡ ፡ ቅጣቶችን ፡ ሚስፈጸሚያ ፡ የሆነው ፡ አስተዳደር ፡ እጅግ ፡ ቀላልና ፡ ወዲያውም ፡ በቂ ፡ ከመሆኑም ፡ ይልቅ ፤ ቀላል ፡ የሆኑ ፡ እስራቶችን ፡ ለማስፈጸም ፡ ተቀጭውን ፡ በከባድ ፡ እሥራት ፡ ውስጥ ፡ በማኖር ፡ አንዳችም ፡ ፍሬ ፡ እንዳያስገኝ ፡ በማድረግ ፡ ፋንታ ፡ ለፈጸመው ፡ ጥፋት ፡ በቂ ፡ ካሣን ፡ ለመክፈል ፡ በሚችልበት ፡ መጠን ፡ እየሠራ ፡ ጥቅም ፡ እንዲሰጥና ፡ የተወሰነበትም ፡ ቅጣት ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ እያከናወነ ፡ በሚያገኘው ፡ ዋጋ ፡ እዳውን ፡ እንዲከፍል ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ጠባዩ ፡ ተሻሽሎ ፡ ሲገኝ ፡ አንዳንድ ፡ ሥፍራዎች ፡ ከመድረስ ፡ በመታገድና ፡ ሙሉ ፡ ነጻነት ፡ ከማግኘት ፡ ተከልክሎ ፡ በመቆየት ፡ በገደብ ፡ የመፈታት ፡ ዕድል ፡ እንዲያገኝ ፡ የማድረግን ፡ ሥርዓት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚያስችል ፡ ዘዴ ፡ ነው ፡ (ቍ ፡ ፩፻፱ ፡ እና ፡ ፩፻፲) [50] ። ይህም ፡ አስተዳደር ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ለሆነው ፡ ለሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ በሩን ፡ በመክፈት ፡ ላይ ፡ ለሚገኝ ፡ አገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅምን ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የሚገኘው ፡ የኤኮኖሚ ፡ ዕድገት ፡ በጥቂቱ ፡ ሊገመት ፡ የሚችል ፡ አይደለም ።

(መ) ከላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ የማቃለያና ፡ የማጠቃለያ ፡ ዘዴዎችም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ማቃለያ ፡ የሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ተገኝተዋል ፤ ከነዚህም ፡ ዋነኛው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ቅጣትን ፡ ለማስከተል ፡ ምክንያት ፡ የሆኑትን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ ተነጣጥለው ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩትን ፡ የተለያየ ፡ ጠባይ ፡ እንዳላቸው ፡ ያህል ፡ የሚቆጠሩትን ፡ ወንጀሎችና ፡ የሚወሰኑባቸውንም ፡ ቅጣቶች ፡ በአንድነት ፡ ቀምሮ ፡ በማስተባበር ፡ ለየራሳቸውና ፡ በየጉዳያቸው ፡ ልዩነት ፡ መጠን ፡ የተከፋፈለ ፡ አንቀጽና ፡ ምዕራፍ ፡ በመስጠት ፡ ባንድ ፡ መጽሐፍ ፡ የመሥራት ፡ ጥበብ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የወል ፡ ሕግንና ፡ የጦር ፡ ወታደርን ፡ ሕግ [51] ፡ በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ኃይሎች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ቅጣት [52] ፡ በማንኛውም ፡ ደረጃ ፡ ባሉት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችና ፡ ሹማምቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡

---

[50] ፕሮስታሲዮን ፡ ፔናል ፡ የተባለው ፡ ደንብ ፡ ቀድሞም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታወጀው ፡ በዩጎዝላቭ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የታወቀ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ብዙ ፡ ተከታይ ፡ አግኝቷል ። በፈረንሳይ ፡ አገርም ፡ ረፎርሚ ፡ ፔናል ፡ ኤ ፡ ፔኒታንሲየር ፡ በተባለ ፡ መጽሔት ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፮ ፡ ሪቤት ፡ ባቀረበው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ምክንያት ፡ የተደረገውን ፡ ሰፊ ፡ ክርክር ፡ ተመልከት ።

[51] ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፺፮ ፡ እስከ ፡ ፫፻፵፰ ፡ እና ፡ ቍጥር ፡ ፭፻፯ ፡ እና ፡ ፭፻፲ ፡ ከ፭፻፴፯ ፡ እስከ ፡ ፭፻፵፱ ፡ (የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀሎች) ።

[52] ከቍጥር ፡ ፫፻፵፱ ፡ እስከ ፡ ፫፻፶፩ ፡ እና ፡ ቍጥር ፡ ፭፻፶ ፡ (የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወንጀሎች) ።

ቅጣቶች[53] ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሱ ፡ የአእምሮ ፡ ጉድለት ፡ ያላቸው ፡ ጥፋተኞች ፡ የወንጀል ፡ ኀላፊ ፡ ስለሚሆንበት ፡ ሕግ[54] ፡ እንዲሁም ፡ አካለመጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ሰዎች[55] ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ለምሳሌ ፡ በመንግሥት ፡ የቀረጥና ፡ የግብር ፡ ገቢዎች ፡ በጠቅላላ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል[56] ፡ በንግድና ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች[57] ፡ እና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በአንድነት ፡ ተጠቃለው ፡ መደበኛ ፡ ሥፍራቸውን ፡ ይዘዋል ።

በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ እንግዲህ ፡ ቅጣትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሁሉ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቃለው ፡ ይገኛሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ የሕግ ፡ ሥልጣን ፡ የየራሱ ፡ የሆኑ ፡ የግል ፡ ድንጋጌዎች ፡ አሉት ፤ ቢሆንም ፡ የአንድነቱን ፡ ጠባይና ፡ ተመሳሳይነቱን ፡ የሚገልጹት ፡ አጠቃላይ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተመደቡት ፡ በዚያው ፡ መሰሉ ፡ በሆኑት ፡ አርእስቶች ፡ ውስጥ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አሠራር ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕጎችን ፡ በአንድነት ፡ አቀላቅሎ ፡ በጥርቅም ፡ ከማበራከት ፡ ለመዳን ፡ ስለተቻለና ፡ ይህም ፡ አሠራር ፡ መሠረታዊውን ፡ አሳብ ፡ የሚያለያየው ፡ ወይም ፡ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ የሚያጋጨው ፡ ማለት ፡ ያንዱን ፡ አሳብ ፡ ሌላው ፡ የሚያፈርሰው ፡ በመሆኑ ፡ የብዙ ፡ አገሮችን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ የማይታወቁና ፡ ሊታወቁ ፡ የማይችሉ ፡ ደኖች ፡ እድርጐት ፡ ስለተገኘ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሌላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ ወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ የሚጥል ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ዱር ፡ ሆኖ ፡ በመታየቱ ፤ (ኤሮር ፡ ጁሪስ ፡ ኖቼት) ፡ ሕግ ፡ ሲሳሳት ፡ ይበድላል ፡ የሚባለውን ፡ ጥንታዊና ፡ ቋሚ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የሚያስከትል ፡ ሆኖ ፡ መገኘቱን ፡ አስረድቶናል ።

ይህን ፡ በመሰለው ፡ ጥበባዊ ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ የተዘጋጀው ፡ ሕግ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጽሑፎችና ፡ ጋዜጦች ፡ ተበታትነው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውለው ፡ የነበሩትን ፡ አዋጆች ፡ ሁሉ ፡ በአንድነት ፡ አጠቃሎና ፡ ተገቢ ፡ ሥፍራቸውን ፡ እንዲይዙ ፡ አድርጎ ፡ በመቀመር ፡ አስተባብሮ ፡ አቅፏቸዋል ። ሊወሰኑ ፡ የሚገባቸውን ፡ ቅጣቶች ፡ መሠረታዊያን ፡ አሳቦች ፡ የቅጣቶቹን ፡ ዓይነትና ፡ መጠን ፡ ወንጀለኛ ፡ የሚያሰኙትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ (ቍጥር ፡ ፫፻፶፬ ፡ እና ፡ ፫፻፶፭ ፡ ፯፻፴፫) ፡ አጠቃሎ ፡ ገልጿቸዋል ። ይህም ፡ የሚያስገኘው ፡ ጥቅም ፡ አንዱን ፡ ከሌላው ፡ በማጠቃቀስ ፡ ዘወትር ፡ ተመሳሳይና ፡ እርግጠኛ ፡ ውጤትን ፡ በቀላሉ ፡ ሲያስገኝ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ በመግሥገሥ ፡ ላይ ፡ ለሚገኝና ፡ የጽሑፍን ፡ ሕግ ፡ በመለማመድ ፡ በዚህም ፡ ለመጠቀም ፡ ቁርጠኛ ፡ ሆኖ ፡ ለተነሳ ፡ አገር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሚስማማው ፡ መንገድ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ መርጦ ፡ አዲስ ፡ በሚሰጠው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ እንዲያገኘው ፡ ማድረግን ፡ ነው ።

ሕጉን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሠርቶ ፡ ማቅረብ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፤ በአንድነት ፡ አጠቃሎና ፡ አስተባብሮ ፡ በአንድ ፡ ሥፍራና ፡ በአንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ለመሥራት ፡ የሚያስችለን ፡ ዕድል ፡ ካጋጠመን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ የሕግ ፡ ዘርፍ ፡ በተለያየ ፡ ቦታ ፡ መበተን ፡ የሚያስፈልግበት ፡ እንዳችም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ለማግኘትም ፡ ሆነ ፡

---

[53] ፬ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፤ ከቍጥር ፡ ፬፻፲ ፡ እስከ ፡ ፬፻፴፯ ፡ እና ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፶፭ ፡ እስከ ፡ ፯፻፷፪ ፡ (የደንብ ፡ መተላለፍ) ።

[54] ፪ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ቍጥር ፡ ፵፰ ፡ እና ፡ ተከታዩ ፡ ከቍጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ እስከ ፡ ፩፻፴፯ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፶፯ ፡ ፯፻፯ ፡ እና ፡ ፯፻፱ ።

[55] ከቍጥር ፡ ፶፪ ፡ እስከ ፡ ፶፯ ፡ መሠረቱ ፡ እና ፡ ከቍጥር ፡ ፩፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፩፻፹፪ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ደንብ ። ፡

[56] ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፰ ፡ (ከቍጥር ፡ ፫፻፶፬ ፡ እስከ ፡ ፫፻፹፰ ፡ እና ፡ ከቍጥር ፡ ፳፬ ፡ እስከ ፡ ፯፻፶፯ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወ) ።

[57] ፯ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፹፩ ፡ እና ፡ ተከታዩ ፡ ከቍጥር ፡ ፰፻፲፯ ፡ እስከ ፡ ፰፻፰ ፡ (የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ወ) ።

አግኝቶ ፡ ለማቅረብ ፡ የምንሰጠው ፡ ሰበብ ፡ አያጋጥመንም ። ይህንንም ፡ ምክንያታችንን ፡ አጥጋቢ ፡ ያደርገዋል ፡ ብለን ፡ ለማመን ፡ የምንችለው ፡ በባሕልና ፡ በልማድ ፡ ለኖረ ፡ አገር ፡ አዲስና ፡ ዘመናዊ ፡ የሆነ ፡ የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ ሲሰጠው ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የኖረውን ፡ የልማዱን ፡ መሠረት ፡ ሳናፈርስ ፡ ዘመናዊውን ፡ እንግዳ ፡ ሕግ ፡ ለመተካት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ መገመት ፡ ገምቶም ፡ እርግጠኛነቱን ፡ ማወቅ ፡ የሚገባን ፡ መሆኑን ፡ ባለመዘንጋት ፡ ነው ።

የወል ፡ ሕግና ፡ የጦር ፡ ሠራዊትን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግ ፡ አንዱ ፡ ካንደኛው ፡ የሚለያይበት ፡ አንዳችም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሌለው ፡ በመሆኑ ፡ እነዚህን ፡ ሁለቱን ፡ ሕጐች ፡ አለያይቶ ፡ መሥራት ፡ አስፈላጊ ፡ ነበረ ፡ የሚያሰኝ ፡ ከባድ ፡ ሰበብ ፡ ሊቀርብልን ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ በተረጋገጠ ፡ ሁኔታ ፡ ለማመን ፡ ችለናል ።

እነዚህን ፡ ሕጐች ፡ ለማቀራረብ ፡ ያለው ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየተብራራ ፡ የሔደው ፡ የሐሳብን ፡ ግንኙነት ፡ ወደ ፡ ማስተባበር ፡ ያዘነበለው ፡ የዘመኑ ፡ ስሜት ፤ ለምሳሌ ፡ በሱዊስ ፡ አገር ፡ የተሠራውን ፡ የ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የወል ፡ ሕግ ፡ የሆነውን ፡ ጽሑፍና ፡ በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የተጻፈውን ፡ የወታደር ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ በአንድነት ፡ የማጠቃለል ፡ ዓላማ ፤ ሐሳብን ፡ በሚማርክ ፡ ሁኔታ ፡ አዘንብሎ ፡ ስላገኘነው ፡ እኛም ፡ በዚሁ ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ መሸነፍ ፡ ግዴታችን ፡ ሆኗል ። ይህን ፡ ዘዴ ፡ ለመከተል ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆነውን ፡ መንገድ ፡ በመምረጥ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወንጀል ፡ ነክ ፡ የሆነውን ፡ በዚያው ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነው ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ አከታትሎ ፡ መመደብና ፡ እንዲሁም ፡ መንግሥታዊ ፡ ወይም ፡ ብሔራዊ ፡ ወንጀሎች ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩትን ፡ ደግሞ ፡ በክፍላቸው ፡ ለይቶ ፡ ከተመሳሳይ ፡ ድንጋጌያቸው ፡ ጋር ፡ የተለየ ፡ ስፍራ ፡ መስጠት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሁኔታም ፡ ቢሠራ ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ አንቀጽ ፡ ብቻ ፡ በቀላሉ ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ እንዳይቀላቀል ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ አይተናል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የተሠራውን ፡ የዩጎዝላቭን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ምሳሌ ፡ የተከተለ ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ ይታወቃል ። በሌላ ፡ ዓይነት ፡ አስተያየት ፡ ረገድ ፡ ደግሞ ፡ የጦር ፡ ሠራዊትን ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ክፍል ፡ አባሎችን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ በመመልከት ፡ በሕጉ ፡ በመደበኛ ፡ ክፍሎቹ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ በጠቅላላ ፡ ክፍሉም [58] ፡ በልዩ ፡ ክፍሉ [59] ፡ ውስጥ ፡ በማጠቃለል ፡ በአንቀጽና ፡ በምዕራፍ ፡ ብቻ ፡ ለ

[58] በውጭ ፡ አገር ፡ የሚገኙ ፡ ወታደሮች ፡ ከሀገራቸው ፡ ውጭ ፡ ሆነው ፡ ለሚፈጽሙት ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ የቅጣቱ ፡ አወሳሰን ፡ እንዴት ፡ እንደሚመራ ፡ በተለይ ፡ ገልጾ ፡ ስለሚያመለክተው ፡ ድንጋጌ ፡ (ቊ ፡ ፲፭) ከሕግ ፡ ወሰን ፡ ሳያልፍ ፡ የተሠራውን ፡ የወታደርን ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ በሚመለከቱ ፡ ተግባሮች ፡ ሊወሰድ ፡ የሚገባውን ፡ ሕጋዊ ፡ እርምጃ ፡ የሚመለከት ፡ [ቊ ፡ ፷፬. ሀ] ከበላይ ፡ የሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ የትእዛዝ ፡ ሰጭውን ፡ አላፊነት ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጻሚው ፡ ከተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ አሳልፎ ፡ ሲገኝ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌ ፡ (ቊ ፡ ፷፱ ፡ እና ፡ ፸) ፤ የወታደርን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለማስከበር ፡ ወይም ፡ የታዛዥነትን ፡ ተግባር ፡ ለማጽናት ፡ ስለ ፡ ወታደራዊ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ፡ (ቊ ፡ ፸፫) ሊያዝ ፡ የሚገባውን ፡ እርምጃ ፡ የሚገልጹ ፡ ድንጋጌዎች ፤ የወታደሮችን ፡ የግል ፡ ነጻነት ፡ በማሳጣት ፡ ቅጣት ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ወታደር ፡ የእስራት ፡ አስተዳደር ፡ (ቊ ፡ ፩፻፲፫ ፤ ስለ ፡ እስራት ፡ እና ፡ ፩፻፲፮ ፡ ን ፡ ቊ ፡ ፩ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የማቆየት ፡ ቅጣት) ወይም ፡ ደግሞ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በጥይት ፡ በመደብደብ ፡ ስለ ፡ መፈጸም ፡ (ቊ ፡ ፩፻፲፮ ፡ ፩ ፡ ሁለተኛ ፡ ኃይለ ፡ ቃል) ፤ እና ፡ ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ ከጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ ማስወገድና ፡ ማዕርግን ፡ ስለ ፡ መግፈፍ ፡ የሚወሰኑትን ፡ ቅጣቶች ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ።

[59] እንዲሁም ፡ የወታደርን ፡ ሰነዶች ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የመለወጥን ፡ ወይም ፡ የማጥፋትን ፡ ወንጀል ፡ የሚያቋቁሙት ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ድንጋጌዎች ፡ (ቊ ፡ ፫፻፹፯ ፡ እና ፡ ፫፻፹፱) ፤ የወታደርን ፡ ምስጢር ፡ በመግለጽ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቊ ፡ ፬፻፬) ፤ የጦር ፡ ምርኮኛ ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ግዞተኛ ፡ እንዲያመልጥ ፡ በማድረግ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፬፻፵፯) ፤ የወታደር ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ በቤታቸው ፡ ወይም ፡ በማደሪያቸው ፡ በሠፈረባቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ሲፈጽም ፤ ወይም ፡ የጓደኞቹን ፡ ወይም ፡ የበላይ ፡ አለቆቹን ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ብረት ፡ የሆነውን ፡ ዕቃ ፡ በመስረቅ ፡ ስለሚፈጽመው ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፮፻፴፩ ፡ ን ፡ ቊ ፡ ፪ ፡ ሀ) ፤ ወይም ፡ እምነትን ፡ በማጉደል ፤ ወይም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡትን ፡ ሀብቶች ፡ በመስረቅ ፡ በማባከን ፡ ወይም ፡ በመደበቅ ፡ ስለሚፈጽመው ፡ ወንጀል ፡ (ቊ ፡ ፮፻፶፯ ፡ መ) ።

ይቶ ፡ የሁለቱንም ፡ ክፍሎች ፡ ማለት ፡ የወታደራዊውንም ፡ ሆነ ፡ የወል ፡ ሕግን ፡ የሚ
መለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በአንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ አስተባብሮ ፡ ለመሥራት ፡ የሚ
ቻል ፡ መሆኑን ፡ ለመገንዘብ ፡ የሚበቃ ፡ ምክንያቶች ፡ እናገኛለን ።

## ፪ ፤ ባሕልንና ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃን ፡ ስለማስታረቅ ፡ ባሕል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በዝርዝር ፡ ገልጸን ፡ ያመለከትናቸው ፡ ምክንያቶች ፡ የኢትዮጵያን ፡
ሕግ ፡ አዲስነት ፡ ለማስረዳት ፡ ሳደረግነው ፡ ሙከራ ፡ የሚበቁ ፡ ሆነው ፡ የተገመቱ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ከላይ ፡ ዘርዝረን ፡ እንዳስረዳነው ፡ ሁሉ ፡ የብዙ ፡ ክፍለ ፡ ዘመናትን ፡ የባሕል ፡
ቅርስ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመደገፍ ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ ለመሻሻል ፡ የተነሳው ፡ አዲስ ፡
ሕግ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የተለወጠ ፡ እንደሆነ ፡ መድኅን ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ የታሰበውን ፡
ሕይወታዊ ፡ ውጤት ፡ በማስገኘት ፡ ፋንታ ፡ ከጥንታዊው ፡ ባሕል ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ አፍታ ፡
የተለያየ ፡ እንደሆነ ፡ ሚዛን ፡ ማጣትን ፡ እንዲያውም ፡ ጸንቶ ፡ የቆየውን ፡ መሠረት ፡
ጨርሶ ፡ የማፍረስን ፡ አደጋ ፡ ለማስከተል ፡ መቻሉ ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ የምንክድበት ፡
ስሜት ፡ አናገኝም ።

የአንድ ፡ ሕግ ፡ እውነተኛ ፡ ተግባሩ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የማደስ ፡ ዐላማ ፡ ያለው ፡
ቢሆን ፡ እንዲያገለግል ፡ የተመደበበትን ፡ ሕዝብ ፡ መንፈስና ፡ ነዋሪ ፡ እምነት ፡ መቃ
ወም ፡ የማይገባው ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ፤ ይህንኑም ፡ ሞንቴስኪዮ ፡ የተባለው ፡
የሕግ ፡ ፈላስፋ ፡ የሕጎች ፡ መንፈስ ፡ በተባለው ፡ ድርሰቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ያበሠረልን ፡
ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ሕጉን ፡ ለማዘጋጀት ፡ የተቋቋመው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ አዘጋጅ ፡
ኮሚሲዮን ፡ ጉባኤ ፡ የተረዳው ፡ ስለሆነ ፡ ለአገሩ ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆነውን ፡ የሕዝቡ ፡
ስሜት ፡ የሚጠይቀውን ፡ ብሔራዊው ፡ የፍርድ ፡ አካሄድ ፡ ልማድ ፡ አሜን ፡ ብሎ ፡ የሚቀ
በለውን ፡ ለይቶ ፡ የሚያውቅ ፡ ስለሆነ ፡ በዚሁ ፡ መንፈስ ፡ ተመርቶ ፡ ይህንኑ ፡ መሠረ
ታዊ ፡ ሐሳብ ፡ ተከትሏል ።

(ሀ) ሕጉ ፡ የተከተለው ፡ ጠቅላላው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ ግርማዊ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ እንደጠቀሱት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ የሐሳብ ፡ ምር
መራ ፡ ግብ ፡ መድረስ ፡ የግድ ፡ አስፈላጊውና ፡ ጠቃሚው ፡ ስለሚሆን ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡
የወንጀል ፡ ሕግ ፡ ፖሊቲካ ፡ ለመሻገር ፡ "አጥፊ ፡ ሲቀጣ ፡ የሚያየው ፡ ብልህ ፡ ይሆናል፤"
ወይም ፡ አጥፊ ፡ የሚቀጣው ፡ ለተመልካቹ ፡ መቀጣጫ ፡ ሆኖት ፡ እንዲሠጋ ፡ (እንዲፈራ)
ነው ፡ የሚባለውን ፡ ልማድ ፤ ወንጀለኛ ፡ የሚቀጣው ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ለመልካም ፡
ሰውነት ፡ እንዲበቃና ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ እንዲመለስ ፡ ለማድረግ ፡ የወንጀልን ፡
ቅጣት ፡ ማቃለል ፡ ያስፈልጋል ፡ በሚለው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ለውጦ ፡ ከኢትዮጵያዊ
ያን ፡ መንፈስና ፡ እምነት ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ የኖረውን ፡ ጥንታዊ ፡ ባሕል ፡ መሥዋዕት ፡
ማድረግ ፡ የለበትም ፤ እጅግ ፡ ጥንታዊ ፡ ወዲያውም ፡ እጅግ ፡ አዲስ ፡ ለሆነ ፡ እስካሁን ፡
ድረስ ፡ ጥንታዊ ፡ ዘላንነቱንና ፡ ጠረኛነቱን ፡ ሳልተወው ፡ ሕዝብ ፡ በሚስማማ ፡ ልማዳዊ ፡
ሕግ ፡ ሲተዳደር ፡ ለኖረ ፡ በጠረፋም ፡ ለሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ የውስጥ ፡ ስሜት ፡ ምርመራ
ንና ፡ የእያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ የነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ኑሮውን ፡ የማሻሻልን ፡ ጉዳይ ፡ ከሚጠይ
ቀው ፡ ክፍል ፡ ይልቅ ፡ በጠቅላላው ፡ የሕዝቡን ፡ ጸጥታና ፡ የኅብረት ፡ ሰላሙን ፡ መጠ
በቅ ፡ ይበልጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ለሚገመተው ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ለሆ
ነው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የማያወላውል ፡ ምሳሌነትን ፡ የሚሰጥ ፡
እጅግ ፡ ጠንካራ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊው ፡

መሆኑ ፡ አያጠራጥርም ። እንዲያውም ፡ የሕጉ ፡ የቅጣት ፡ ከባድነት ፡ ኃይል ፡ ምሳሌነት ፤ ጠንካራ ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ እንደገና ፡ ለማቋቋምና ፡ ለማደርጀት ፡ የሰላምን ፡ ጥበቃ ፡ ለማጠንከር ፡ ተቀጭውም ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ሰውነት ፡ ተመልሶ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ እንዲመደብ ፡ የማድረግን ፡ ጉዳይ ፡ የሚያቃናው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እነዚህን ፡ ግምቶች ፡ ሁሉ ፡ በቸልታ ፡ ሊዘነጋቸው ፡ ስለማይገባው ፡ አብዛኛውንም ፡ ጊዜ ፡ ኤሮፓ ፡ አገር ፡ ጥንታዊና ፡ ቋሚ ፡ ሕጎች ፡ አሠራር ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ አጥፊ ፡ የሚቀጣው ፡ ለሌላው ፡ መቀጣጫ ፡ ሆኖ ፡ ተመልካቹ ፡ እንዲጠቀም ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ እምነት ፡ መሸጋገሪያ ፡ ሳያደርግ ፡ ለማለፍ ፡ አልቻለም ።

ወንጀል ፡ ሠሪዎች ፡ ጥፋት ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ የሚደርስባቸው ፡ ሕጋዊ ፡ የማስፈራራት ፡ የወቀሳ ፡ ተግሳጽና ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ወንጀልን ፡ ከመሥራት ፡ እንዲወገዱ ፡ የማይበቃ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፤ በሠሩት ፡ ወንጀል ፡ መጠን ፡ ቅጣት ፡ እንዲደርስባቸው ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚለውን ፡ ዐላማ ፡ የተከተለው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በኅብረቱ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ እንዲወገድ ፡ ለማድረግ ፤ ለሕዝቡ ፡ ዋስትና ፡ የሚሰጠው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ መሆኑን ፡ አልዘነጋም ። የሕጉ ፡ ጉዳይና ፡ ግቡ ፡ ዋነኛ ፡ ዐላማውም ፡ ይኸው ፡ መሆኑን ፡ መጽሐፉ ፡ በመጀመሪያው ፡ ቁጥሩ ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ አመልክቶት ፡ ይገኛል ፡ (የወ ፡ መ ፡ ሕ ፡ ቍ ፡ ፩) ።

እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ አርቆ ፡ አስተዋይነት ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የሞት ፡ ቅጣትን ፡ ፍርድ ፡ ጨርሶ ፡ ማስቀረትና ፡ መሠረዝ ፡ ለዘመኑ ፡ የማይስማማ ፡ እንዲያውም ፡ ፈጽሞ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ሳይገነዘበው ፡ አልቀረም ፤ ይህ ፡ ፍርድ ፡ የማኅበራዊውን ፡ ኑሮ ፡ ጸጥታ ፡ ለመከላከል ፡ የተረጋገጠ ፡ ዋስትናን ፡ የሚሰጥ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ የሆነውን ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ማለት ፡ በአርአያ ፡ ሥላሴ ፡ የተፈጠረውን ፡ ሰው ፡ መግደል ፡ በነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሞት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ካሣ ፡ ሊተካ ፡ ወይም ፡ በየትኛውም ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡ ሊከፈል ፡ አይችልም ፡ ከሚለው ፡ ከኢትዮጵያዊያን ፡ የፈራጅነት ፡ መንፈስ ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ የኖረ ፡ ጽኑ ፡ እምነት ፡ ነው ። በመካከለኛው ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ኤሮፓ ፡ ዘንድ ፡ ይታመንበት ፡ እንደነበረው ፡ ሁሉ ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ማለት ፤ የኃጢአተኛውን ፡ የጥፋት ፡ ዋጋ ፡ ማስከፈያና ፡ ሞትን ፡ በሞት ፡ በከፈለ ፡ ጊዜም ፡ አጥፊው ፡ ይቅርታንና ፡ ሥርየተ ፡ ኃጢአትን ፡ የሚያገኝበት ፡ ወዲያውም ፡ ላፈሰሰው ፡ ደም ፡ ዋጋውን ፡ በደሙ ፡ የሚከፍልበት ፡ ማለት ፡ ደምን ፡ በደም ፡ የሚክስበት ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉም ፡ በአንድ ፡ አሳብ ፡ የሚቀበለውና ፡ የሚስማማበት ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ አጥፊው ፡ ራሱም ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ቅጣት ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ በማመን ፡ የሚቀበለው ፡ ነው ። በኢትዮጵያም ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ኤሮፓ ፡ ዘንድ ፡ እንደሚደረገው ፡ የተቀጭውን ፡ አንገት ፡ በመጥረቢያ ፡ ወይም ፡ ጊዮሎቲን [60] ፡ በሚባለው ፡ መሣሪያ ፡ በመቁረጥ ፡ ሳይሆን ፡ የሟቹን ፡ ክብር ፡ በሚጠብቅና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ በተከተለ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

---

[60] ይህንን ፡ ፕሮብሌም ፡ ስለሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ረቡዊ ፡ እንቴርናሲዮናል ፡ ዱ ፡ ክሪሚኖሎዢ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ፖሊስ ፡ ቴክኒክ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ ላይ ፡ በ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በጻፍነው ፡ በገጽ ፡ ፪፻፭ ፡ እና ፡ በተከታዩ ፡ እጅግ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ አስተያየታችንን ፡ ሰጥተናል ፤ እንዲሁም ፡ ላትሪቡዊን ፡ ደ ፡ ዠኔቭ ፡ በተባለው ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ «በኢትዮጵያ ፡ የሰው ፡ መስቀያ ፡ እንጨቶች ፡ እግር ፡ ሥር» በሚል ፡ አርዕስት ፡ የተጻፈውን ፡ እውነቱን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የሚለውጥ ፡ የሀሜት ፡ ቃል ፡ በመቃወም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተከተለውን ፡ እውነተኛ ፡ መንፈስ ፡ አብራርተን ፡ በመግለጽ ፡ በአፕሪል ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በላክነው ፡ መልክት ፡ የሕጉን ፡ ትክክለኛ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ለማስረዳት ፡ ችለናል ።

እንዲሁም ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የቀድሞው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ የአካል ፡ ቅጣትን ፡ (ግርፋትን) ለማስቀረት ፡ አስቦ ፡ እንደነበረ ፡ እያስታወስን ፡ ዛሬም ፡ በአዲሱ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘበት ፡ ምክንያት ፡ በቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ መንፈስና ፡ በባሕላዊው ፡ ልማድ ፡ መካከል ፡ የኖረው ፡ የሐሳብ ፡ መጋጨት ፡ ያስከተለው ፡ ውጤት ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ይህ ፡ ቅጣት ፡ አረመኔነትን ፡ የተመረኰዘ ፡ ከዛሬው ፡ ዘመን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ የሰብአዊ ፡ ፍጡርን ፡ ክብር ፡ የሚያዋርድና ፡ የዘመኑ ፡ መንፈስ ፡ ተቃራኒ ፡ መሆኑን ፡ የማይክድ ፡ የለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ደፋርና ፡ ጀግና ፡ የሆነ ፡ የተፈጥሮ ፡ ኩራት ፡ የሚሰማው ፡ ሕዝብ ፡ ይበልጥ ፡ የሚፈራው ፡ ውርደትን ፡ እንጂ ፡ በቅጣት ፡ መሠቀየትን ፡ ስላልሆነ ፡ ይህም ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ ጥፋቱ ፡ ለሞራል ፡ የሚቀፍ ፡ ወራዳነትን ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆነ ፡ መንፈሰ ፡ ልክስክስነትን ፡ ወይም ፡ የወንጀል ፡ አድራጊውን ፡ የተለየ ፡ ጨካኝነትንና ፡ የአውሬነት ፡ ጠባይ ፡ ያዘለ ፡ ክፋትን ፡ በግልጽ ፡ በሚያሳይበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ይህን ፡ ለመሳሰለው ፡ ወንጀል ፡ የሚፈጸም ፡ ቅጣት ፡ በመሆኑ ፡ ማንኛውም ፡ መንፈስ ፡ እንደሚቀበለውና ፡ እንደሚደግፈው ፡ ይታመናል ። ስለሆነም ፡ ይህ ፡ ቅጣት ፡ ጨርሶ ፡ እንዲቀርና ፡ በአዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይጻፍ ፡ በሚለው ፡ አሳብ ፡ ሰፊ ፡ ክርክር ፡ ተደርጐበት ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ጉባኤ ፡ በኩል ፡ ከፍተኛ ፡ የድምፅ ፡ ድጋፍ ፡ አግኝቶ ፡ ከሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ተሠርዞ ፡ ቀሪ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ፓርለማው ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጻፍ ፡ የሚለውን ፡ አሳብ ፡ እንዲደግፍ ፡ ያነሳሳውና ፡ ከሕጉ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔዎች ፡ አንዱ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ ያስደረገው ፡ ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጻፍነው ፡ ባሕላዊ ፡ ምክንያት ፡ ስላለ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ ቅጣት ፡ ያልሠረዘውም ፡ ቢሆንና ፡ እንዲሁም ፡ የአካል ፡ (የግርፋት) ቅጣትንም ፡ እንደተጨማሪ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ አድርጎ ፡ ቢያስቀረውም ፡ እንኳ ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳያጸድቁት ፡ እንደማይፈጸም ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ይህን ፡ ፍርድ ፡ የሚሰጠው ፡ እጅግ ፡ ለተወሰኑ ፡ ወንጀሎች ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በአፈጻጸሙም ፡ በኩል ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄን ፡ የተከተለ ፡ እንዲሆንና ፡ (ከቁጥር ፡ ፩፻፲፮ ፡ እስከ ፡ ፩፻፲፱) ስለሞት ፡ ፍርድና ፡ ፍርዱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቅጣት ፡ ሊለወጥ ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ የግርፋቱም ፡ ቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ እንደዚሁ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄንና ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ክብር ፡ የሚጠብቅ ፡ እንዲሆን ፡ (ቍ ፡ ፩፻፳ ፡ ሀ)[61] አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ልዩ ፡ ጥንቃቄ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ተሠርቷል ።

ንብረት ፡ በመውረስ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ቅጣቶችን ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ደግሞ ፡ በተለይ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የተቀጭውን ፡ ንብረት ፡ የመውረስን ፡ ቅጣት ፡ (ቍ ፡ ፺፯) የመወሰንና ፡ እንዲሁም ፡ ለተበዳይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ካሣና ፡ ስለ ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ (ቍ ፡ ፩፻ ፡ እና ፡ ፩፻፩) ንብረት ፡ የመውረስን ፡ ወይም ፡ የመያዝ ፡ ቅጣትን ፡ መወሰን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባሕል ፡ ሲሠራበት ፡ የኖረ ፡ ነው ። ይህም ፡ ልማድ ፡ እስከ ፡ እኛ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ የቆየውን ፡ የነፍስ ፡ ዋጋን ፡ በገንዘብ ፡ መክፈልን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ በመከተል ፡ ሲያያዝ ፡ ከመጣው ፡ ባሕል ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የእነዚህ ፡ አርእስቶች ፡ አሠራር ፡ ሕጉ ፡ ጥንታዊውን ፡ ባሕል ፡ ጨርሶ ፡ ሳይለቅ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ዘመናዊው ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ ለመሻገር ፡ እንዲቻል ፡ የተደረገውን ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚያስረዳ ፡ ከመሆኑም ፡

---

[61] ይህ ፡ የተለየ ፡ ምልክት ፡ የተሰጠው ፡ ልዩ ፡ ቍጥር ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ ገብ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘበት ፡ ምክንያት ፡ በድጋሚ ፡ የተጻፈው ፡ ፩፻፳ ፡ (ሀ) ቍጥር ፡ መጀመሪያ ፡ ከሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ጨርሶ ፡ በመሠረዝ ፡ ቀሪ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ በፓርላማው ፡ በተደረገው ፡ ክርክር ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ እንዲጻፍ ፡ ስለ ፡ ተወሰነ ፡ ተከታታይ ፡ ስፍራ ፡ በማጣት ፡ በድጋሚ ፡ በመጻፉ ፡ ነው ።

በላይ ፡ የጥንታዊውን ፡ ልማድ ፡ በማሻሻል ፡ በዘመናዊ ፡ መንፈስ ፡ መመራት ፡ የሚቻል ፡ መሆኑንና ፡ ልማዱ ፡ ጨርሶ ፡ መለወጡ ፡ ሳይሰማ ፡ በአዲስ ፡ መንፈስ ፡ ተተክቶ ፡ የሁሉ ንም ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑንም ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ። የንብረት ፡ መውረስ ፡ ቅጣት ፡ አፈጻጸም ፡ ወሰን ፡ የአጥፊውንና ፡ የቤተሰቡን ፡ ኑሮ ፡ በሚ ገባ ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ አጥብቆ ፡ በመከተል ፡ ከቤተሰቡ ፡ መሃል ፡ ከወንጀሉ ፡ ንጹሕ ፡ የሆነው ፡ ዘመዱ ፡ በአጥፊው ፡ ወንጀለኛነት ፡ ምክንያት ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስበት ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ በማድረግ ፡ ሊፈጸም ፡ ይገባዋል ፡ የሚለውን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሲሠራበት ፡ የቆየው ፡ ልማድና ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከወጣው ፡ ከቀድሞው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ (ከቍ ፡ ፳፫ ፡ እስከ ፡ ፴፱) የጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ የፍትሕ ፡ መንፈሱ ፡ ባሕላዊውን ፡ ፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ልማድ ፡ መሪ ፡ አድርጎት ፡ ስለተገኘና ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ሲሠራም ፡ በአንዳንድ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የጥንታዊ ውን ፡ ባሕል ፡ መንፈስ ፡ መከተል ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ በመገመት ፡ ይህንኑ ፡ የመሳሰለ ውን ፡ አሳብ ፡ ከቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በመቅዳት ፡ አሻሽሎ ፡ ለዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ በሚ ስማማ ፡ አጻጻፍ ፡ እንዲያገለግል ፡ ማድረግ ፡ የሚገባን ፡ መሆኑን ፡ በመረዳታችን ፡ ተጠቅ መንበታል ።

(ለ) የግል ፡ አላፊነትን ፡ (የነፍስ ፡ ወከፍ) አጥፊነትንና ፡ ይህን ፡ በመሰሉት ፡ ሌ ሎች ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የሚወሰደውን ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ብዙ ፡ ድን ጋጌዎች ፡ አመሠራረት ፡ የሕጉ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ የተከተለው ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ መሠረ ታዊ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። እንዲሁም ፡ አጥፊው ፡ ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፡ ሕግን ፡ ባለማወቅ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በሚገመትበት ፡ ጊዜና ፡ ይቅርታን ፡ የሚያሰጥ ፡ ምክ ንያት ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ የሚደግፈው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከጥፋት ፡ የደረሰው ፡ በእርግጠኛ ፡ እምነቱ ፡ የሰራው ፡ መስሎት ፡ የተሳሳተውም ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መስሎት ፡ አንድ ፡ ጥፋት ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣቱ ፡ ስለሚቃለልበት ፡ ሁኔታ ፡ (ቍ ፡ ፭፰) ፡ እንዲሁም ፡ ጥፋቱን ፡ የፈጸመው ፡ በእውቀቱ ፡ መጉደል ፡ ባለማወቅ ፡ በመንፈስ ፡ ልልነት ፡ ወይም ፡ ባላሰበውና ፡ ድንገተኛ ፡ በገጠ መው ፡ ምክንያት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛው ፡ ወንጀሉን ፡ እስከ ፡ ሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የዘወትር ፡ ጠባዩ ፡ መልካም ፡ እንደነበረ ፡ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ በመመርመር ፡ ረገድ ፡ ስለሚወሰደው ፡ የውሳኔ ፡ አሰጣጥ ፡ እርምጃ ፡ (ቍ ፡ ፭፱) ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ወንጀለኛው ፡ ጥፋት ፡ የሠራው ፡ በከሐዲነት ፡ በወስላታነት ፡ በከፋ ፡ ጠባይና ፡ በመጥፎ ፡ አመል ፡ በቂመኛነት ፡ በወራዳነት ፡ አሳብ ፡ በመነሳሳት ፡ ወይም ፡ በክፉ ፡ ፍላ ጐትና ፡ ምኞት ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ክፋትና ፡ ጨካኝነት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣትን ፡ ስለ ማክበድ ፡ (ቍ ፡ ፹፩) ስለሚወሰደው ፡ እርምጃ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣውን ፡ የቀድሞውን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ (ቍ ፡ ፵፩ ፡ እና ፡ ተከታዩ) መንፈስ ፡ በመከተል ፡ ሲሆን ፡ የአጻጻፉን ፡ ዘዴ ፡ ግን ፡ ለዘመናዊው ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ተስማሚ ፡ በሚሆን ፡ ዐይነት ፡ አሻሽለን ፡ በማስፋፋትና ፡ በማብራራት ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ አስፍረነዋል ።

የሕጉን ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቅ ፡ ባዘጋጀንበት ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባሕል ፡ የነበረው ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲሠራበት ፡ የኖረው ፡ ልማድ ፡ ጨርሶ ፡ እንዳይቀር ፡ በማሰብ ፡ ስለ ንብረት ፡ ወንጀለኞች ፡ (ስለ ፡ ንብረት ፡ አላፊነት) ማለት ፡ ከመካከለኛው ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ርቀው ፡ የሚገኙ ፡ እስከዛሬም ፡ በዘላንነት ፡ የሚኖሩ ፡ የጠረፍ ፡ ግዛት ፡ ነገዶች ፡ እንደሚሠሩት ፡ ሁሉ ፡ የንብረት ፡ ዘረፋ ፡ ወይም ፡ በተባባሪነት ፡ ሰው ፡ የመግደል ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ የንብረት ፡ ዘረፋውና ፡ የሰው ፡ መግደሉ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመው ፡ ተለይተው ፡ ባልታወቁ ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ የአጥፊዎቹ ፡ ነገድ ፡ የታወቀ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ በቅጣቱ ፡ አወሳሰን ፡ ረገድ ፡ ስለሚወሰደው ፡ እርምጃ ፡ ድንጋጌውን ፡

አዘጋጅተን ፡ የነበረው ፡ የቀድሞውን ፡ ልማድ ፡ ከዘመናዊው ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ጥበብ ፡ ጋር ፡ በማስታረቅ ፡ አወራርሰን ፡ ለዘመኑ ፡ መንፈስ ፡ በሚስማማ ፡ ሁኔታ ፡ ተዛምዶ ፡ እንዲገኝ ፡ ለማድረግ ፡ ስለነበረ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ አግብተን ፡ የነበረው ፡ ከእንቴርናሲዮናል ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ የመነጨውን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ በመከተልና ፡ (ረቂቁ ፡ ጽሑፍ ፡ ከቍ ፡ ፶፫ ፡ እስከ ፡ ፶፰) ፡ የቅጣቱንም ፡ አወሳሰን ፡ ጉዳይ ፡ ተስማሚ ፡ ከሆነው ፡ የአስተዳደር ፡ ደንብ ፡ ጋር ፡ በማስተባበር ፡ (ከቍ ፡ ፩፻፸፬ ፡ እስከ ፡ ፩፻፹፩) እና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ባሕል ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ የቆየውን ፡ መንፈስ ፡ በመከተል ፡ ነበረ ። በዚሁ ፡ አሳብ ፡ ጸንተን ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተውን ፡ ክፍል ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ለማስቀረት ፡ ብንችል ፡ ኖሮ ፡ በእውነቱ ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ለተከተለው ፡ መንፈስ ፡ ክርክር ፡ የሌለበትን ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚሰጥ ፡ በባሕላዊ ፡ መሠረቱ ፡ ላይ ፡ የታነጸና ፡ ከአዲሱ ፡ ዘመን ፡ ስሜት ፡ ጋር ፡ በፍጹም ፡ የማይጋጭ ፡ ሐሳቡን ፡ በማሻሻል ፡ ብቻ ፡ የጥንቱን ፡ ልማድ ፡ እንደነበረ ፡ የማስቀረት ፡ መሠረታዊ ፡ ጥቅም ፡ እንዳስገኘን ፡ ያህል ፡ እንቆጥረው ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ነገር ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፶፩ ፡ ከተጻፈው ፡ አላፊነት ፡ የግል ፡ ነው ፡ ከሚለው ፡ ሕጋዊ ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ ምክንያት ፡ ከአዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተሠርዞ ፡ ቀሪ ፡ ሆኗል ።

(ሐ) በአንዳንዶቹ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነጥቦች ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ በችኮላ ፡ ለማለፍም ፡ ሆነ ፡ ድፍረትን ፡ የሚያሳዩ ፡ ወይም ፡ ድንገተኛ ፡ ሆነው ፡ የሚታዩ ፡ አዲስ ፡ ነገሮችን ፡ በጥንቱ ፡ ልማድ ፡ መተካት ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ መለወጥ ፡ የማይቻል ፡ ከመሆኑም ፡ ይልቅ ፡ ለክሪሚኖሎጊክ ፡ ሶሲያል ፡ ሲያንስ ፡ (ለወንጀልና ፡ የወንጀለኞች ፡ ዕውቀት ፡ ጥናት ፡ ምርምር ፡ ኅብረ - ኑሮ ፡ ትክክለኛ ፡ ዕውቀት) ፡ ገና ፡ አሁን ፡ በሩን ፡ ለከፈተ ፡ በተለይም ፡ የፕሲኮፓቲ ፡ (በአእምሮ ፡ መበላሸት ፡ አስተያየት ፡ አለመብሰል) ፡ የፕሲኮሎጊ ፡ (የሰው ፡ ልጅ ፡ አእምሮና ፡ ስሜት ፡ አቋምና ፡ አገልግሎት ፡ ዕውቀት) እና ፡ የፔዳጎጊ ፡ (የትምርት ፡ አስተዳደግ ፡ ዕውቀት) መንፈስ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ እንግዳ ፡ ደራሽ ፡ ለሚሆንበት ፡ አገር ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ አዲስ ፡ ሙከራ ፡ ማድረግ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ልንከተለው ፡ የሚገባን ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባራችን ፡ ይመክረናል ።

ይኸውም ፡ ቢሆን ፡ ሕጉ ፡ እጅግ ፡ ፈጣን ፡ ወደሆነ ፡ ዘመናዊነት ፡ ርቆ ፡ የተራመደ ፡ በመሆኑ ፡ የሱዊስን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ (ቍ ፡ ፲፭ ፡ እና ፡ ተከታዩ) የአንዳንድ ፡ ሌሎች ፡ ዘመናዊ ፡ ሕጎችን ፡ አጻጻፍ ፡ ምሳሌ ፡ በመከተል ፡ የተቀነሱ ፡ የወንጀል ፡ አላፊነቶችን ፡ (ቍ ፡ ፷፱) አላፊነት ፡ በሌላቸውና ፡ አላፊነታቸው ፡ በተቀነሰ ፡ አጥፊዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ግዞት ፡ ሕጋዊ ፡ ሕክምና ፡ እንዲደረግ ፡ በሚሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ረገድ ፡ የቅጣትን ፡ ውሳኔ ፡ ለጊዜው ፡ አግዶ ፡ ስለማቆየትና ፡ (ከቍ ፡ ፩፻፷፩ ፡ እስከ ፡ ፩፻፷፯) ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ነገር ፡ ስለሚመለከት ፡ የቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ አጠባበቅ ፡ የሕጉ ፡ አሠራር ፡ በከፊል ፡ ቅጣትን ፡ የሚወስን ፡ ሲሆን ፡ በከፊል ፡ ደግሞ ፡ በሕክምና ፡ ጥበብ ፡ የመመርመርን ፡ ተቀጪውን ፡ የመደገፍንና ፡ የመጠበቅን ፡ ዝንባሌ ፡ የያዘ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ቅንጅት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በሚቻልበትና ፡ ጉዳዩም ፡ እጅግ ፡ ጥልቅ ፡ የሆኑ ፡ ምርመራዎችንና ፡ ጥናቶችን ፡ የማድረግ ፡ ሥርዓትን ፡ የተከተለ ፡ በሆነበት ፡ በምዕራባዊያን ፡ አገሮች ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ጉዳዮች ፡ በሚያጋጥሙበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የወንጀል ፡ አላፊነት ፡ የሚወሰነው ፡ በከፊል ፡ ሆኖ ፡ ይህንኑ ፡ አላፊነት ፡ የተቀነሰ ፡ ለማድረግ ፡ ምክንያት ፡ ለሚሆነው ፡ ለአእምሮ ፡ ጉደሎነት ፡ ወይም ፡ በቢዮ-ፕሲኮሎጊክ ፡ (በሕያው ፡ ነገር ፡ የአእምሮና ፡ ስሜት ፡ አቋምና ፡ አገልግሎት ፡ ዕውቀት) ጠንቅ ፡ ለሚደርስ ፡ የአንጐል ፡ መናወጥ ፡ የሕክምናን ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ አጠባበቅን ፡

ወይም ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሕመም ፡ የደረሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ ተይዘው ፡ እንዲጠበቁ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ የማቆየትን ፡ ፍርድ ፡ ያስወስናል ፡ የሚያሰኝ ፡ በቂና ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ ባጋጠመ ፡ ቍጥር ፡ (የአጥፊው ፡ አላፊነት ፡ በከፊል ፡ እንደመሆኑ ፡ ቅጣቱንም ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ መቀነስ ፡ ግዴታ ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር) ቅጣትን ፡ ከተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ጋር ፡ አመዛዝኖ ፡ በማጣመር ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ፡ ወይም ፡ አይቻልም ፡ በሚለው ፡ ነጥብ ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ መገመቱ ፡ በግልጽ ፡ የታመነ ፡ ነው ። በዚህ ፡ የተነሳም ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ማለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ከመዘጋጀቱ ፡ በፊት ፡ በሮም ፡ ስብሰባ ፡ አድርጎ ፡ የነበረው ፡ የኢንቴርናሲዮናል ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ምርመራ ፡ ሸንጎ ፡ (ኮንግሬስ) ፡ በጉዳዩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ ጉዳይ ፡ ቅልቅል ፡ የሆነ ፡ ቅንጅት ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ የማይገባ ፡ መሆኑንና ፡ ስለ ፡ ጥንቃቄ ፡ አጠባበቅ ፡ ከሚሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ጋር ፡ የቅጣቱን ፡ ውሳኔ ፡ ተደራቢ ፡ በማድረግ ፡ አጣምሮ ፡ መወሰን ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ ዳኛውም ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጥ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ከመመራት ፡ መወገድ ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ በቂ ፡ ቍጥር ፡ ባላገኘ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠቱን ፡ እናስታውሳለን ። የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ቅንጅት ፡ የተመሠረተው ፡ በረቂቅ ፡ መንፈስ ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ ግዙፍ ፡ ሆኖ ፡ በሚታየው ፡ በእውነተኛው ፡ የክሪሚኖሎጂክ ፡ (የወንጀል ፡ አፈጻጸም ፡ ምርምር ፡ ጥናት ፡ ዕውቀት) መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ላይ[62] ፡ ያለመሆኑን ፡ በማወቃችን ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ቅንጅት ፡ የመከተያችን ፡ ዘመን ፡ ማለፉን ፡ ከመረዳታችንም ፡ በቀር ፡ የትኛውም ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ ወይም ፡ ዘመናዊውን ፡ መሻሻል ፡ የተከተለ ፡ ሕግ ፡ ገና ፡ ያልደረሰበት ፡ ነጥብ ፡ መሆኑንም ፡ መዘንጋት ፡ አንችልም ።

ይህንንም ፡ ድርጅት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ቍጥራቸው ፡ እጅግ ፡ የተቀነሰ ፡ አገሮች ፡ ብቻ ፡ ሊያገኙ ፡ የሚችሉትን ፡ አቋምና ፡ እጅግ ፡ የተራቀቀ ፡ የፕሲኪያትር (የአእምሮ ፡ መናወጽን ፡ የሚመለከት ፡ ሕክምና) ፡ የፔኖሎግ ፡ (የቅጣትና ፡ ወንጀል ፡ እንዳይፈጸም ፡ መከላከል ፡ የእስር ፡ ቤቶችና ፡ የጠባይ ፡ ማረሚያዎች ፡ ጥናት ፡ ዕውቀት) እና ፡ የዚሁ ፡ ልዩ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ዐዋቆች ፡ (ስፔሲያሊስት) የሆኑ ፡ ዳኞች ፡ ለሚያስፈልገው ፡ ጉዳይ ፡ አዲስና ፡ ዘመናዊ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ ለመመሥረት ፡ ያለውን ፡ ፍላጐት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ለገለጸና ፡ ወደዚህም ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥረት ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ በሚገኝ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ አዲስ ፡ ቅንጅት ፡ ብናስገባ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለው ፡ አደጋ ፡ ከፍተኛነት ፡ በጥቂቱ ፡ የማይገመት ፡ ድንገተኛ ፡ ለውጥ ፡ (ሬቮሊሲዮን) እንደማነሳሳት ፡ የሚቆጠር ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በራሳችን ፡ የግል ፡ አስተያየት ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ወንጀለኛ ፡ ሕጋዊ ፡ የአካለ ፡ መጠን ፡ ዘመን ፡ ማለት ፡ በወንጀል ፡ ሕግና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በኢዴዎሎጂክ ፡ (የሰው ፡ ልጅ ፡ ሐሳቦችና ፡ ተምኔቶች ፡ የመሻሻል ፡ እድገት ፡ ፍልስፍና) እስኪተወሰነው ፡ ወይም ፡ ፍጹም ፡ እስኪሆነው ፡ የአካለ ፡ መጠን ፡ መድረሻ ፡ አማካይ ፡ ዘመን ፡ መካከል ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ የሚወሰንበትን ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ አጠባበቅን ፡ ተግባር ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ (ቍ ፡ ፩፻፹፩) (በስዊስ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፩፻) በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተሠራው ፡ ቅንጅት ፡ በቂ ፡ ስላልሆነ ፡ ተሻሽሎ ፡ መሠራት ፡ የሚገባው ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተሠራው ፡ የቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ አጠባበቅ ፡ ውሳኔ ፡ ቅንጅት ፡ በወጣቱ ፡ ወንጀ

62 ረቮዊ ፡ ፔናል ፡ ሱዊስ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ ልዩ ፡ ቍጥር ፡ ስለ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጀርማን ፡ ምስጋና ፡ ባደረግነው ፡ ድርሰት ፤ ስለ ፡ አላፊነት ፡ ጉዳይ ፡ የወንጀል ፡ ክፍል ፡ ዳኛ ፡ ሥራና ፡ ተግባር ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በጻፍነው ፡ በገጽ ፡ ፪፻፵፮ ፡ ተመልከት ፡ (ግራቨን) ።

ለኛ ፡ ላይ ፡ የግዴታ ፡ የሆነ ፡ የማሥልጠን ፡ ወይም ፡ በሕክምና ፡ የማዳን ፡ ጠንካራ ፡ ውሳኔ ፡ በመሆን ፡ ፋንታ ፡ (ቅጣቱን ፡ የማቅለል ፡ ደንብ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ) አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሰ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ጥበቃ ፡ ልክ ፡ እንዲቀጣ ፡ በማድረግ ፡ ቅንጅት ፡ መተካት ፡ ይገባዋል ፡ ብለን ፡ እንገምታለን ፤ ስለሆነም ፡ በዚህ ፡ ትንጅት ፡ አሠራር ፡ ረገድ ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፡ ሳይስማሙበት ፡ ገና ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ ይህን ፡ ቅንጅት ፡ ሌሎቹ ፡ እንዲከተሉ ፡ ለዓለም ፡ ተቀዳሚ ፡ ምሳሌ ፡ መስጠት ፡ የግዴታ ፡ ተግባሩ ፡ ያለመሆኑ ፡ የታመነ ፡ ነው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያደረገው ፡ እርምጃ ፡ እጅግ ፡ አጥጋቢ ፡ ነው ፡ የሚያሰኘው ፡ ወጣቱ ፡ ወንጀለኛ ፡ በሰውነቱ ፡ አስተዳደግና ፡ በአእምሮው ፡ መጐልመስ ፡ ረገድ ፡ የአካለ ፡ መጠን ፡ ዕድሜ ፡ ለማድረስ ፡ ብዙ ፡ ያልራቀ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ እንዳልሆነ ፡ ልዩ ፡ መርማሪው ፡ እንዳቀረበው ፡ አሳብም ፡ ለታናናሾች ፡ በደለኞች ፡ ለተመደበው ፡ ለሕክምና ፤ ለትምህርት ፡ ሥልጣኔ ፡ ለጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ጉዳይ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ማለት ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ለመመለስ ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ሊሰጥ ፡ ስለሚገባው ፡ ውሳኔ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ ቅንጅት ፡ ለመመሬት ፡ ወይም ፡ በወጣቱ ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባውን ፡ ቅጣት ፡ መርጦ ፡ ለመወሰን ፡ የሚችልበትን ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ በመሆኑ ፡ ነው ፡ (ቍ ፡ ፩፻፹፪) [63] ።

(መ) ያለፉት ፡ ዘመናት ፡ ያወረሱንን ፡ መታሰቢያዎች ፡ በማስታወስና ፡ ለኢትዮጵያም ፡ ባሕል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ልማዶች ፡ ጠቃሚነት ፡ ባለመዘንጋት ፡ እነዚሁኑ ፡ መሠረታዊያን ፡ ነገሮችን ፡ የመከተል ፡ ግዴታችንን ፡ በሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነጥቦች ፡ ላይ ፡ ባሰፈርናቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ ገልጸናቸዋል ። ይህንኑም ፡ ለመረዳት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የታሪክ ፡ ቅርስ ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ በመኖር ፡ ከጥቂት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የነበረውንና ፡ አሁንም ፡ ያለውን ፡ ጽኑ ፡ እምነት ፡ በመከተል ፡ ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሕይወት ፡ አጠባበቅ ፡ በተመለከተው ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ አጻጻፍ ፡ (ቍ ፡ ፪፻፵፰ ፡ እና ፡ ተከታዩ) ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ (ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር) መሆኑና ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ ተያይዞ ፡ ከመጣው ፡ ትውልድ ፡ የተገኘ ፡ መሆኑም ፡ ከብዙ ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ ያለውን ፡ የታሪክ ፡ እምነት ፡ በመከተል ፡ የተሠራ ፡ መሆኑን ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ጉዳዮችን ፡ በያዙት ፡ ነጥቦች ፡ ላይ ፡ ሕጉ ፡ የተከተለው ፡ የአጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ ለምሳሌ ፡ ባለዋጋ ፡ ማዕድኖችንና ፡ ዕንቍዎችን ፡ ያላግባብ ፡ ስለ ፡ ማዘዋወርና ፡ በነዚህ ፡ ስለ ፡ መነገድ (ቍ ፡ ፫፻፶፰ ፡ እና ፡ ፯፻፵፩) የሀገር ፡ ንብረት ፡

---

[63] ረቩዊ ፡ እንቴርናሲዮናል ፡ ደ ፡ ክሪሚኖሎዢ ፡ ኤ ፡ ፖሊስ ፡ ቴክኒክ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ወንጀለኞች ፡ ዳኛ ፡ የሆኑት ፡ ቢቦ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ቍ ፡ ፩፻፲፫ ፡ በጻፉት ፡ አርዕስተ ፡ አንቀጽ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የሰጠነውን ፡ የኛን ፡ አስተያየት ፡ ተመልከት ። ለዲፋንስ ፡ ሶሲያል ፡ ጉዳይ ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ስቶክሆልም ፡ ስብሰባ ፡ ያደረገው ፡ እንቴርናሲዮናል ፡ ኮንግሬስ ፡ በዚሁ ፡ ወጣት ፡ ወንጀለኞችን ፡ በሚመለከት ፡ ነገር ፡ ክርክር ፡ አድርጎ ፡ ነበረ ፤ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ዘንድ ፡ የዚሁ ፡ ክፍል ፡ ሹም ፡ የሆኑት ፡ ኤም ፡ ሎፔዝ ፡ ሬይ ፡ በዚሁ ፡ መጽሔት ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በገጽ ፡ ፳ ፡ ላይ ፡ የሰጡትን ፡ መግለጫ ፡ ተመልከት ። እንዲሁም ፡ ዶክተር ፡ ሼስኒ ፡ በዚሁ ፡ ነጥብ ፡ ላይ ፡ ዝንቶ ፡ ያቀረቡት ፡ የሱዊስ ፡ ራፖር ፡ እንዳመለከተው ፡ የዕድሜ ፡ አወሳሰን ፡ ደረጃ ፡ ሲስቴም ፡ እጅግ ፡ ጥብቅ ፡ በመሆን ፡ ፋንታ ፡ በመጠኑ ፡ እንዲላላና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫን ፡ መንፈስ ፡ እንዲከተል ፡ አሳስቧል ። በዚያው ፡ መጽሔት ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ቍ ፡ ፪፻፶፬ ፡ ተመልከት ። የዚህንም ፡ ፕሮብሌም ፡ ፍች ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የስዊስን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለማሻሻል ፡ የተቋቋመው ፡ ኮሚሲዮን ፡ ሊከተለው ፡ ይገባል ፡ ተብሎ ፡ የቀረበ ፡ ሀሳብ ፡ ነው ፤ ረቩዊ ፡ ደ ፡ ሲያንስ ፡ ክሪሚኔል ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ድሯ ፡ ፔናል ፡ ኮምፓሬ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፤ ስለሱዊስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የዛሬ ፡ እርማት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ጀርማን ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በቍ ፡ ፯፻፶፬ ፡ እና ፡ በተከታዩ ፡ የጻፈውን ፡ ተመልከት ። ይህም ፡ እስካሁን ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም ።

የሆኑትን ፡ ታሪካዊና ፡ ጥበባዊ ፡ ነገሮችን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶችን ፡ ደኖችንና ፡ የዱር ፡ አውሬዎችን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ (ቍ ፡ ፯፻፫ ፡ እና ፡ ፯፻፬) የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይህን ኑ ፡ ሙንፈስ ፡ በንግግር ፡ የሚገልጹ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሰውን ፡ የመጥ ለፍ ፡ በማይገባ ፡ ይዞ ፡ አገልጋይ ፡ የማድረግ ፡ በባርነት ፡ ስም ፡ ይዞ ፡ በግዴታ ፡ የማሠ ራት ፡ ወንጀል ፡ (ቍ ፡ ፯፻፶፯ ፡ እና ፡ ተከታዩ ፡ ቍ ፡ ፯፻፶፰) በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፡ ቅጣት ፡ ከባድ ፡ እንዲሆን ፡ እንዲሁም ፡ የሴሰኝነት ፡ ቁባት ፡ የማስቀመጥ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ የማድረግ ፡ ወንጀል ፡ (ከቍ ፡ ፯፻፲፮ ፡ እስከ ፡ ፯፻፲፰) በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ የሚወሰነው ፡ ቅጣት ፡ የተቃለለ ፡ እንዲሆን ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ የተከተለው ፡ የአ ጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ የነገሩን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታና ፡ የአገሩንም ፡ ባሕል ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የሰውን ፡ በሽታ ፡ በተጋቦት ፡ እንዲበዛ ፡ የማድረግ ፡ የከብ ትን ፡ በሽታ ፡ አራብቶ ፡ የማሰራጨት ፡ የሰብልን ፡ ወይም ፡ የደንን ፡ ትላትል ፡ በመንዛት ፡ ውሃን ፡ የማበላሸትና ፡ የመመረዝ ፡ ግጦሽን ፡ የማበላሸት ፡ በጠቅላላውም ፡ የጤና ፡ አጠባ በቅ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ በመተላለፍ ፡ ስለ ፡ ሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፯፻፫ ፡ እና ፡ ተከ ታዩ ፡ ቍ፡ ፯፻፬) ችግር ፡ ወይም ፡ ረኃብ ፡ እንዲመጣ ፡ የማድረግና ፡ በግጦሽ ፡ በሜዳና ፡ በደን ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ የተለቀቁ ፡ እንስሳትን ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ በመልቀቅ ፡ በግ ጦሽ ፡ በእርሻ ፡ ቦታና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የማይገባ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፯፻፵፱) ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ ባዘጋጀውና ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ባሰፈራቸው ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ የተከተለው ፡ የስፍራውን ፡ ሁናቴ ፡ የአገሩን ፡ ባሕል ፡ በክፍሉ ፡ የሚገኘውን ፡ የሀብት ፡ ዐይነትና ፡ የሕዝቡን ፡ የኑሮ ፡ የመተዳደሪያና ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡ በመገመትና ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ መሆኑን ፡ በሕጉ ፡ አጻጻፍ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ።

የመርዝነት ፡ አደጋን ፡ ሊያስከትሉ ፡ የሚችሉ ፡ ሥራይ ፡ የሚሆኑ ፡ ብናኝ ፡ ዱቄቶ ችን ፡ የተቀመሙ ፡ መጠጦችን ፡ ወይም ፡ ሌሎችን ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ በመስጠት ፡ በሰው ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በማድረስ ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፯፻፲፮) ለመከላከል ፡ ወይም ፡ በጥንቆላና ፡ በምትሐት ፡ ዘዴ ፡ የሚፈጸሙትን ፡ ወንጀሎች ፡ (በወገኖቻቸው ፡ መካከል ፡ የዚህን ፡ ሥራ ፡ የቆየ ፡ ልማድ ፡ በሚያጸድቀው ፡ መጠን ፡ ዕውቀት ፡ ከሥራ ፡ ልምድ ፡ ጋር ፡ ያላቸው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀላቸው ፡ ሰዎች ፡ በሀገሬው ፡ ዘዴ ፡ መድኀኒት ፡ ቢያደርጉ ፡ የማያስቀጣቸው ፡ መሆኑ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ) [ቍ ፡ ፯፻፲፯ ፡ (፩)] ፡ ወይም ፡ በጥንቆላ ፡ በጋኔን ፡ በርኩስ ፡ መናፍስት ፡ ልመና ፡ የወ ደፊቱን ፡ እተነባለሁ ፡ ብሎ ፡ በሰው ፡ እምነት ፡ በመጠቀም ፡ የተሸሸገ ፡ ገንዘብ ፡ አገኛለሁ ፡ የሚል ፡ ዘዴ ፡ አስመስሎ ፡ በማቅረብ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ የጥንቆላ ፡ ዘዴ ፡ ሰበብ ፡ በማድረግ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሰውን ፡ በማታለል ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፯፻፲፰) በሚወሰነው ፡ ቅጣትዋ ፡ ረገድ ፡ የአገርን ፡ ልማድና ፡ ባሕል ፡ በመከተል ፡ የተ ሠራ ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ ከባድ ፡ አይሆንም ። እንዲሁም ፡ ተቀጪው ፡ በራሱ ፡ መኖ ሪያ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እስራት ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰንበት ፡ ድንጋጌና ፡ (ቍ ፡ ፯፻፳) ፡ የሰዓት ፡ እላፊ ፡ ደንብ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ በሌ ሊት ፡ መዘዋወርን ፡ ስለመከልከል ፡ የተወሰነውን ፡ ሰዓት ፡ አክብሮ ፡ ስለመጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፯፻፳፩) በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተሰ ጠው ፡ ውሳኔ ፡ የተመሠረተው ፡ በቀጥታ ፡ በስፍራው ፡ ከሚገኘው ፡ አኗኗር ፡ ሕይወት ፡ የመነጨውን ፡ ልማዳዊ ፡ ስሜት ፡ በመከተል ፡ ነው ።

ሕጉ ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ ወንጀል ፡ በመቁጠርና ፡ የቅጣት ንም ፡ ውሳኔ ፡ እንዲያስከትሉ ፡ በማድረግ ፡ በየዓይነታቸውና ፡ በየመልካቸው ፡ ስፍራ ፡

አስይዞ ፡ ሲመድባቸው ፣ ምንም ፡ እንኳ ፡ አብዛኞቹ ፣ ጥንታዊውን ፡ ልማድ ፡ ከመከተል ፡ ግዴታው ፡ ውስጥ ፡ የመነጩ ፡ ቢሆኑ ፡ ለዘመናዊው ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆኑበትን ፡ ዘዴ ፡ አጥብቆ ፡ በመፈለግና ፡ በጉዳዩም ፡ እጅግ ፡ አርቆ ፡ በማሰብ ፡ በጠቅላላው ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ ገብ ፡ ሆነው ፡ መገኘታቸው ፡ እንዳይሰማና ፡ አወሳሰናቸውም ፡ የሚገባና ፡ ትክክል ፡ ማመዛዘኛ ፡ ፈሊጥ ፡ ቋሚ ፡ ዕውቀት ፡ (ሎጂክ) የሆነውን ፡ መንገድ ፡ እንዲከተል ፣ ላሮጌ ፡ ነገሮችም ፡ አዲስ ፡ መልክና ፡ ዘመናዊ ፡ ሕይወት ፡ በመስጠት ፡ የቅጣቱ ፡ አወሳሰን ፡ ከብሔራዊው ፡ ሕይወትና ፡ ጥቅም ፡ ጋር ፡ የተመዛዘነ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ በማድረግ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የተመራ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል ።

## ፫ ፤ የሕጉ ፡ አዲስ ፡ ጠባይና ፡ አዲስ ፡ መንፈስ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ሐተታዎች ፡ ተዘርዝረው ፡ የተመለከቱት ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ሕይወትን ፡ የሰጠው ፡ አዲሱ ፡ መንፈስ ፡ የትኛው ፡ እንደሆነ ፡ በበቂ ፡ ሁኔታ ፡ ገልጸው ፡ አስረድተዋል ።

ስለዚህ ፡ ከጠቅላላው ፡ የአሠራር ፡ ቅንጅት ፡ ሆነ ፡ ከልዩ ፡ ክፍሉ ፡ ተውጣጥተው ፡ በመጡት ፡ አንዳንድ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አማካይነት ፡ የተሰጡትን ፡ ማብራሪያዎች ፡ በቅርብ ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

የሕጉ ፡ አሠራር ፡ አጥፊ ፡ የሚቀጣው ፡ ከወንጀል ፡ ሥራው ፡ እንዲወገድ ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሲቀጣ ፡ ሌላው ፡ ተመልካች ፡ እንዲፈራ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ የሚባለውን ፡ ልማዳዊውን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የተከተለ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ማንኛውም ፡ ዘመናዊ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ያልደረሰበትን ፡ ነጥብ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ደረጃ ፡ በመድረስ ፣ ጥፋተኛን ፡ ከመቅጣት ፡ ይልቅ ፡ ወንጀል ፡ እንዳይሠራ ፡ መከላከል ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘመናዊ ፡ ጥበብ ፣ ሕጉ ፡ ለወንጀለኞች ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በመሆን ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥበትን ፡ ዘዴ ፣ ወደ ፡ በጐ ፣ ፈቃድ ፡ ሊመራ ፡ የሚችል ፡ ጠባይ ፡ የሚያሳይ ፡ ጥፋተኛ ፡ እንዲታረም ፣ እንዲሻሻልና ፡ ማኅበራዊው ፡ ጸጥታም ፡ በሚገባ ፡ ተጠብቆ ፡ ለመኖር ፡ እንዲችል ፡ ጠቃሚና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ዘመናዊ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በአዲስ ፡ ጥበብ ፡ አሻሽሎ ፡ ከመሥራት ፡ አልታገደም ።

ሕጉ ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሰጠው ፡ በድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ በመመራት ፣ ባልተረጋገጠና ፣ አጠራጣሪ ፡ በሆነ ፡ አስተያየት ፡ በመነሳሳት ፣ ወይም ፡ ከየቦታው ፡ ተውጣጥተው ፡ የተሰበሰቡ ፡ ቁርጥራጭ ፡ ማስረጃዎችን ፡ በመከተል ፡ አይደለም ፣ ነገር ፡ ግን ፡ እያንዳንዱን ፡ ነገር ፡ አጣርቶ ፡ በመመርመር ፣ የዛሬው ፡ ዘመን ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የአሠራር ፡ ጠባይ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ግዴታ ፡ በጥብቅ ፡ በመከተል ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፣ ጉዳዩን ፡ በሚገባ ፡ ተከታትሎ ፡ የተረዳ ፡ ማናቸውም ፡ ዳኛ ፡ ሁሉ ፡ የተቃናውን ፡ የአመራር ፡ መንገድ ፣ ሊከተል ፡ የሚችልበትን ፡ ዘዴ ፡ አብራርቶ ፡ በመግለጽ ፡ በጠባብ ፡ አነጋገር ፡ "ወንጀል" ፣ ወይም ፡ ወንጀለኛን ፡ መቅጣት ፡ ከሚለው ፡ ቋንቋ ፡ ይልቅ ፡ ወንጀል ፡ እንዳይሠራ ፡ መከላከልንና ፡ ወንጀል ፡ ሠሪው ፡ ከጥፋተኛነት ፡ እንዲወገድ ፤ እንዲታረም ፡ ወደሚለው ፡ ስሜት ፡ በማዘንበል ፡ (በማድላት) መመራት ፡ የሚቻልበትን ፡ ጠቅላላ ፡ ዘዴ ፡ አጣርቶና ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመከተል ፡ ነው ። ይህም ፡ ዐላማ ፡ ተፈላጊውን ፡ ውጤት ፡ እንዲያገኝና ፡ ወደ ፡ ታሰበው ፡ ግብ ፡ እንዲደርስ ፡ ሊያደርገው ፡ የሚችለው ፡ የጥንቃቄ ፡ አጠባበቅንና ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰንን ፡ ደንብ ፡ በተሻላ ፡

አስተዳደር ፡ አጠቃለው ፡ በመያዝ ፡ የተሠሩትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለማስፈጸም ፡ ቁርጠኛ ፡ ሆኖ ፡ የተነሳ ፡ ያመራር ፡ ሥልጣን ፡ ነው [64] ።

(ሀ) የተቋቋሙበትን ፡ ዓላማ ፡ ማለት ፡ ጉዳዩና ፡ ግባቸውን ፡ ሆነ ፡ ያነሳሳቸውና ፡ የመራቸውን ፡ ጠቅላላ ፡ መንፈስ ፡ እንደሚገልጹና ፡ አፈጻጸማቸውንም ፡ ከሌላ ፡ ዘንድ ፡ መጠየቅ ፡ እንዳለባቸው ፡ ብዙዎች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጎች ፡ በአሠራራቸው ፡ የተከተሉትን ፡ መንገድ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ አዲሱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ የሠራው ፡ ሕግ ፡ አውጪ ፡ የሕጉን ፡ ጠቅላላ ፡ ቅንጅት ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በማብራራት ፡ ዳኞች ፡ የሚመሩበትን ፡ ትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ በመክፈትና ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ማስፈጸም ፡ ውሳኔዎች ፡ በሕጉ ፡ መንፈስና ፡ ሕጉ ፡ ሊደርስበት ፡ ያሰበውን ፡ ዓላማ ፡ ለማረጋገጥ ፡ በሚቻልበት ፡ ሁኔታ ፡ መፈጸም ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑን ፡ በማስረዳት ፡ (ቍ ፡ ፹፩ ፡ ፩ኛ ፡ መስመር) ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ በማናቸውም ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮ ፡ የሚገባውን ፡ ክብር ፡ ሁሉ ፡ አክብሮ ፡ መጠበቅ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ማለት ፡ ሕጉ ፡ በጠቅላላው ፡ ለወንጀለኞች ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መሆኑንና ፡ ማስጠንቀቂያው ፡ በቂ ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ የወንጀል ፡ ሥራን ፡ የመድጋገም ፡ ተግባር ፡ እንዳይፈጸም ፡ ለመከላከል ፡ ወንጀለኞችን ፡ መቅጫ ፡ ከጥፋትና ፡ ወንጀልን ፡ ከመድጋገም ፡ እንዲድኑ ፡ ማድረጊያ ፡ (ቍ ፡ ፩) መሆኑን ፡ ዳኞች ፡ እንዲያውቁት ፡ በግልጽ ፡ በማመልከት ፡ የሕጉ ፡ ጉዳይና ፡ ግብ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ በተብራራ ፡ ሁኔታ ፡ አስረድቷል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ሰውን ፡ "የሚያሰቅቁ" ፡ የሰውን ፡ ክብር ፡ ጨርሶ ፡ "የሚያዋርዱ" ቅጣቶች ፡ መኖር ፡ የለባቸውም ፡ ማለት ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ካለ ፡ ግን ፡ ሕጉ ፡ የተመሠረተበትን ፡ ሕንጻ ፡ አስ ቀድሞ ፡ እንደማፍረስ ፡ ይቆጠራል ።

ቅጣት ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፡ በያንዳንዱ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ የአጥፊውን ፡ ሁኔታና ፡ የጥፋቱን ፡ መጠን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመከተል ፡ የወንጀለኛውን ፡ የአደገ ኛነት ፡ ጠባይ ፡ እንደመጠኑ ፡ በመገመት ፡ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ በመመርመር ፡ ለማጥፋት ፡ ያነሳሱትን ፡ ምክንያቶችና ፡ የአሳቡን ፡ ዓላማ ፡ የግል ፡ ኑሮውን ፡ ሁኔታና ፡ የትምህርቱን ፡ ደረጃ ፡ የጥፋቱን ፡ ከባድነትና ፡ ያፈጸመውን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመገመት ፡ በራሱ ፡ የግል ፡ አጥፊነት ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ (ቍ ፡ ፹፯) ተብሎ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገል ጿል ፤ ይህንንም ፡ ማለት ፡ ቅጣትን ፡ በአጥፊው ፡ (ወንጀሉን ፡ በፈጸመው) ሰው ፡ በራሱ ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ ቅጣትን ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ በግንባር ፡ የማይደላደል ፡ ግዴታና ፡ የፍርድ ፡ አወሳሰን ፡ መደበኛ ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ማለት ፡ ነው [65] ።

ተጨማሪ ፡ ቅጣቶችንና ፡ አዲሱ ፡ የወንጀል ፡ (የክሪሚኖሎጂ) ፖሊቲካ ፡ ሊደርስ በት ፡ ወዳሰበው ፡ ግብ ፡ ለመመራት ፡ በሚቻልበት ፡ ሁኔታ ፡ ተቀምረውና ፡ በሚገባ ፡ ቅንጅት ፡ ተጠናቀው ፡ በመብራራት ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተገለጹትን ፡ የማስጠንቀቅንና ፡

---

64 የዘመናዊ ፡ ክሪሚኖሎጂክን ፡ መሠረታዊያን ፡ አሳቦች ፡ በፖሊቲፍ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ የሚለውን ፡ አሳብ ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ ሎዛን ፡ የተሰጠው ፡ በ፯ኛው ፡ የኢንቴርናሲዮናል ፡ ክሪሚኖሎጂክ ፡ የትምህርት ፡ ጥናት ፡ ምርምር ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ በሱዊስና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጐች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በማስተያየት ፡ በተደረገው ፡ ምርመራ ፡ ላይ ፡ በመመሥረት ፡ ክግራቨን ፡ የተሰጠውን ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ ተመልከት ። ይኸውም ፡ በእስፓኝ ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጉሞ ፡ አኑዋሪዮ ፡ ዲ ፡ ዴሬቾ ፡ ፔናል ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በቍ ፡ ፫ ፡ በገጽ ፡ ፬፻፹፫—፭፻፲ ፡ ታትሞ ፡ ይገኛል ።

65 ስለዚሀ ፡ ጉዳይ ፡ በኢንቴርናሲዮናል ፡ ሕጎች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ እያመሳከሩ ፡ ስለመመ ርመር ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ሉክሳምቡርግ ፡ በተደረገው ፡ የኢንቴርናሲዮናል ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የትምህርትና ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ የግራቨንን ፡ ማብራሪያ ፡ (መግለጫ) ተመልከት ።

የመጠበቅን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ነገሮችም ፡ እንደዚሁ ፡ እነዚህን ፡ ውሳኔዎች ፡ ለዋነኛው ፡ ቅጣት ፡ ተደራቢና ፡ ማሟያ ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ የሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚወስኑዋቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ተሟልተው ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ የቅጣቱን ፡ ዓላማና ፡ በተቀጭው ፡ ላይ ፡ ሊያደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ የጥበቃና ፡ የጠባይ ፡ ማረም ፡ ዝንባሌ ፡ በመከተል ፡ ከጥፋት ፡ እንዲወገድና ፡ እንዲጠበቅ ፡ ወይም ፡ በትምህርት ፡ እንዲሠለጥንና ፡ በሕክምና ፡ እንዲድን ፡ ለማድረግ ፡ መሆኑን ፡ በማስረዳት ፡ ይህም ፡ ሲሆን ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ቅጣቶች ፡ መወሰን ፡ ባስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የነገሩን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ መከተል ፡ እንጂ ፡ የሕጉ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ በየጊዜውና ፡ በየሥራው ፡ ዘርዝሮ ፡ እንዲያመለክት ፡ አስፈላጊ ፡ ያለመሆኑን ፡ ጭምር ፡ በማስረዳት ፡ ሕጉ ፡ አመልክቷቸው ፡ ይገኛል ፡ (ቍ ፡ ፩፻፰ ፡ እና ፡ ፩፻፴፰) ። ይህ ፡ ቅንጅት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚውልበት ፡ አፈጻጸም ፡ በኩል ፡ አስቸጋሪ ፡ መሆኑ ፡ በእርግጥ ፡ የታመነ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ጉዳዩ ፡ ሊያስገኝ ፡ የሚችለውን ፡ ውጤት ፡ በሕሊናቸው ፡ በሚገባ ፡ ለመረዳት ፡ በቂ ፡ ንማችነት ፡ ያላቸው ፡ የሕጉን ፡ መንፈስ ፡ የመከተልና ፡ በዚህም ፡ ለመጠቀም ፡ ሕጉን ፡ እንደልብ ፡ ወደ ፡ ግቡ ፡ ለመምራት ፡ የሚበቃ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ በሕግ ፡ ልምድም ፡ ረገድ ፡ የአርቆ ፡ ማስተዋልን ፡ ችሎታ ፡ አሟልተው ፡ የያዙ ፡ ዳኞች ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊዎች ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ በግንባር ፡ ማለት ፡ አጥፊ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንዲደርስ ፡ የግል ፡ ማድረግን ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃና ፡ የሥልጣን ፡ መደብ ፡ የሚገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ሊከተለው ፡ የሚገባው ፡ ዋነኛው ፡ ዓላማ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ አይደለምን ?

(ለ) በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ በተደራጀው ፡ ጠቅላላ ፡ መደብ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ልዩ ፡ ልዩዎቹ ፡ ቅጣቶችና ፡ የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ የማስፈጸም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሁሉ ፡ የተሠሩት ፡ የማደስን ፡ መንፈስ ፡ በተከተለ ፡ ነው ።

በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ የሚደረገው ፡ ቅጣትም ፡ የሚወሰነው ፡ ዘወትር ፡ ከተቀጭው ፡ አቅም ፡ ጋር ፡ የተመዛዘነ ፡ ሊሆን ፡ የሚችልበትን ፡ ዘዴ ፡ በመፈለግ ፡ የተቀጭውን ፡ የትዳር ፡ ሁኔታና ፡ የሀብቱን ፡ ምንጭ ፡ ስለቤተሰቦቹ ፡ አስተዳደር ፡ ያለበትን ፡ ሸክም ፡ የሞያ ፡ ሥራውንና ፡ በዚህም ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለውን ፡ ጥቅም ፡ በመገመትና ፡ ቅጣቱም ፡ ከፈጸመው ፡ ጥፋት ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ መሆን ፡ እንደሚገባው ፡ (ቍ ፡ ፹፰) አከፋፈሉም ፡ ደግሞ ፡ ተቀጭው ፡ የተወሰነበትን ፡ መቀጮ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ በማድረግ ፡ የተቀጭውን ፡ መብት ፡ በሚገባ ፡ የጠበቀና ፡ ገንዘቡም ፡ መከፈሉ ፡ እንዳይቀር ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችልበትን ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ በየደረጃው ፡ መድቦታል ፡ (ከቍ ፡ ፺፩ ፡ እስከ ፡ ፺፮) ። ይህም ፡ አሠራር ፡ የአገሩን ፡ የኤኮኖሚክ ፡ ዕድገት ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ሥርዓት ፡ ጥቅምን ፡ እንዲያስገኝ ፡ አጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ እንዲያስከትልና ፡ በትክክለኛ ፡ የፍርድ ፡ መንፈስ ፡ የተመራ ፡ እንዲሆን ፡ አድርጎታል ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደገለጽነው ፡ ሁሉ ፡ የተቀጭው ፡ የግል ፡ ነፃነት ፡ ሳይነካ ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ የመቆጣጠር ፡ ጥንቃቄ ፡ ስር ፡ ሆኖ ፡ በሚያከናውነው ፡ የጉልበት ፡ ሥራ ፡ ከሚያገኘው ፡ ደመወዙ ፡ እየተቀነሰ ፡ መቀጫውን ፡ ገቢ ፡ እንዲያደርግ ፡ የሚወሰነው ፡ ቅጣትም ፡ እንደዚሁ ፡ ጥንታዊ ፡ ሆኖ ፡ የዘመናዊውን ፡ ሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ የተከተለ ፡ ስለሆነ ፡ (ከቍ ፡ ፩፻፪ ፡ እስከ ፡ ፩፻፫) ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ለጠቅላላው ፡ የሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሚውለውን ፡ የሥራ ፡ ክንውን ፡ የሚያሟላው ፡ ሲሆን ፡ ወዲያውም ፡ ተቀጭው ፡ ገንዘቡን ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ ቢሰጠውም ፡ ለመክፈል ፡ ያቃተው ፡ እንደሆነ ፡ ቅጣቱን ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ በሚያሳጣ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ እሥራት ፡ በመወሰን ፡ ፋንታ ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ በማሠራት ፡ ለመለወጥ ፡ የሚያስችል ፡ ይሆናል (ቍ ፡ ፺፱) ። የግል ፡ ነፃነትን ፡ የሚያሳጣ ፡ ቅጣት ፡ (ቍ ፡ ፩፻፭ ፡

እና ፡ ተከታዩ) ፣ አወሳሰን ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተደነገገው ፡ ከባድነቱ ፡ መካከለኛ ፡ የሆነ ፡ ወንጀልን ፡ በሠራና ፡ ጥፋተኛውም ፡ እጅግ ፡ አደገኛ ፡ ሆኖ ፡ የማይገመት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከጥፋቱ ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሚሆን ፡ እሥራት ፡ ስለሆነ ፡ እጅግ ፡ የተራቀቀውን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ አስተዳደር ፡ በመከተል ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ወንጀል ፡ ሠሪውም ፡ የሚቀጣው ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ እንዲመለስ ፡ ወደ ፡ ማድረግ ፡ ዘዴ ፡ በማዘንበል ፡ ነው ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ በእሥራቱ ፡ ጊዜ ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ የማሠራት ፣ በትምህርት ፡ የማሠልጠንና ፡ የመንፈሳዊ ፡ እርዳታ ፡ በመስጠትም ፡ የአእምሮ ፡ ማጐልመሻ ፡ ትምህርት ፡ እንዲያገኝ ፡ በማድረግ ፡ የተቀጭውን ፡ ጠባይ ፡ የማሻሻልን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ የተረጋገጠ ፡ ውጤት ፡ እንዲያስገኝ ፡ በማድረግ ፡ ነው ፡ (፩፻፱ ፡ እና ፡ ፩፻፲) ፡፡ ይህም ፡ እጥፍ ፡ የሆነውን ፡ ቅጥ ፡ የያዘ ፡ አሠራር ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ንድፈ-ሐሳባዊ ፡ (ቲዎሪክ) የሆነው ፡ ጠቅላላ ፡ ጠባዩ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ በሚችልበት ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ቅጣት ፡ ያስከተለው ፡ ወንጀል ፡ ቢያንስም ፡ ቢያድግም ፡ የከባድነቱ ፡ አደገኛነትና ፡ ይህ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሠራ ፡ ለመከላከል ፡ የተረጋገጠ ፡ ዋስትና ፡ ለማግኘት ፡ የሚቻልበት ፡ ሙንገድ ፡ ተገኝቶ ፡ በተግባር ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የማድረግን ፡ ዓላማና ፡ የሚያስገኘውም ፡ ውጤት ፡ ተፈላጊውን ፡ ፍሬ ፡ ሊሰጥ ፡ ወደሚችልበት ፡ ግብ ፡ እንዲደርስ ፡ ለማድረግ ፡ የሚጠቅም ፡ ነው [ቍ ፡ ፩፻፳ ፡ (፩) እና ፡ ቍ ፡ ፩፻፳፪ ፡ (፩)] ፡፡ ወንጀልን ፡ እንደሞያ ፡ ሥራቸው ፡ አድርገው ፡ የያዙ ፡ የማይታረሙ ፡ ጥፋተኞች ፡ ቢያንስም ፡ ቢበዛም ፡ እንደመጠኑ ፡ ረጅም ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡ ግዞት ፡ እንዲወገዱ ፡ ተደርጓል ፡ (ቍ ፡ ፩፻፹፰ እና ፡ ተከታዩ) ፤ እንዲሁም ፡ በአእምሮ ፡ ጐደሎነት ፡ በመንፈስ ፡ መናወጽ ፡ (በእብደት) ፡ ምክንያት ፡ አላፊነት ፡ የሌላቸው ፡ አላፊነታቸው ፡ የተቀነሰ ፡ ወንጀለኞች ፡ ለነዚሁ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነው ፡ የሕክምና ፡ አጠባበቅ ፡ ወይም ፡ የጥንቃቄ ፡ ጥበቃ ፡ ተግባር ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ በሕጉ ፡ ተወስኗል ፡ (ቍ ፡ ፩፻፴፫ ፡ እና ፡ ተከታዩ) ፡፡

የቅጣትን ፡ ማቆም ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሳኔዎችም ፡ ቅጣቱ ፡ እንዳይፈጸምም ፡ ሆነ ፡ የቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ለጊዜው ፡ ታግዶ ፡ እንዲቆይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ብይን ፡ (ቍ ፡ ፩፻፺፭) ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸም ፡ ጊዜ ፡ ስለመስጠት ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ [66] ፡ ለጥፋቱ ፡ መነሻ ፡ የሆኑትን ፡ ምክንያቶች ፡ በጠቅላላው ፡ በመመልከት ፡ በጥፋተኛ ው፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ለጊዜው ፡ ታግዶ ፡ እንዲቆይ ፡ ማድረግ ፡ የወንጀለኛውን ፡ ጠባይ ፡ ለማረምና ፡ ለማሻሻል ፡ ወደ ፡ ደንበኛው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ለመመደብ ፡ ጠቃሚ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ስለመሆኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ እምነት ፡ የሚያገኝ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ሙንገድ ፡ እንዲከተል ፣ እንዲሁም ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ አስቀድሞ ፡ ምርመራ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ ምርመራ ፡ ተደርጎ ፡ ተፈላጊው ፡ ውጤት ፡ እንዲቀርብ ፡ በማዘዝና ፡ የቀረበው ፡ የምርመራ ፡ ውጤት ፡ ያመለከተውን ፡ በመከተል ፡ (ቍ ፡ ፩፻፺፱) በአጥፊው ፡ ላይ ፡ የተወሰነበት ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸምበት ፡ የማድረግን ፡ ውሳኔ ፡ የመስጠትን ፡ (ከቍ ፡ ፩፻፩ ፡ እስከ ፡ ፩፻፫) ዓላማ ፡ ተከትሏል ፡፡

ይህንንም ፡ ጉዳይ ፡ የሕጉ ፡ ድንጋጌ ፡ ገልጾ ፡ እንዳመለከተው ፡ ሁሉ ፡ ቅጣትን ፡ በማቆም ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ጥርጣሬም ፡ ሆነ ፡ አወሳሰኑ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ አልፎ ፡ የመጠቀ

---

66 ይህ ፡ አሠራር ፡ የእንግሊዝን ፡ የፕሮቤሺን ፡ ሲስቴምና ፡ ቅጣትን ፡ ስለማቆም ፡ በኮንቲናንታል ፡ ሕግ ፡ ስለተመለከተው ፡ ሲስቴም ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ኤር ፡ ቤርዢር ፡ ዠኔቭ ፡ በጻፈው ፡ ቴስስ ፡ ላይ ፡ ያቀረበውን ፡ አሳብ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡ እኛ ፡ ራሳችን ፡ (ግራቨን) በዠኔቭ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የትምህርት ፡ ሥራ ፡ ጥርቅም ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በሱዊስ ፡ ሕግ ፡ ቅጣትን ፡ በገደብ ፡ የማቆም ፡ (የማገድ) ሲስቴም ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ቢሐሳቡ ፡ ማጠቃለያ ፡ በገጽ ፡ ፩፻፳ ፡ እና ፡ ረቩዊ ፡ ፔናል ፡ ሲዊስ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ ልዩ ፡ ቍጥር ፡ ስለፕሮፌሰር ፡ ቶርማን ፡ ምስጋና ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በቍ ፡ ፫ ፡ ባደረግነው ፡ ድርሰት ፤ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የታደሰ ፡ ሲስቴም ፡ በሚል ፡ መነሻ ፡ የሰጠነውን ፡ መግለጫ ፡ ተመልክት ፡፡

ምን ፡ ተግባር ፡ እንዳያስከትል ፡ ከተቀጭው ፡ የመታረምን ፡ መልካም ፡ ፈቃደኛነትና ፡ የራሱን ፡ እርዳታ ፡ የሚያስፈልግ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ውሳኔው ፡ የታሰበውን ፡ ውጤት ፡ ለማስገኘት ፡ ያለመቻሉ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ እንዲቋረጥ ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ ጭምር ፡ አስረድቷል ፡ (ቍ ፡ ፩፻፷፬) እንዲሁም ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ ስለመለቀቅ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ እስረኛው ፡ የእሥራቱን ፡ ቅጣት ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በሚያሳየው ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ከእሥራት ፡ ሲለቀቅም ፡ ለመልካም ፡ ጠባዩ ፡ የተወሰነ ፡ ዋስትና ፡ ሰጥቶ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከእሥራቱ ፡ ተለቆ ፡ እንዲቆይ ፡ የሚያደርግ ፡ ደንብ ፡ ሲሆን ፡ (ቍ ፡ ፪፻፯ ፡ እና ፡ ፪፻፲) ይህም ፡ የሕጉ ፡ ፍጹም ፡ ጠቅላላ ፡ የሆነ ፡ ገደብ ፡ ነው ። በአመክሮ ፡ የመለቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ በቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የተቀጭውን ፡ ጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊው ፡ ኑሮ ፡ መደብ ፡ እንደገና ፡ መመለሻ ፡ ሲሆን ፡ ሊወሰን ፡ የሚቻለውም ፡ ተቀጭው ፡ ለዚህ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑና ፡ አፈጻጸሙም ፡ እርግጠኛ ፡ ውጤትን ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ስለሆነና ፡ (ቍ ፡ ፪፻፰) እንዲሁም ፡ ቅጣትን ፡ የማቆምና ፡ እንደገና ፡ የመሰየም ፡ ውሳኔዎች ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ያስገኛሉ ፡ ተብሎ ፡ እንደሚገመተው ፡ (ቍ ፡ ፪፻፶፪ ፡ እና ፡ ተከታዩ) ፡ ይህንን ፡ ውሳኔ ፡ ለማግኘትም ፡ ተቀጭው ፡ በማንኛውም ፡ ሁኔታ ፡ ለዚህ ፡ ብቁ ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ የተገለጸው ፡ እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ ቅንጅት ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ጠባያት ፡ የያዙ ፡ እንደመሆናቸው ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ የደረሱትን ፡ ጉዳቶች ፡ ለመካስ ፡ ወንጀለኛውም ፡ ከመጥፎ ፡ ጠባዩ ፡ እንዲታረም ፡ ለማድረግ ፡ መሠረታዊ ፡ ዋስትናዎች ፡ እንደሆኑ ፡ ስለ ሚቆጠሩ ፡ ነው ።

በመጨረሻውም ፡ ዕድሜያቸው ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ እስኪሞላ ፡ ድረስ ፡ በወላጆቻቸው ፡ ወይም ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ሥር ፡ የሚጠበቁ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ትንንሽ ፡ ልጆች ፡ ጥፋት ፡ በሠሩ ፡ ጊዜ ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ ከአገሩ ፡ የኑሮ ፡ ዕድገት ፡ ደረጃ ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ የአካለ ፡ መጠን ፡ ማድረሻ ፡ ተብሎ ፡ እስከተወሰነው ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ የሰውነት ፡ አስተዳደጋቸው ፡ ወይም ፡ በአእምሮ ፡ የመብሰል ፡ ጠባያቸው ፡ የሚያሳስብ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ለሕጋዊ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ማድረሻ ፡ እስከተወሰነው ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ሲደርሱ ፡ እንዲሆን ፡ በሕጉ ፡ ተደንግጓል ፤ ቅጣቱም ፡ እንደ ተግሣጽ ፡ እንደ ፡ ወቀሳ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በሚፈጸም ፡ የማረፊያ ፡ ቤት ፡ እሥራት ፡ በቁጥጥር ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጸም ፡ በትምህርት ፡ የመሠልጠን ፡ አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ የተገመተ ፡ ሲሆን ፡ የአለንጋ ፡ (የአርጩሜ) ቅጣት ፡ ነው ፡ (ቍ ፡ ፩፻፸፪) ። የጥንቃቄ ፡ ተግባር ፡ ማስፈጸም ፡ ቅጣትም ፡ ቢኖር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዳስፈላጊነቱ ፡ መጠን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ ሊለውጠው ፡ የሚችልበት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል ፡ (ቍ ፡ ፩፻፷፩ ፡ እና ፡ ተከታዩ) ። በቍጥር ፡ ፩፻፸፫ ፡ የተመለከተው ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ወንጀል ፡ ካላጋጠመ ፡ በቀር ፡ የቅጣቱን ፡ ውሳኔ ፡ አግዶ ፡ የማቆየትና ፡ በጠቅላላው ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ የጠባዩ ፡ ምርምር ፡ ፈተና ፡ የማድረግ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጣቸው ፡ ይቻላል ፤ ይህም ፡ የሚደረገው ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ አፈጻጸም ፡ መልካም ፡ ፍሬን ፡ ለማስገኘት ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ በተገመተ ፡ ቍጥር ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ጥፋቱ ፡ እጅግ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ቅጣትን ፡ የማስቀረት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ፡ አስፈላጊ ፡ ያለመሆኑን ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ የማግባት ፡ ሥርዓት ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የተገመተ ፡ እንደሆነ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ይቻላል ፡ (ቍ ፡ ፩፻፸፩) ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ከሆኑት ፡ ወንጀሎች ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ተቀጭዎቹ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ተመልሰው ፡ በመሻሻል ፡ ወደ ፡ ደንበኛው ፡ የማኅበ

ራዊ ፡ ኑሮ ፡ የሚመደቡበትን ፡ የመሻሻል ፡ መንፈሳቸውን ፡ እንዳያሰናክልባቸው ፡ ከብ ሔራዊ ፡ መብት ፡ የመገፈፍ ፡ ውሳኔ ፡ እንዳይደርስባቸው ፡ ተደርጓል ፡ (ቍ ፡ ፩፻፳፪) ።

(ሐ) ከዋናዎቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ውሳኔ ፡ ጋር ፡ በመዋሐድ ፡ የተሠራው ፡ የተ ጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ የጥንቃቄና ፡ የጥበቃ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የሆነውም ፡ ውሳኔ ፡ አሠ ራር ፡ ሰፊ ፡ ቅንጅት ፡ ፍጹም ፡ ወደሆነ ፡ የመሻሻል ፡ እርምጃና ፡ በሚገባ ፡ ወደተደራጀ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የሚያደርስ ፡ ድንጋጌ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ውስጥ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጉዳዮች ፡ ይገኙበታል ።

1ኛ ፤ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ወቀሳ ፡ የተግሣጽ ፡ ማስጠንቀቂያና ፡ እንዲያውም ፡ ዘወትር ፡ ጠቃሚ ፡ በመሆኑ ፡ በአሁኑ ፡ አሠራር ፡ ጠቅላላ ፡ ሲስቴም ፡ ውስጥ ፡ እንደገና ፡ በመግባት ፡ ተስፋፍቶ ፡ መያዝ ፡ እንደሚገባው ፡ እንደጥንቱ ፡ ልማድ ፡ ጥፋትን ፡ አምኖ ፡ በግልጽ ፡ ይቅርታን ፡ እንደመጠየቅ ፡ ያሉት ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶችና ፡ (ቍ ፡ ፩፻፴፩) ከሕዝባዊ ፡ መብት ፡ የመሻር ፤ ይልቁንም ፡ ከክብር ፡ ከሞያ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ከቤተሰብ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ መብቶች ፡ የማገድና ፡ የማስወገድ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ (ቍ ፡ ፩፻፴፪) ፤

2ኛ ፤ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ ዋስ ፡ እንዲሰጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ከተገመተም ፡ የወን ጀል ፡ ሥራ ፡ ሳይፈጸምበት ፡ በፊት ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ መሣሪያን ፡ አስቀድሞ ፡ በመውረስ ፡ የሚሰጡት ፡ የግዙፍነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ የጥንቃቄና ፡ የአጠባበቅ ፡ ተግባር ፡ የማስ ፈጸም ፡ ውሳኔዎች ፤

3ኛ ፤ ካንዳንድ ፡ ሥራ ፡ በማገድ ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ በማስወገድ ፡ ማለት ፡ ወንጀል ፡ አድራጊው ፡ በእነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ ከመጠን ፡ አሳልፎ ፡ የተጠቀመባቸው ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ በማሰብ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ወንጀል ፡ ወደ ፡ መሥራት ፡ የሚያዘነ ብል ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ የሚወድቅ ፡ መሆኑ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ ብሔራዊ ፡ መብ ትን ፡ ከመግፈፍ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀትን ፡ (ኮንሴሲዮንን)፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ፈቃድን ፡ የመንጠቅና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ እንዱስት ሪዎችን ፡ ወይም ፡ ለማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ አገልግሎት ፡ የተቋቋሙ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ቤቶችን ፡ በመዝጋት ፡ የሚሰጡ ፡ የተጨማሪ ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔዎች ፡ (ቍ ፡ ፩፻፵፮ ፡ እና ፡ ፩፻፵፯) ፤

4ኛ ፤ ወንጀልን ፡ ከመሥራት ፡ ፈተና ፡ ወይም ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አደጋ ፡ የሚ ያድኑ ፡ የግል ፡ ነጻነትን ፡ በመቀነስ ፡ አንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ከመድረስ ፡ ወይም ፡ ከማዘው ተር ፡ በመከልከል ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ አገር ፡ ከመኖር ፡ ወይም ፡ ውሎ ፡ ከማደር ፡ ባንድ ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ በመኖር ፡ ግዴታ ፡ በግልጽ ፡ የተሰጡትን ፡ ወረቀ ቶች ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በመውሰድ ፡ የሚሰጡ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ (ቍ ፡ ፩፻፵፱ ፡ እስከ ፡ ፩፻፶፬) ፤

5ኛ ፤ በመጨረሻውም ፡ አዲስ ፡ ወንጀል ፡ ከመሥራት ፡ የሚያስጠነቅቁና ፡ የሚ ጠብቁ ፡ የማስጠንቀቅ ፡ አሰጣጥ ፡ ለባለሥልጣን ፡ የማስታወቅና ፡ መረጃ ፡ የመስጠት ፡ የተሰጠውን ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ለሰላማዊ ፡ ሥራ ፡ ማከና ወኛ ፡ (ለአድሚኒስትራሲዮን) ወይም ፡ ለጦር ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የመስጠት ፡ ተገቢ ፡ ለሆነው ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ለጠቅላላው ፡ የሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሚያገለግል ፡ ሆኖ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ የፍርዱ ፡ ውሳኔ ፡ በግልጽ ፡ እንዲወጣ ፡ የማድረግ ፡ የተቀጭውን ፡ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ለማወቅ ፡ ተቀጭው ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ ሊመደብ ፡ የሚችልበትን ፡ ቀና ፡ መንገድ ፡ እንዳያሰናክልበት ፡ ሕጉ ፡ ገልጾ ፡ እንዳመለከ ተው ፡ ሁሉ ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ላልሆኑት ፡ ወይም ፡ በጉዳዩ ፡ ለማያገባቸው ፡ ባዕ ዶች ፡ እንዳይገለጽ ፡ አድርጎ ፡ ፍርዱ ፡ በግል ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ እንዲመዘገብ ፡ የሚሰጡ ፡ የተጨማሪ ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔዎች ፡ (ቍ ፡ ፩፻፷) ።

ሙ) ወደታሰበው ፡ ጠቅላላ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ እነዚህን ፡ በሚገባ ፡ የተመደቡትንና ፡ ተገቢ ፡ ስፍራቸውን ፡ በመያዝም ፡ በመልካም ፡ ቅንጅት ፡ የተደራጁትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሁሉ ፡ አንዱን ፡ ካንደኛው ፡ በማጠቃቀስ ፡ ብቻ ፡ ወደተሻሻለ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ የቻሉበትን ፡ ጠባይ ፡ በቀላሉ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ፡ ብለን ፡ እንገምታለን ።

እንግዲህ ፡ ስለ ፡ ሕጉ ፡ አሠራር ፡ የቅደም - ተከተል ፡ ተራ ፡ (ሎጂክ) አመዳደብ ፡ የሚመለከተውን ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝረን ፡ ካስረዳን ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላለው ፡ የወታደርነቱንና ፡ የጀግንነት ፡ ክብሩን ፡ የመጠበቅ ፡ ባሕሉ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ለታወቀለት ፡ አገር ፡ አስፈላጊና ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ በሆነው ፡ ስለ ፡ አገር ፡ መከላከያ ፡ ኃይል ፡ አጠባበቅ ፡ (ቍ ፡ ፪፻፳) በተሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ አጠገብ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (፫ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ከቍ ፡ ፪፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፺፭) ሕጉ ፡ የተከተለውን ፡ ሥርዓት ፡ ማስረዳት ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ እናምናለን ።

ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ከፍተኛ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የያዘው ፡ አርእስት ፡ የሚያስገኘው ፡ ፍሬ ፡ የተረጋገጠ ፡ ውጤትን ፡ እንዲሰጥ ፡ በሕጉ ፡ ሲሠራ ፡ ከብሔራዊው ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ተዋሕዶ ፡ እንዲገኝ ፡ ማድረጉ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የመንፈስ ፡ ኃይል ፡ የጠየቀ ፡ ከመሆኑም ፡ ይልቅ ፡ ስለ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ድርጅት ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ዠኔቭ ፡ ላይ ፡ ከተደረገው ፡ የእንቴርናሲዮናል ፡ ዲፕሎማቲክ ፡ ኮንቫንሲዮንም ፡ በኋላ ፡ ሆነ ፡ በዠኔቭና ፡ በላሐይ ፡ ኮንቫንሲዮኖች ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ መብት ፡ አጠባበቅ ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንዲጸድቁ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ ማለት ፡ በዲሳምብር ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በወጣው ፡ ሕግ ፡ የተሻሻለው ፡ የሱዊስ ፡ የወታደር ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ በፌቭሪዮ ፡ ፳፯ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የተሻሻለው ፡ የዩጎዝላቭ ፡ የወታደር ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በዡዮ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) እና ፡ በሜ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ)[67] ፡ እንደወጡት ፡ እንደ ፡ ሆላንድ ፡ ያሉ ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ እንኳ ፡ ያልተከተሉትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሚገባ ፡ የገለጸውና ፡ እጅግ ፡ በተራቀቀ ፡ ቅንጅት ፡ አጠናቆ ፡ የሠራው ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተውን ፡ ድንጋጌ ፡ ከማንኛውም ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ቅድሚያ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ያደረገው ፡ እርምጃ ፡ ከማንኛዎቹም ፡ ዘመናዊ ፡ ሕጎች ፡ የበላይነትን ፡ የሚያሰጠውን ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የያዘ ፡ መሆኑ ፡ በፍጹም ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ እነዚህ ፡ የእንቴርናሲዮናል ፡ ወንጀሎች ፡ የተደነገጉት ፡ በራሱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በተሠሩት ፡ በመደበኞቹ ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ከቍ ፡ ፬፻፴፰ ፡ እስከ ፡ ፬፻፶፱) እና ፡ ሕዝብ ፡ እንዲጠቀምባቸው ፡ በሕግ ፡ በተሰጡ ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ከቍ ፡ ፬፻፳ ፡ እስከ ፡ ፬፻፳፰) ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ያደረገው ፡ የመሻሻል ፡ እርምጃ ፡ በቀላል ፡ የሚገመት ፡ አይደለም ፤ ከእነዚህ ፡ ወንጀሎች ፡ የመጀመሪያው ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ጥንታዊና ፡ ቋሚ ፡ ሕጎች ፡ ላይ ፡ የሚጻፈው ፡ ሳይሟላ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንዳንዱ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነና ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በዘመናዊ ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ በመጻፍ ፡ ፋንታ ፡ በልዩ ፡ ሕጎ

---

[67] የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ለመከላከል ፡ ስለሚወሰኑ ፡ ቅጣቶች ፡ ጥናት ፡ በዠኔቭ ፡ በተደረገው ፡ ኮንቫንሲዮን ፡ (ጉባኤ ፡) እ ፡ ኤ ፡ አ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቍጥር ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፩ ፡ እና ፡ በተከታዩ ፤ ረቩዊ ፡ እንቴርናሲዮናል ፡ ደክሪሚናሎዥ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ፖሊስ ፡ ቴክኒክ ፡ በተባለው ፡ መጽሔት ፡ ግራቨን ፡ የጻፈውን ፡ ድርሰት ፡ ተመልከት ። ቤልጅግም ፡ የወንጀልን ፡ ሥራ ፡ ለመከላከል ፡ ስለሚወሰኑ ፡ ቅጣቶች ፡ በዠኔቭ ፡ ኮንቫንሲዮን ፡ (ጉባኤ) የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ አድርጋ ፡ በመከተል ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ አዘጋጅታለች ። እንዲሁም ፡ የሱዊስንና ፡ የዩጎዝላቪያን ፡ ሕጎች ፡ ምሳሌ ፡ በመከተል ፡ አንድ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ለመዘጋጀት ፡ በጥናት ፡ ላይ ፡ ትገኛለች ።

ች ፡ ድንጋጌ ፡ የሚሰጥበት ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ፤ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተሟልቶ ፡ የተሠራበትም ፡ ምክንያት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ የሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ በሰፊው ፡ እንዲጠበቅ ፡ ስለፈለገ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ሊደበቅ ፡ የሚገባውን ፡ የወታደርን ፡ የሥራን ፡ የግል ፡ ሞያ ፡ ሥራን ፡ የሳይንስን ፡ የእንዱስትሪንና ፡ የንግድን ፡ ምስጢር ፡ በመግለጽ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ከቍ ፡ ፬፻፬ ፡ እስከ ፡ ፬፻፱) ፤ የሚመለከቱን ፡ ሁሉ ፡ ሕጉ ፡ በአንድ ፡ መደብ ፡ ሰብስቦ ፡ በማጠናቀቅ ፡ እጅግ ፡ በተከናወነ ፡ ቅንጅት ፡ የተሠሩ ፡ አርእስቶችን ፡ ሰጥቶ ፡ በግልጽ ፡ ያመለከታቸው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በሌላው ፡ ክፍሉ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ በሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ በሕዝብ ፡ ሰላም ፡ በሕዝብ ፡ ረግቶ ፡ መኖር ፡ ላይ ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ (ከቍ ፡ ፬፻፷፩ ፡ እስከ ፡ ፬፻፸፯) ፡ የሚመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎችና ፡ (ስለሴኩሪቴ ፡ ኮሌክቲቭ) ስለ ፡ ጋራ ፡ ጸጥታና ፡ ስለ ፡ መገናኛዎች ፡ አጠባበቅ ፡ ጕዳይ ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በመተላለፍ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ከቍ ፡ ፬፻፸፰ ፡ እስከ ፡ ፭፻፪) ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ድንጋጌ ፡ የቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ይከተል ፡ የነበረውን ፡ አሮጌ ፡ ቅንጅት ፡ አልፎ ፡ የሄደ ፡ በመሆኑ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ በሁለት ፡ ቦታ ፡ ከፋፍሎ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በግል ፡ ሰዎችና ፡ በግል ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚሠሩትን ፡ አለያይቶ ፡ በመጸፍ ፡ ፋንታ ፡ በየአርእስታቸው ፡ በመመደብ ፡ ብቻ ፡ በአንድነት ፡ አጠቃሏቸዋል ። እንዲሁም ፡ የሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ደንቦችን ፡ መጠባበቂያ ፡ የሚሆኑትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡትን ፡ ዕቃዎች ፡ ስለመጠበቅ ፡ የወጣውን፡ ሕግ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፬፻፺፭ ፡ እና ፡ ፬፻፺፮) ፡ በመገናኛዎች ፡ ጸጥታና ፡ ነጻነት ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ በተቋቋሙ ፡ ሥራዎችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገልግሎቶች፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ ለመጠበቅ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ በመገናኛዎችና ፡ በሕዝብ ፡ መመላለሻ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ ስለመጠበቅ ፡ የወጡትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፬፻፺፱ ፡ እና ፡ ፭፻) ፡ የንጹ ፡ መዘዋወርን ፡ መብትና ፡ የሥራ ፡ ነጻነትን ፡ ስለመጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በመድፈር ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፭፻፲፱ ፡ እና ፡ ፭፻፳) ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ለሀገር ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ የተቋቋሙትን ፡ የሞተር ፡ ዕቃዎች ፡ መኪናዎች ፡ የመኪና ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ ተክሎች ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በማፍረስ ፡ የሚደርሱትን ፡ አደጋዎች ፡ ስለመጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በመጣስ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎችና ፡ [ቍ ፡ ፯፻፶፬ ፡ (ለ)] እነዚህንም ፡ የመሳሰሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተጠቃለው ፡ የተሠሩት ፡ በቴክኒክና ፡ በእንዱስትሪ ፡ አቋሙ ፡ በኩል ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ደረጃ ፡ ላልደረሰና ፡ ለወደፊት ፡ ግን ፡ በሙላ ፡ ኃይሉ ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊውን ፡ እርምጃ ፡ ለማድረግ፡ በመጣጣር ፡ ላይ ፡ ለሚገኝ ፡ አገር ፡ ለኤኮኖሚክና ፡ ለሶሺያል ፡ ዕድገቱ ፡ ጠቃሚና ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆነውን ፡ የሚስማማውንም ፡ ቅንጅት ፡ በመምረጥ ፡ ይህንኑ ፡ እንደዋና ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመከተል ፡ ነው ።

የሕዝብ ፡ ጤንነትና ፡ ጽዳትን ፡ ስለመጠበቅ ፡ የቤተሰብንና ፡ የሕፃናትን ፡ አስተዳደግ ፡ ሥርዓት ፡ ማለት ፡ የአገሪቱ ፡ ሕይወታዊ ፡ ኃይሎች ፡ የሆኑትን ፡ ክፍሎች ፡ በሕግ ፡ ስለመጠበቅ ፡ ከዘመናዊው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ጋር ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ በመሄድ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ የዕድገት ፡ ደረጃ ፡ እንዲደርሱ ፡ በተለይ ፡ የሚታሰብበትን ፡ የኤኮኖሚክንና ፡ የንግድን ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ ስለመጠበቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ በተሰጠው ፡ ሁኔታ ፡ የተሠሩትን ፡ የሕጉን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በቅርብ ፡ ብንመረምራቸው ፡ ይህን ፡ ቅንጅት ፡ በመከተል ፡ የተሠሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ለመገንዘብ ፡ እንችላለን ።

አገርን ፡ መግዛት ፡ (ማስተዳደር) ለወደፊት ፡ የሚበጀው ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ተደራጅቶ ፡ እንዲገኝ ፡ ማድረግን ፡ የሚጠይቅ ፡ ከሆነ ፣ ሕግንም ፡ በጊዜው ፡ ተሠርቶ ፡ እንዲገኝ ፡ ማድረግን ፡ ይጠይቃል ።

ስለዚህ ፡ ለዘመናዊው ፡ ኑሮ ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆኑትን ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በጊዜው ፡ መፍጠር ፣ ስለሚያስፈልግ ፣ እነዚህም ፡ ገና ፡ በመፈጠር ፡ ላይ ፡ ስለሆኑ ፣ በሕክምና ፡ ጥበብና ፡ በጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ ስለመጠቀም ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ ሊጠበቁ ፡ የሚገባቸው ፡ ሥርዓቶች ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ታስበባቸው ፡ ተደራጅተው ፡ እንዲገኙ ፡ ለማድረግ ፡ እጅግ ፡ በተጣራና ፡ በተጠናቀቀ ፡ ቅንጅት ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተሠርተዋል ፣ (ከቍ ፡ ፭፻፲፰ ፡ እስከ ፡ ፭፻፳) ፤ እንዲሁም ፡ ኀፍረተ ፡ ነገርን ፡ የሚያሳዩትን ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ አሳትሞ ፡ በማውጣት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ልጆች ፡ በሕሊና ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ የሚጥሉ ፡ ዕቃዎች ፣ ሥዕሎች ፣ ጽሑፎችና ፡ እነዚህንም ፡ የመሳሰሉትንም ፡ በማሳተም ፣ በማሳየት ፣ በአደባባይ ፡ በመግለጽ ፡ በዚህ ፡ አድራጎት ፡ ሊመጣ ፡ የሚችለው ፡ አደጋ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ አድርጎ ፡ ሊታሰብበት ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ጥንቃቄ ፡ የተሞላበት ፡ ድንጋጌ ፡ እንዲኖር ፡ ተደርጓል ፡ (ከቍ ፡ ፮፻፱ ፡ እስከ ፡ ፮፻፲፫) ፤ ምክንያቱም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ የሚመለከተው ፡ ነጥብ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ደርሰዋል ፡ በሚባሉት ፡ አገሮቻችን ፡ ላይ ፡ ያደረሰውን ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ በመረዳታችን ፡ ሲሆን ፡ እንዲሁም ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርቷል ፡ ለሚባሉት ፡ አገሮች ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አደጋ ፡ ለመጠበቅ ፣ ወላጆች ፣ ወይም ፡ የአባትነት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቷቸው ፡ በአላፊነታቸው ፡ የሚያስተዳድሯቸውን ፡ ሕፃናት ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ባለመላክ ፡ የሚፈጸሙትን ፡ ቸልተኛነት ፡ ለመቆጣጠር ፣ (ቍ ፡ ፮፻፳፯) በሕጉ ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ እንዲኖር ፡ በተቀጻሚነት ፡ ታስቦበታል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ በባንክ ፡ ተቀማጭ ፡ አድርጎ ፡ የሚያዝበት ፡ ገንዘብ ፡ ሳይኖረው ፡ ቼክ ፡ በመስጠትና ፡ በአሹራንስ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ የማጭበርበር ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ የሚፈጸሙትን ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፮፻፶፯ ፡ እና ፡ ፮፻፶፱) በሰው ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ተንኮል ፡ በማድረግ ፣ በአደራ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ በተንኮል ፡ በመምራት ፡ ጥቅም ፡ ታገኛለህ ፡ በማለት ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በመደለል ፡ አነሳስቶ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ በመጣል ፣ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ንብረታቸውን ፡ የሚጐዳ ፣ ጥቅማቸውን ፡ የሚያጐድል ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ በማነሳሳት ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ የተንኮል ፡ አድራጎት ፡ የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ የሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎችን ፡ አጥብቆ ፡ ስለመከላከል ፡ (ከቍ ፡ ፮፻፷፫ ፡ እስከ ፡ ፮፻፷፮) ፣ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ በማድረግ ፡ የፋብሪካ ፡ ምልክቶችን ፡ (ማርኮችን) ፡ የተሠሩበትን ፡ ስፍራና ፡ የወጡበትን ፡ እንዱስትሪ ፡ የሚያመለክቱ ፡ ጽሑፎችን ፡ ሥዕሎችንና ፡ ዐይነቶችን ፡ ወደ ፡ ሀሰት ፡ በመለወጥ ፡ የድርሰት ፡ መጻሕፍትን ፡ ወይም ፡ የኪን ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎችን ፡ ሥዕሎችን ፡ ወደ ፡ ሀሰት ፡ በመለወጥ ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ (ከቍ ፡ ፮፻፸፫ ፡ እስከ ፡ ፮፻፸፮) [68] ፡ በምርጫ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫን ፡ ለማግኘት ፡ መደለያ ፡ በመስጠት ፣ ወይም ፡ በመክሰርና ፡ በመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ የማጭበርበር ፡ ተግባር ፡ በመፈጸም ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፮፻፹፯ ፡ እና ፡ ፮፻፹፰) ፣ በመጨረሻውም ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጥርጣሬ ፡ መንፈስ ፡ ነዋሪ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየውን ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ በተሰጣ

---

68 የወንጀልን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ እዋጆች ፡ አለያይቶና ፡ በየስፍራው ፡ እበታትኖ ፡ ከመጻፍ ፡ ይልቅ ፤ ሁሉም ፡ ሰው ፡ በሚያውቀውና ፡ ማናቸውም ፡ በሚገለገልበት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ አጠቃሎ ፡ በመሥራት ፡ ባንድነትና ፡ ባንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገኙ ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ፡ የሚለው ፡ አሳብ ፡ የመነጨው ፡ ከኢትዮጵያዊው ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

ቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ የሚሠራውን ፡ ወይም ፡ ድርጅቶቹ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ የሚያደር ሱትን ፡ ወንጀል ፡ ስለመከላከል ፡ በክብር ፡ ላይ ፡ የሚሠሩትን፡ ወንጀሎችና ፡ (ቍ ፡ ፭፻፸፬) በማኅበር ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ላይ ፡ እምነትን ፡ በማጉደል ፡ የሚሠሩትን ፡ ወንጀሎች ፡ (ቍ ፡ ፮፻፹፱) ለመከላከል ፡ የሚቻልበትን ፡ በቂ ፡ ዘዴ ፡ የማዘጋጀት ፡ ጉዳይ ፡ አስቀ ድሞ ፡ የሚታሰብበት ፡ ሆኖ ፡ ስለተገመተ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ሠርቶ ፡ ማቆየት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ።

የዚህ ፡ ዐይነቶቹ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሁሉ ፡ ተስማሚና ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ የቅጣት ፡ አወሳሰን ፡ መደብ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ተገቢ ፡ ስፍራቸውን ፡ በየረድፋቸው ፡ ይዘው ፡ በደ ንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ ውስጥም ፡ በተስፋፋ ፡ ሁኔታ ፡ ተሠርተው ፡ ይገኛሉ ። ጥንታዊና ፡ ቋሚ ፡ በሆኑት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሚመለከቱት ፡ በያንዳንዶቹ ፡ ነገሮች ፡ አጠገብ ፡ ለዘመናዊው ፡ የአኗኗር ፡ ሕይወት ፡ ተስማሚ ፡ የሆኑትም ፡ ዘመናዊ ፡ አቅድን ፡ የያዙ ፡ ውሳኔዎች ፡ በየቦታቸው ፡ ተመድበዋል ፤ ለምሳሌ ፡ ውድቅ ፡ በሆኑ ፡ ወ ይም ፡ ወደ ፡ ሀሰት ፡ በተለወጡ ፡ የመመላለሻ ፡ ካርኔዎች ፡ (ቲኬቶች) ፡ በትራንስፖርት ፡ ወረቀቶች ፡ (ካርኒዎች) ፡ ያላገባብ ፡ በመጠቀም ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ (ቍ ፡ ፯፻፴፯) ፡ በማዕርግ ፡ ስም ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ችሎታ ፡ በሚሰጡ ፡ ምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ (ሴርቲፊካዎችና ፡ ዲፕሎሞች ፡ ብረቬዎች) ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ በሚደረግ ፡ የፈተና ፡ ውድድር ፡ ውጤት ፡ ማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ወረ ቀት ፡ (ሴርቲፊካ) ያላገባብ ፡ በመጠቀም ፡ ወይም ፡ እነዚህን ፡ የምስክርነት ፡ ማስረጃ ዎች ፡ አጭበርብሮ ፡ በማግኘትና ፡ በነዚህ ፡ በመጠቀም ፡ ስለሚሠራ ፡ የደንብ ፡ መተ ላለፍ ፡ (ቍ ፡ ፯፻፴፰) ወይም ፡ ደግሞ ፡ የቴያትር ፡ ቤቶችንና ፡ የሕዝብ ፡ መደሰቻ ፡ ስፍራዎችን ፡ ስለመጠበቅ ፡ የወጣውን ፡ ደንብ ፡ በመተላለፍ ፡ (ቍ ፡ ፯፻፸፯ ፡ እና ፡ ፯፻፹፪) ፡ የሕንጻ ፡ ሥራዎችን ፡ የሥራ ፡ ክንውን ፡ ስለመጠበቅ ፡ የመገናኛዎችን ፡ ጸጥታ ፡ የሚፈነዱ ፡ መሣሪያዎችንና ፡ አደገኛ ፡ ነገሮችን ፡ ስለመጠበቅ ፡ (ቍ ፡ ፯፻፹፩ ፡ ፯፻፹፫ ፡ እና ፡ ፯፻፹፬) ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጤንነት ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጽዳትና ፡ ንጽሕና ፡ አጠባበቅ ፡ መርዛም ፡ አፍዛዥና ፡ ጉዳትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ቅመማትን ፡ መጠጦችንና ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለመቆጣጠር ፡ የወጡትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመጣስ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ (ቍ ፡ ፯፻፹፭ ፡ እና ፡ ተከታዩ) እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ድንጋ ጌዎች ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ሰፍረዋል ።

## (ሐ) ማጠቃለያ ፤

እንግዲህ ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕግ ፡ ሌሎች ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ለአሠራራቸው ፡ ቅን ጅት ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ከሚከተሉት ፡ ባሕሎች ፡ ጋር ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንዲራመዱ ፡ በማድረግ ፡ ለዘመናዊው ፡ ሕይወት ፡ የሚስማሙትን ፡ ነገሮች ፡ በመምረጥ ፡ አሻሽሎና ፡ ተመሳሳይነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ አድርጎ ፡ በማጠቃለል ፡ የያዛቸው ፡ በሕግም ፡ እንዲጠ በቁ ፡ ያደረጋቸው ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሰጠነው ፡ ሐተታ ፡ የገለጽ ናቸውን ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሆኑን ፡ አስረድተናል ።

በሕጉ ፡ አሠራር ፡ ጠቅላላነትም ፡ ሆነ ፡ በውስጡ ፡ በሚገኙት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዝር ዝር ፡ አቀራረብ ፡ ረገድ ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ አንድ ፡ የተሟላ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕንጻ ፡ (አንድ ፡ አዲስ ፡ ቤት) ሠርቶ ፡ ለማስረከብ ፡ የተቻለውን ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ አድርጓል ። ይህንንም ፡ እጅግ ፡ የተሟላ ፡ ሥራውን ፡ በማውሳት ፡ በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) የሱዊስን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ የሠሩት ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ በበኩላቸው ፡ ተናግረውት ፡ እንደነ

በረው ፡ ሁሉ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ ሥርዓትንና ፡ ሰላምን ፡ ጸጥታንና ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃን ፡ ለማትረፍ ፡ የሚያስችል ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ስለሆነ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ በቂ ፡ መተማመኛ ፡ መሆኑ ፡ ተረጋግጧል ።

ይህ ፡ እጅግ ፡ ዘመናዊ ፡ የሆነ ፡ የፍርድ ፡ መሣሪያ ፡ በጣም ፡ አዲስ ፡ ከመሆኑም ፡ ይልቅ ፡ አገልግሎቱን ፡ እንዲሰጥ ፡ የተዘጋጀለት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመግባት ፡ በሚያደርገው ፡ እርምጃ ፡ ቆራጥነትንና ፡ ደፋርነትን ፡ እንደሚጠይቀው ፡ የማያጠራጥር ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ በሚያስገኘው ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ እንዲችልና ፡ ያስገኛል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ የተጣለበትንም ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ እንዲያተርፍ ፡ ያለንን ፡ ጥልቅ ፡ ምኞት ፡ እንገልጻለን ።

ለአንድ ፡ አገር ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ በመስጠት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ለማንም ፡ የተሰወረ ፡ አይደለም ። ለኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ በር ፡ ከፋችና ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ሰጭ ፡ የሆኑት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የዚህን ፡ ሥራ ፡ አላፊነት ፡ ራሳቸው ፡ ሲወስዱ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲደርስ ፡ ያላቸውን ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ በፈጣሪያቸው ፡ ላይ ፡ በመተው ፡ "ሰው ፡ ይጀምራል ፡ የመጨረስ ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው ፤" በሚል ፡ ሐሳብ ፡ ተነሳስተው ፡ የሚወዱትን ፡ ሕዝባቸውን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ለማድረስ ፡ የዘወትር ፡ ጥረታቸው ፡ ስለሆነና [69] ፡ ለዚህም ፡ የተቀበሉትን ፡ አደራና ፡ ያለባቸውን ፡ አላፊነት ፡ በተለመደ ፡ እርቆ ፡ አስተዋይነታቸው ፡ እየመሩ ፡ በብዙ ፡ ጥረት ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲደርስ ፡ ያደረጉት ፡ ይህ ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ ሥራው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አላፊነትንና ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ መሻሻልን ፡ የሚያቋቁም ፡ እውነተኛ ፡ ተግባር ፡ ነው ።

ከአዲሱ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ዘመናዊ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ ትይዩ ፡ ሆኖ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንዲራመድ ፡ ስለተደረገው ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ መስፋፋት ፡ ሕጉን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውሉ ፡ ከፍተኛ ፡ የፍርድ ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ ስለመፍጠር ፡ የሞያ ፡ ሥራቸው ፡ በተለይ ፡ የሕግ ፡ ሊቅነት ፡ የሆነ ፡ ዳኞችን ፡ መርጦ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ስለመመደብ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ደረጃና ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸውን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንደገና ፡ ለስማቋቋምና ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ዘመናዊ ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሻሻል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በጻፍነው ፡ ድርሰታችን ፡ ላይ ፡ አብራርተን ፡ የገለጽን ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ በመቅድማችን ፡ ላይ ፡ መላልሶ ፡ መጻፍ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ። ጉዳዩን ፡ በመረመርንበት ፡ ጊዜ ፡ እንደገለጽነው ፡ ሁሉ ፡ ለመጭው ፡ ዘመን ፡ ልናስብበት ፡ የሚገባንንም ፡ ጭምር ፡ ሥግለጽ ፡ ስላለብን ፡ ሕግ ፡ ሰጭዎች ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ ሥራቸውን ፡ አከናውነው ፡ ሕጉን ፡ ካስረከቡ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ታሪካዊ ፡ ሕግ ፡ እውነተኛ ፡ ፍሬውን ፡ እንዲሰጥ ፡ የተረጋገጠ ፡ ዋስትና ፡ ያለውን ፡ ውጤት ፡ እንዲያስገኝ ፡ የዳኝነቱ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የፍርዱና ፡ የፔናሎዢኩ ፡ (የቅጣቶችና ፡ ወንጀል ፡ መከላከል ፡ የስር ፡ ቤቶ

[69] የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሥራዎችና ፡ በየጊዜው ፡ የሚያደርጉዋቸው ፡ ንግግሮች ፡ ሁሉ ፡ ጉዳዩን ፡ በግልጽ ፡ የሚያስረዱን ፡ ናቸው ። የግርማዊነታቸውን ፡ ሰውነትና ፡ የዘመነ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ታሪካዊ ፡ እርምጃ ፡ በቅርብ ፡ ለመመልከት ፡ ዕድል ፡ የገጠመው ፡ ሁሉ ፡ ሊያምንበት ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ይበልጥ ፡ ለመረዳት ፡ በ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታወጀውን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ መቅድም ፤ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተቋቋመበትን ፡ የአዋጅ ፡ ቃልና ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱንም ፡ በፈርማቸው ፡ ሲያጸድቁ ፡ በመሳፍንቱና ፡ በመኳንንቱ ፡ በጳጳሳቱና ፡ በሊቃውንቱ ፡ በኮር ፡ ዲፕሎማቲኮች ፡ ፊት ፡ ያደረጉትን ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ (ከዚህ ፡ በፊት ፡ የጠቀስነውን ፡ ዝርንጐል ፡ ዱዊፕሬይ ፡ የጻፈውን ፡ ድርሰት ፡ ከገጽ ፡ ፫፻ ፡ እስከ ፡ ፫፻፲ ፡ ተመልከት ፤ እንዲሁም ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በዓል ፡ በተከበረ ፡ ጊዜ ፡ የተሻሻለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሲያጸድቁና ፡ አዲሱን ፡ ሕግ ፡ ሲያውጁ ፡ ያደረጉትን ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ ከፍተኛ ፡ ነጥቦቹን ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ጠቅሰናቸዋል ።) የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ አከባበር ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ፓሪስ ፡ የታተመውን ፡ መጽሔት ፡ ቍ ፡ ፴፬ ፡ ገጽ ፡ ፲፭ ፡ እና ፡ ተከታዩን ፡ እንደገና ፡ ማንበብ ፡ በቂ ፡ ነው ።

ችና ፡ የጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ቤቶች ፡ ጥናት ፡ ዕውቀቱ) ቅንጅት ፡ ዘመናዊ ፡ እርምጃውን ፡ ያለመሰናከል ፡ እንዲቀጥል ፡ በማድረግ ፡ ከብዙ ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ ከዓለም ፡ ሁሉ ፡ ቀደምትነት ፡ ያለውን ፡ ጥንታዊ ፡ የፍርድ ፡ ሥርዓትና ፡ የዳኝነት ፡ አቋሙን ፡ ይዞ ፡ የኖረው ፡ አገር ፡ ተገቢውን ፡ ስፍራ ፡ እንደያዘ ፡ እንዲኖር ፡ የማድረጉ ፡ አላፊነት ፡ የሚመለከተው ፡ የተረከቡትን ፡ ታሪካዊ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውሉ ፡ ተመርጠው ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ የተመደቡትን ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ነው ።

የሥራውን ፡ ከባድነት ፡ በጥልቅ ፡ የሚመረምር ፡ ሁሉ ፡ ከዥስቲኒየስ ፡ ወይም ፡ ከቆስጠንጢኖስ ፡ ጥንታዊ ፡ ሕግ ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብ ፡ ሕግ ፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ [70] ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ እየተሻሻለ ፡ መጥቶ ፡ እስከዚህ ፡ ደረጃ ፡ የተራመደውን ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎችን ፡ ለማግኘትና ፡ ድርጅቶችን ፡ ለማቋቋም ፡ የሚደርሰውን ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ስለሚረዳው ፡ ለዚህ ፡ ፕሮብሌም ፡ በቂ ፡ ፍች ፡ ሊገኝ ፡ ይችል ፡ ይሆንን ? ብሎ ፡ መጠየቁ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ትእግሥትን ፡ ረቂቅነትን ፡ ቆራጥነትንና ፡ ደፋር ፡ የሆነ ፡ የሙንፈስ ፡ ጥንካሬን ፡ የሚጠይቅ ፡ ሥራ ፡ በመከናወን ፡ ላይ ፡ ይገኛል [71] ፤ ወደ ፡ ግቡ ፡ እንደሚደርስም ፡ ያለን ፡ ጽኑ ፡ እምነት ፡ የማያወላውል ፡ ነው ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በመጋቢት ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮንን ፡ ጉባኤ ፡ ከፍተው ፡ በመረቁ ፡ ጊዜ ፡ "ይህን ፡ ለሕይወታችን ፡ እንደከፍተኛ ፡ ሥራ ፡ አድርገን ፡ የጀመርነውን ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ እንዲያበቃንና ፡ የሥራውም ፡ ውጤት ፡ ለሙጭው ፡ ትውልድ ፡ ደኅንነትን ፡ እንዲያስገኝለት ፡ የተቀደሰ ፡ ፈቃዱ ፡ ይሆ

---

[70] ካሁን ፡ ቀደም ፡ በጠቀስነው ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) በታተመው ፡ መጽሔት ፡ በገጽ ፡ ፪፻፷፯ ፡ እና ፡ በተከታዩ ፡ እንደገለጽነው ፤ በተለይ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የሥራ ፡ መሪዎችን ፡ ለማሠልጠን ፡ ይልቁንም ፡ በየካቲት ፡ ፲፱ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተመረቀ ፡ በውስጡ ፡ የሕግ ፡ ኮሌጅ ፡ ያለው ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አቋቁሞ ፡ የተለየ ፡ ሞያቸው ፡ የሕግ ፡ ሊቅነት ፡ የሆነ ፡ ሰዎች ፡ ለማግኘትና ፡ በዚህ ፡ ኮሌጅም ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ከተመረቁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ በትልልቅ ፡ የሕግ ፡ ዩኒቨርሲቲዎች ፡ ትምህርታቸውን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ እንዲያደርሱ ፡ በማድረግ ፡ ቍጥራቸው ፡ በየጊዜው ፡ እያደገ ፡ የሚሄድ ፡ የሕግ ፡ ሰዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የተደረገውን ፡ ጥረትና ፡ ያስገኘውንም ፡ ውጤት ፡ አብራርተን ፡ የጻፍነውን ፡ ተመልከት ።

[71] ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በዓል ፡ በተከበረ ፡ ጊዜ ፡ በፓርላማ ፡ የተደረገው ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ በ፵ቱ ፡ ዓመት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የተፈጸሙትን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሥራዎች ፡ በመግለጽ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያላቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ ያስረዳናል ፤ (የተጠቀሰውን ፡ ቡለቲን ፡ ገጽ ፡ ፲፩ ፡ እና ፡ ተከታዩን ፡ ተመልከት) ፤ ይኸውም ፡ በመጀመሪያው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከ፵፰ ፡ የማይበልጥ ፡ የነበረው ፡ ሆስፒታሎችና ፡ የሕክምና ፡ መስጫ ፡ ጣቢያዎች ፡ የዛሬው ፡ የዘውድ በዓል ፡ በኢዮቤልዩ ፡ በተከበረበት ፡ በ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፪፻፶ ፡ ደርሷል ። በሕዝብ ፡ ጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ረገድ ፡ የተደረገው ፡ የሥራ ፡ ድካም ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ በመስጠቱ ፡ መደበኛውን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃና ፡ የሕዝቡን ፡ ሕይወት ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ አድርሶታል ፤ የሕፃናት ፡ ሞት ፡ እጅግ ፡ በመቀነሱ ፡ የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ከዕለት ፡ ወደ ፡ ዕለት ፡ እያደገ ፡ ሄዷዋል ፤ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከነበሩት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያሉት ፡ ብዛት ፡ በ፴፮ ፡ አጠፌታ ፡ ጨምሯል ። ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚላኩትና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የሚመጡት ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ከ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በአራት ፡ አጠፌታ ፡ አድገዋል ፤ ከቅባት ፡ ፍሬዎችና ፡ ከዘይት ፡ እህሎች ፡ ከቆዳ ፡ ጋር ፡ የአገሪቱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ንግድ ፡ ዋና ፡ የኤኮኖሚ ፡ ምንጭ ፡ የሆነውን ፡ የቡናን ፡ ሰብል ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድም ፡ እንደዚሁ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በ፵ ፡ ዓመት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ሰብሉ ፡ በአሥር ፡ አጠፌታ ፡ አድጓል ። ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ ከአምስት ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ ያልነበረው ፡ የአገሪቱ ፡ የዓመት ፡ ወጭ ፡ በጀት ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከአንድ ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ አልፏል ፤ በ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከ፰ ፡ ሚሊዮን ፡ የማይበልጥ ፡ የነበረው ፡ በገበያ ፡ ላይ ፡ የሚዘዋወረው ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከ፪፻፳ ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ ሆኗል ፤ እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በወርቅ ፡ የሚከፈለው ፡ የገንዘብ ፡ መጠን ፡ በ፳ ፡ አጠፌታ ፡ ከፍ ፡ ብሏል ። ከፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ድርጅት ፡ መቋቋም ፡ እርምጃ ፡ ይልቅ ፡ በመጨረሻዎቹ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ የተደረገው ፡ ጠቅላላ ፡ የመሻሻል ፡ እርምጃ ፡ ዝግ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተቋቋሙት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብዛት ፡ ሸሪአ ፡ ከሚባለው ፡ የእስላም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጭምር ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆኑት ፡ ምክትል ፡ ወረዳ ፡ የሚባሉት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በቍጥር ፡ ውስጥ ፡ ሳይገቡ ፡ ከ፭፻፹፪ ፡ እስከ ፡ ፰፻፶ ፡ ደርሷል ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ እርምጃ ፡ እየተሻሻለ ፡ የሚቀጥለው ፡ አስተዳደር ፡ በመሪዎቹ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ አዲስ ፡ ተግባርና ፡ አዲስ ፡ አላፊነት ፡ በመዘርዘር ፡ ይገልጻል ።

ንልን ፡ ዘንድ ፡ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ ፈጣሪያችንን ፡ እንለምነዋለን ፤'' ሲሉ ፡ በተናገሩት ፡ ቃል ፡ የሥራውን ፡ ከባድነት ፡ አመዛዝነውታል ። እንዲሁም ፡ ይህን ፡ እጅግ ፡ ከባድና ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሕሊና ፡ ደስታን ፡ የሚያስገኘውን ፡ ሥራ ፡ ለማቋቋም ፡ እንድንረዳ [72] ፡ ተጠርተን ፡ ባገለገልንበት ፡ በረጅሙ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሐሳባችን ፡ ተለይቶ ፡ የማያውቀውን ፡ ስናስታውስ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ምሕረት ፡ ሕጉን ፡ ባወጁ ፡ ጊዜ ፡ ባሰሙት ፡ መቅድማዊ ፡ ቃል ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ "የፍርድ ፡ ምንጭ [73] ፡ የጥበብና ፡ የሀብት ፡ መገኛ ፡ በሆነ ፡ ሁሉን ፡ በሚችል ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ለአሁኑ ፡ ሕዝባችንና ፡ ለመጭው ፡ ትውልድ ፡ ለሰላሙና ፡ ለደኅንነቱ ፡ እንዲሆን ፡ እናምናለን ፤'' ሲሉ ፡ በተናገሩት ፡ የሕሊና ፡ ሰላምና ፡ እምነት ፡ በተመላበት ፡ ንግግራቸው ፡ ሕጉ ፡ ለአገራቸው ፡ ሊያስገኝ፡ የሚችለውን፡እውነተኛ፡ጥቅም ተረድተውታል።

ዣን ፡ ግራቨን ፡ (ሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ። -

[72] ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በተናገሩት ፡ ቃል ፡ በራሳቸው ፡ የበላይ ፡ ጠባቂነትና ፡ የቅርብ ፡ መሪነት ፡ በአበራታችነታቸውም ፡ ሕጉን ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ የተጠሩት ፡ የኤውሮፓ ፡ ሊቃውንቶች ፡ ስላሳዩት ፡ ትጋትና ፡ ስላስገኙት ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ ሰጥተዋቸዋል ፤ በንግግራቸውም ፡ ውስጥ ፡ «በመሪነታችንና ፡ በራሳችን ፡ አላፊነት ፡ እየተቆጣጠርን ፡ በማሠራት ፡ ያስጀመርነው ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ የረዱንን ፡ ሊቃውንት ፡ ልናመሰግናቸው ፡ እንወዳለን ፤ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ የንግድና ፡ የባሕር ፡ ሕጎች ፡ የተሠሩት ፡ የጥንታዊቱን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባሕላዊ ፡ ፋና ፡ ብርሃን ፡ በመከተል ፡ ለዛሬውና ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡ የሚጠቅመውን ፡ በመምረጥና ፡ በዘመናዊ ፡ ዘዴ ፡ በማሻሻል ፡ ሲሆን ፡ ሥራውም ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፡ ለምንወደው ፡ ሕዝባችን ፡ መልካም ፡ ኑሮና ፡ ደኅንነት ፡ ዋስትናን ፡ በመስጠት ፡ በተዘጋጀው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ለመጠቀም ፡ እምነት ፡ አለን ፤ ይኸውም ፡ በሕይወታችን ፡ ከሠራነው ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ የምንቆጥረው ፡ ነው ፤ የአስተዳደሩ ፡ አቋም ፡ የተለያየም ፡ ቢሆን ፡ ለአንድ ፡ መንግሥት ፡ ከሚያስፈልጉት ፡ ነገሮች ፡ ዋነኛው ፡ ሕግ ፡ ነው» የሚሉ ፡ ቃላት ፡ ይገኙበታል ።

[73] ከዚህም ፡ በቀር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የዘፋን ፡ ንግግር ፡ በተለይ ፡ ይጠቅመናል ፡ ብለን ፡ የተነሳንበትን ፡ ሥራ ፡ ማለት ፡ የሕጉን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ማብራሪያ ፡ በመስጠት ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ በሚጠብቁት ፡ አንቀጾች ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ከፍተኛ ፡ ጥቅም ፡ በመጥቀስ ፤ የሰውን ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ ስለመጠበቅና ፡ ስለመሠረታዊያን ፡ ነፃነቶች ፡ አጠባበቅ ፡ ብቻ ፡ ከ፴፯ ፡ አንቀጾች ፡ የማያንሱ ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተመልክተውበት ፡ ይገኛል ፤ እያንዳንዱም ፡ አንቀጽ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ባሕል ፡ በመመንጨትም ፡ ሆነ ፡ በሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ከሚገኙት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የነፃነት ፡ አሰጣጥ ፡ ደረጃ ፡ ከያዙት ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ በመከተል ፡ ረገድ ፡ ከመላው ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ከደረሱት ፡ ከብዙዎቹ ፡ አገሮች ፡ የያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ የግል ፡ መብት ፡ ስለመጠበቅ ፡ ካሰጡት ፡ ሕግ ፡ እጅግ ፡ የበለጡ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ፤ በዚህም ፡ ሁኔታ ፡ የማንም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ በኩል ፡ የተጠበቀ ፡ መሆኑን ፤ ስለ ፡ ብሔራዊ ፡ መብት ፡ አጠባበቅም ፡ በማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ መካከል ፡ ፈጽሞ ፡ ልዩነት ፡ የማይደረግ ፡ ስለመሆኑ ፤ በወንጀል ፡ ረገድም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አጥፍተሃል ፡ ተብሎ ፡ ቢከሰስ ፡ በሕግ ፡ እስኪመሰከርበት ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ንጹሕ ፡ ተቆጥሮ ፡ መብቱ ፡ የሚጠበቅለት ፡ ስለመሆኑ ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ በግልጽ ፡ አጭበርብሮ ፡ እጅ ፡ ተፍንጅ ፡ ካልተያዘ ፡ በቀር ፡ በዕዳ ፡ ምክንያት ፡ የማይታሰር ፡ ስለመሆኑ ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ማንኛውም ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ የደረሰ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ላይ ፡ ያልፈቀደውን ፡ የተሻሻለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ብቻ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በደል ፡ ቢደርስበት ፤ በማንኛውም ፡ ሚኒስቴር ፤ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ በማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ለሆነ ፡ ሁሉ ፡ የተጠበቀ ፡ መሆኑ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አቤቱታውን ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ስለሚገኝ ፡ የሕዝቡን ፡ ብሔራዊ ፡ መብት ፡ የሚጠብቁት ፡ በሕግ ፡ የተቋቋሙት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ራሳቸው ፡ ጭምር ፡ ሕጉን ፡ የሚያስፈጽሙ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ፡ ባደረጉት ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ ውስጥ ፡ «ይህን ፡ በሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ የሰጠነውን ፡ መብት ፡ ለሕዝባችን ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ለማድረግ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፡ የተቋቋሙት ፡ የማንኛውም ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆኑ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ ድርጅቶች ፡ ሕጉን ፡ አክብረው ፡ እንዲያስከብሩና ፡ ፈጽመው ፡ እንዲያስፈጽሙ ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ እየተቆጣጠርን ፡ እናስፈጽማለን» ብለዋል ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ከሚገኘው ፡ ከዝቅተኛው ፡ ሰው ፤ ከመጨረሻው ፡ ደኃ ፡ እስከ ፡ ከፍተኛው ፡ ሀብታም ፡ ድረስ ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ሁሉ ፡ አንዳችም ፡ ልዩነት ፡ ሳይኖርባቸው ፤ በወሕኒ ፡ ቤት ፡ እስከሚገኘው ፡ ወንጀለኛም ፡ ድረስ ፡ ብሔራዊና ፡ ግላዊ ፡ መብቱ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተጠበቀለት ፡ ስለሆነና ፡ መሠረታዊ ፡ ነፃነቱም ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ እንዳይነካበት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ራሳቸው ፡ የሚጠብቁለት ፡ ለመሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ዋስትና ፡ አለው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሰፊ ፡ መሻሻልና ፡ የሕጎችም ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፡ ባጭሩ ፡ ይህ ፡ ነው ።